# ቤተ ክርስቲያን መትከል

ዳግ ሂዋርድ ሚልስ

ተርጓሚ፡- ሬቨረንድ አማኑኤል ቶማስ

አርታኢ፡- መጋቢ ልዑል ኃይሉ

ካልተገለጸ በቀር፣ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያሉ ጥቅሶች ሁሉ የተወሰዱት በ1954 ዓ.ም ከታተመው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ነው።

Email Dag Heward- Mills :
bishop@daghewardmills.org
evangelist@daghewardmills.org

Find out more about Dag Heward Mills at:
www. daghewardmills.org

www. lighthousechapel.org

www.healingjesuscrusade.org

Write to:
Dag Heward-Mills
P.o. Box 114
Korle-Bu
Accra
Ghana

ላይትሃውስ ቻፕል ኢንተርናሽናል

መ.ሳ. ቁጥር 15134

አዲስ አበባ

ኢትዮጵያ

ይህን መጽሐፍ በሙሉም ሆነ በከፊል ያለ አሳታሚው ፈቃድ ማባዛት የተከለከለ ነው።

# መታሰቢያነቱ

ለ፡- ኒ አጆዱ እና አድጎዲ አማር

ስለ ወዳጅነታችሁ፣ ድጋፋችሁ እና ስለ ማተሚያ ቤቱ አመሰግናችኋለሁ!

## ማውጫ


1. ቤተ ክርስቲያን ማስፋፋት .............................................. 1
2. የቤተ ክርስቲያን ተካዮች አስተሳሰብ.............................................. 7
3. የቤተ ክርስቲያን ተካዮች ሥራ..............................................26
4. ቤተ ክርስቲያን መትከል እና የኢየሩሳሌሟ ቤተ ክርስቲያን.............31
5. ቤተ ክርስቲያን መትከል እና የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን...............39
6. መስበክ፣ ማስተማር እና ቤተ ክርስቲያናትን መትከል...................42
7. ስብከት ለምን ኃያል ሆነ..............................................51
8. ማስተማር ኃያል ነገር የሆነው ለምንድር ነው..........................65
9. ቤተ ክርስቲያን መትከል እና የድንኳን አገልግሎት........................71
10. እንዴት እና መቼ ወደ ድንኳን አገልግሎት መግባት እንደሚቻል.....77
11. መካንነት እና ቤተ ክርስቲያን መትከል....................................90
12. መካንነትን እንዴት ለይቶ ማወቅ እንደሚቻል..........................99
13. የተለያዩ ዓይነት መካንነቶችን እንዴት መዋጋት ይቻላል.............103
14. ምልጃ ከመካንነት የመውጫ መንገድ..........................123
15. ቃል ኪዳናት እና ቤተ ክርስቲያንን መትከል............................128
16. የርብቃ ቅባት..............................................................130
17. መሥዋዕትነትና ቤተ ክርስቲያንን መትከል............................132
18. መታዘዝ እና ቤተ ክርስቲያን መትከል..................................146
19. ቤተ ክርስቲያን መትከል እና የክህነት አገልግሎት......................162
20. ቤተ ክርስቲያን እንዴት ይተከላል........................................165
21. የቤተ ክርስቲያናት መረብ መዘርጋት......................................177

# ቤተ ክርስቲያን ማስፋፋት

## ወደ ፊት መግፋት

አንዳንድ ጊዜ አንድ ሰው በእርግጥ ቤተ ክርስቲያን ወደ ፊት እየገሰገሰች ነው ወይስ አይደለም ብሎ ግራ ሊጋባ ይችላል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ እንቅስቃሴዎች እና ፕሮግራሞች በመካሄድ ላይ ናቸው። ግን በእርግጥ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደፊት እየገሰገሰች ናት ወይስ ዙሪያ ጥምጥም እየዞረች ነው?

አንዳንድ ጊዜ በትላልቅ ከተሞች ውስጥ አዳዲስ ቤተ ክርስቲያኖች ሲያብቡ ትመለከታለህ። አብዛኛውን ጊዜ፣ እነኚህ አዳዲስ ቤተ ክርስቲያኖች የከተማው ወሬ ይሆኑና እግዚአብሔር አዲስ ነገር እየሠራ ይመስላል። ሁሉም ሰው ወደ እነዚህ ቤተ ክርስቲያናት ይጎርፋል እናም ይህን አዲስ ነገር የሚወደው ይመስላል። ይሁንና ግን ይህን አዲስ እንቅስቃሴ ጠጋ ብለህ ስትመለከት፣ አብዛኛውን ጊዜ አዲሶቹ ጉባዔዎች የተመሠረቱት በአካባቢው ካሉ ሌሎች ቤተ ክርስቲያናት በፈለሱ ሰዎች መሆኑን ትረዳለህ።

የእግዚአብሔር መንግሥት ሁልጊዜ አዲስና የሚያስደንቅ ነገር በሚፈልጉ ሥጋዊ ክርስቲያኖች የተሞላች ነች። ብዙ መጋቢዎች ቤተ ክርስቲያናቸው እያደገች እና መንፈሳዊ መነቃቃት (ሪቫይቫል) የመጣ እየመሰላቸው ይደነቃሉ። እውነታው ግን፣ በእግዚአብሔር መንግሥት

ውስጥ ያለው አጠቃላይ ዕድገት በጣም ውስን ነው። ሰዎች ዝም ብለው ከቤተ ክርስቲያን ወደ ቤተ ክርስቲያን እየዞሩ ነው። **የእግዚአብሔር መንግሥት የእውነት ወደ ፊት መገስገስ አለባት።**

ከዓመታት በፊት አውሮፓውያን የወንጌል መልእክተኞችን ወደ አፍሪካ እና ወደ እስያ ላኩ። በዚህ የመሥዋዕትነት እርምጃ ውስጥ፣ አገሮች ሁሉ ክርስትናን ተቀበሉ። ቀድሞ አረማዊ የነበሩ ሕዝቦች ወደ ክርስቲያንነት ተለወጡ። ራሳችንን አናስት፤ በዛሬውም ዓለም ውስጥ ብዙ ሰዎች አሉ። እንዲሁም ውጤታማ ቤተ ክርስቲያን እና መጋቢዎች የሌላቸው ብዙ ሰዎች አሉ። እንዲያውም ዛሬ ክርስትና ወዳልደረሰባቸው ግዛቶች የቤተ ክርስቲያን መስፋት በከፍተኛ ደረጃ ይፈለጋል።

የዛሬ ሁለት መቶ ዓመት አውሮፓውያን የወንጌል መልእክተኞችን ሲልኩ፣ በዓለም ላይ የነበረው የሕዝብ ብዛት አንድ ቢልዮን ብቻ ነበር። ዛሬ፣ እ.አ.አ በ2004፣ በዓለም ላይ 6.1 ቢሊዮን ሕዝብ አለ። ዓለም የዶክተሮች ቁጥር እና የሕዝብ ብዛትን እያነጻጸረ ያጉረመርማል። የመጋቢዎችን ብዛት ከሕዝብ ብዛት ጋር አነጻጽሮ ያማረረ አለ? በዚህ ዘመን ያለውን የሕዝብ ብዛት ካሉት ወንጌላዊያን ሲነጻጸር ምን ያህል ነው?

## የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዴት ማስፋት ይቻላል?

የእግዚአብሔር መንግሥት በእውነት የምትሰፋው የክርስቶስን መመሪያ ስንከተል ነው። የኢየሱስ የመጨረሻ ትእዛዝ ወደ ዓለም ሁሉ በመሄድ ደቀ መዛሙርትን እንድናፈራ ነው!

> ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናገራቸው፡- ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ። **እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ** በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ **እያስተማራችኋቸው** ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።
>
> ማቴዎስ 28፡18-20



በዚህ ጥቅስ ውስጥ፣ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ቃል እንድናስተምር ይነግረናል። ሰዎችን በቋሚነት በአንድነት ካልሰበሰብካቸው በስተቀር ልታስተምራቸው የምትችልበት ምንም ዓይነት መንገድ የለም።

## ቤተ ክርስቲያን በእርግጥ ምንድር ነች

ለትምህርት ዓላማ በቋሚነት የሚከማች የክርስቲያኖች ስብስብ "ቤተ ክርስቲያን" ይባላል። በሌላ አነጋገር፣ ጌታችን ወደ ዓለም ሁሉ በመሄድና ሰዎችን በቋሚነት *በማሰባሰብ* ቃሉን እንድናስተምራቸው ይናገረናል። እግዚአብሔር ሊማሩ የሚችሉ ሰዎችን *በመሰብሰብና* በማስተማር ሥራ ውስጥ ይገኛል። እግዚአብሔር በመንፈሱ ወደ ዓለም ሁሉ በመሄድ ሰዎችን በቋሚነት በመሰብሰብ ቃሉን የሚያስተምሩ ሰዎችን በማስነሣት ላይ ነው።

በርካታ ስብሰቦች እና ቡድኖች ባሉ መጠን፣ ታላቁ ተልእኮ በይበልጥ እየተፈጸመ ይሄዳል። የተማሩ ብዙ ቡድኖች ባሉ መጠን፣ ታላቁ ተልእኮ እየተፈጸመ ይሄዳል። እነኚህ ቡድኖች ታዛዥ በሆኑ የጌታ ባሪያዎች የተተከሉ ናቸው።

## ሰዎችን ማስደነቅ እንፈልጋለን

የሚያሳዝነው ነገር፣ ብዙ መጋቢዎች ምን ያስባሉ የሚለው ነገር በጣም ስለሚያሳስባቸው፣ ታላቁን ተልዕኮ እንደሚገባ ሊፈጽሙ አይችሉም። የሁሉም ሰዎችን ትኩረት የሚስብ አንድ ትልቅ ጉባዔ እንዲኖረን እንፈልጋለን! ሰዎች ታላቅ ነው እንዲሉን እንፈልጋለን! ለነገሩማ፣ በጉባዔው ውስጥ ብዙ ሰዎች ባሉ መጠን፣ መጋቢዎች ታላቅ ሰው ይመስላሉ።

> የንጉሥ **ክብር በሕዝብ** ብዛት ነው፤ . . .
>
> ምሳሌ 14፡28

ታላቁን ተልእኮ ለመፈጸም በሚቻልበት ስፍራ ሁሉ ብዙ የሰዎች ስብስብን መጀመር ያስፈልጋል። የዓለም ስፋት እና የሰዎች ስርጭት መጋቢዎችና ሰዎች ***ከአንድ ጉባዔ ቤተ ክርስቲያን ወደ ተለያዩ ስፍራዎች በመሄድ ብዙ ስብስቦችን እንዲጀምሩ ግድ ይላል።*** ጌታችንን ለመታዘዝ ቁርጠኞች ከሆንን፣ ይህንን ከመታዘዝ ውጭ ምርጫ የለንም።

መሪዎች ሊሰለጥኑ ይገባል። መጋቢዎች ሊሰለጥኑ ይገባል። ሠራተኞች ሊሰለጥኑ ይገባል። "ከሁሉ በላይ ነኝ" የሚለው የቤተ ክርስቲያን አስተሳሰብ ሊሞት ይገባዋል። ይህ ከእኔ በላይ የለም ዓይነት አስተሳሰብ ሁሉም ሰው እውቅና የሚሰጠውና የሚያወድሰው አንድ ታላቅ መጋቢ እንዲኖረን እንድንፈልግ ያደርጋል።

ብዙውን ጊዜ እጅግ ብዙ ሕዝብ ያለበት ጉባዔ መጋቢ በመንግሥተ ሰማያት ታላቅ ይሆናል ብለን በማሰብ ራሳችንን እናስታለን። የሚሆነው ይህ ነው። በመንግሥተ ሰማያት ታላቅ የሚሆነው መጋቢ *ትሑት እና እንደ ልጅ የሆነ መጋቢ ነው።*

> በዚያች ሰዓት ደቀ መዛሙርቱ ወደ ኢየሱስ ቀርበው፡- **በመንግሥተ ሰማያት ከሁሉ የሚበልጥ ማን ይሆን?** አሉት። ሕፃንም ጠርቶ በመካከላቸው አቆመ እንዲህም አለ፡- እውነት እላችኋለሁ ካልተመለሳችሁ እንደ ሕፃናትም ካልሆናችሁ፣ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከቶ አትገቡም። እንግዲህ እንደዚህ ሕፃን ራሱን የሚያዋርድ ሁሉ፥ **በመንግሥተ ሰማያት** የሚበልጥ እርሱ ነው።
>
> ማቴዎስ 18፡1-4

ኢየሱስ በመንግሥተ ሰማያት ማን ታላቅ የሚሆን እንደሆነ በጣም ግልጽ አድርጎታል። ማንም ሰው ትሁት መሆንህን በጉባዔህ መጠን ሊገልጽ አይችልም። *እንዲያውም፣ ትልቅ ጉባዔ ካላቸው መጋቢዎች ይልቅ ትንሽ ጉባዔ ያላቸው መጋቢዎች ይበልጥ ትሑት መሆን*



*አዝማሚያ ይታይባቸዋል (ስለዚህ በመንግሥተ ሰማያት ታላቅ ይሆናሉ)።*

የሚያስፈልገን ለጌታችን ብዙ ጉባዔ፣ ብዙ ቤተ ክርስቲያን እና ብዙ ፍሬ ማፍራት ነው። "ቤተ ክርስቲያናትን እንትከል! "ቤተ ክርስቲያን በሁሉም ደጅ እና በሁሉም ቋንቋ" የሁሉም እውነተኛ የእግዚአብሔር ባሪያ ግብ ሊሆን ይገባል። በየኤሌክትሪክ ፖል እና ዛፍ ሥር መሰባሰብ የእግዚአብሔርን መንግሥት ወደ ፊት እንዲጓዝ ያደርጋል።

የሰዎችን ትኩረት መሳብ እናቁም። አገልግሎቶቻችንን በጉባዔአችን መጠን መገምገም እናቁም። ስብስቦች ይኑሩን። ውድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች፣ ከሰዎች ክብርን አንፈልግ፤ ይልቁን የእግዚአብሔርን ክብር (ማረጋገጫ፣ አድናቆት) እንሻ።

> እናንተ እርስ በርሳችሁ ክብር(ማረጋገጫ፣ አድናቆት) የምትቀባበሉ ከአንዱም ከእግዚአብሔር ያለውን ክብር(ማረጋገጫ፣ አድናቆት) የማትፈልጉ፥ እንዴት ልታምኑ ትችላላችሁ?
>
> ዮሐንስ 5፡44

## ወንጌልን መስበክ ታላቁን ተልእኮ መፈጸም ነውን?

የወንጌል ጀማ ስብከት እና ክሩሴድ ጥሩ ነገር ናቸው፤ ምክንያቱም የእነዚህ ትምህርቶች መነሻ ነጥብ ናቸውና። የወንጌል ስርጭት ወደ ፊት መራመድ አለበት። ግን በእርግጥ ታላቁን ተልእኮ ይፈጽማሉ? አዎም አይደለምም! **አዎ**፣ ምክንያቱም ሂደቱን ጀምረኸልና **አይደለም**፣ ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያን መመሥረት ማስተማር ካልተጨመረበት፣ ታላቁ ተልእኮ በእውነት ሊፈጸም አይችልምና።

በቀላሉ ለማስቀመጥ፣ **ታላቁ ተልእኮ ቤተ ክርስቲያን መትከልን የሚያስከትል የወንጌል ስርጭት ነው።** ቤተ ክርስቲያናት የሰዎች ስብስቦች ናቸው እና እነኚህ ስብስቦች ደግሞ የእግዚአብሔርን ቃል ይማራሉ።

## በወንጌል ባልተደረሱ ስፍራዎች ቤተ ክርስቲያናትን ትከል

ከሁሉ በላይ፣ ጌታ በሚመራን ስፍራዎች ቤተ ክርስቲያናትን መትከል አለብን። ቤተ ክርስቲያናትን በከተሞችና በገጠሮች መተከል አለባቸው።

ወንጌል ባልደረሰባቸው ስፍራዎች ቤተ ክርስቲያናትን መትከል እንደሚያስፈልግ ይታየኛል። ብዙዎቻችን ሁኔታዎች በጥሩ ሁኔታ በመሥራት ላይ በሚገኙባቸው ስፍራዎች እናተኩራለን። ግን እነግርሃለሁ፣ እግዚአብሔር ወደ ብዙ ያልተነኩ ቦታዎች ጠርቶናል። ነፍሳትን የመማረክ እና ቤተ ክርስቲያን የመትከል ቅንዓት እና መሰጠት ወደ ቤተ ክርስቲያን መመለስ አለበት፤ ስለዚህም ደግሞ ወጣት ልጆቻችንን መሥዋዕት ማድረግ አለብን።

መጋቢዎች፣ የእስልምና አብዛኛውን የአፍሪካ እና የዓለምን ክፍል መቆጣጠር ሊያሳስበን ይገባል፤ ቤተ ክርስቲያን ግን ግድ ያልሰጣት ትመስላለች። ሙስሊሞች መሥዋዕትነት መክፈልና በብዙ አገሮች ውስጥ ወዳሉ ከተሞችና ገጠሮች ዳርቻ መሄድ አያሳስባቸውም።

በዚህ ሁኔታ ውስጥ ግን፣ እስከ ዓለም ዳርቻ እንዲሄዱ የታዘዙ ክርስቲያኖች፣ ቅርብ እና በጣም ምቹ በሆኑ የዓለማችን ከተሞች ተቀምጠዋል!

ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፤ በኢየሩሳሌምም፣ በይሁዳም ሁሉ ከሰማሪያም እስከ **ቅርቦቹ፣ በጣም ምቹ ወደ ሆኑት እና ወደ በለጸጉት የዓለም ክፍሎች በመሄድ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ!** (ይህ የትኛው መጽሐፍ ቅዱስ ነው?)

> *ከዚህም ሁሉ በላይ፣ ልጄ ሆይ፣ ተግሣጽን ስማ ብዙ መጻሕፍትን መጻፍ ፍጻሜ የለውም።*



*ምዕራፍ 2*

# የቤተ ክርስቲያን ተካዮች አስተሳሰብ

. . . ይህ አሳብ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን።

ፊልጵስዩስ 2፡5

ክርስቶስ ያደረጋቸውን ነገሮች እንዲያደርግ ያደረገው አስተሳሰብ ነበረው። ይህ ጥቅስ ልክ ክርስቶስ ያስብ እንደነበረው እንድናስብ ያስተምረናል። "ይህ አሳብ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን" ማለት ይህ ነው።

የእግዚአብሔርን ፈቃድ መፈፀም የምትችለው አእምሮህ በሆነ ዓይነት መንገድ ሲሠራ (ሲያስብ) ብቻ ነው ።

እየጻፍሁ ያለሁት ቤተ ክርስቲያን የምትተክል ከሆነ አእምሮህ እንዴት መሥራት እንዳለበት ነው። ያለዚህ መሠረት፣ በጣም አስቸጋሪ ወደ ሆነው ቤተ ክርስቲያን የመትከል ሥራ ለመግባት ማንም ሰው አይችልም።

የሚቀጥሉት ምዕራፎች መሠረታዊ የሆኑ ቤተ ክርስቲያናት የመትከል አስተምህሮዎች ያስተምሩሃል። ታድጋለህ አገልግሎትም ወደ መጨረሻው ታላቁ ሐዋርያዊ ቤተ ክርስቲያን የመትከል እንቅስቃሴ ውስጥ ለመግባት ይነሣሣል።

## 1. እግዚአብሔር ሥራህን እየተቆጣጠረ እንደሆን እወቅ

ውድ ወዳጅ፣ በምድር ላይ የምትሠራውን ተመልካች አለ። እግዚአብሔር በውስጥህ ያስቀመጠውን ይፈልግብሃል። በሰጠህ ስጦታ ምን እንደሠራህበት ይጠይቅሃል። እግዚአብሔር የሰጠህን ነገሮች ይጠይቅሃል። እግዚአብሔር *ሥራዎችህን* ይጠይቃል!

ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት በተጻፈው ደብዳቤዎች ውስጥ አንድ የሚገርም ነገር አለ፤ ይህም *"ሥራህን አውቀዋለሁ"* የሚለው ሐረግ *መደጋገሙ* ነው። እነኚህ *ሥራዎች* የትኞቹ ናቸው? ምንም ይሁኑ ምን፣ እነኚህን *ሥራዎች* ሙሉ በሙሉ ስፍራ ማስያዝ ለእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን እጅግ አስፈላጊ ነው።
የሚከተሉትን ጥቅሶች ልብ በል፦

> **ሥራህንና** ድካምህን ትዕግሥትህንም **አውቃለሁ፤** ክፉዎችንም ልትታገሥ እንዳትችል፣ እንዲሁም ሳይሆኑ፦ ሐዋርያት ነን የሚሉትን መርምረህ ሐሰተኞች ሆነው እንዳገኘሃቸው አውቃለሁ።
>
> ራእይ 2:2

> *ሥራህንና* መከራህን፣ ድህነትህን አውቃለሁ፤ ነገር ግን ባለ ጠጋ ነህ፤ የሰይጣንም ማኅበር ናቸው እንጂ አይሁድ ሳይሆኑ፦ አይሁድ ነን የሚሉት የሚሳደቡትን ስድብ አውቃለሁ።
>
> ራእይ 2:9

> **ሥራህንና** የሰይጣን ዙፋን ባለበት የምትኖርበትን **አውቃለሁ፤** ስሜን ትጠብቃለ፣ ሰይጣንም በሚኖርበት በእናንተ ዘንድ የተገደለው የታመነው ምስክሬ አንቲጳስ በነበረበት ዘመን እንኳ ሃይማኖቴን አልካድህም።
>
> ራእይ 2:13

> **ሥራህንና** ፍቅርህን እምነትህንም አገልግሎትህንም ትዕግሥትህንም ከፊተኛውም *ሥራህ* ይልቅ የኋለኛው እንዲበዛ **አውቃለሁ።**
>
> ራእይ 2:19



> በሰርዴስም ወዳለው ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስትና ሰባቱ ከዋክብት ያሉት እንዲህ ይላል፦ **ሥራህን አውቃለሁ** ሕያው እንደመሆንህ ስም አለህ ሞተህማል።
>
> ራእይ 3:1

> **ሥራህን አውቃለሁ** እነሆ፣ በአንተ ፊት የተከፈተ በር ሰጥቼአለሁ ማንም ሊዘጋው አይችልም፤ ኃይልህ ምንም ትንሽ ቢሆን ቃሌን ጠብቀሃል፣ ስሜንም አልካድህምና።
>
> ራእይ3:8

እግዚአብሔር፣ "ቤቶችህንና መኪኖችህን አውቃለሁ"፤ አላለም። "መርቼዲስ ቤንዝህን አውቃለሁ"፤ አላለም፤ እርሱ ያለው *"ሥራዎችህን አውቃለሁ!"* ነው። "ዲግሪህን አውቃለሁ" አላለም፣ "እናትና አባትህን" አውቃለሁ አላለም፣ *"ሥራዎችህን አውቃለሁ"* ነው ያለው!

## 2፡ ቤተ ክርስቲያን መትከል ከእግዚአብሔር ጋር ለመዝለቅ ቁልፍ ነው

> ነፍሱን ሊያድን የሚወድ ሁሉ ያጠፋታልና፣ ስለ እኔና ስለ ወንጌል ነፍሱን የሚያጠፋ ሁሉ ግን ያድናታል።
>
> ማርቆስ 8:35

በ1985 እ.ኤ.አ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ለዘለቄታው ለመጓዝ እርምጃ ወሰድሁ። በዚያን ወቅት አስቸጋሪ የሆነ የሕክምና ትምህርት ቤት ፈተና ልክ መጨረሴ ነበር። በእኔ ግምት ፈተናውን እንደነገሩ ነበር የሠራሁት። ለዚያ ፈተና ያደረግሁትን ጥረት ሳስብ፣ የለፋሁትን ልፋት ሳስብ፣ በልቤ የተሰማኝ በፍጹም የማይገባው እንደሆነ ተረዳሁ። ለምንድር ነው ለሕክምና ይህን ያህል የምሠቃየው? ስለ ምን ሕይወቴን እንደዚህ ላለው ነገር እሰጣለሁ?

ከዚህ በኋላ ቅድሚያ የምሰጠው ለእግዚአብሔር *ሥራ* እንደሆነ ማልሁ። በመጀመሪያ እግዚአብሔር በሕይወቴ ውስጥ ተቀዳሚ እንደሆነ አስብ ነበር። በጣም ቀራጥ ክርስቲያን መሪ ነበርሁ ግን የእግዚአብሔርን

ሥራ በሕይወቴ ውስጥ ቅድሚያ እንዳልሰጠሁት ተረዳሁ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ፣ አንድ አላማ ብቻ እንዳለኝ ወሰንሁ፣ ያም የእግዚአብሔርን ሥራ መሥራት! ሌሎች ነገሮች ሁሉ ተቀፅላ ሆኑ። ይህ በእውነት የሕይወቴ ለውጥ መነሻ ነጥብ ነበር።

ከዚያ በኂላ፣ አንደኛው የሕይወቴ ግብ እግዚአብሔርና አገልግሎት ሆነ። የሕክምና ትምህርት ቤት ሁለተኛ ወይም ሦስተኛነትን አልነፈግሁትም። ምናልባት ያንን ወቅት ወደ ሙሉ ጊዜ አገልግሎት እንደገባሁበት አድርጌ መውሰድ እችላለሁ።

የሚገርመው ነገር ያንን ውሳኔ ከወሰንሁ በኋላ፣ የሕክምና ትምህርቴ ልቁ መውጣት ጀመርሁ። ከፍተኛ ማዕረግ በማግኘት ሽልማት አሸነፍሁ! ይድነቅህ ብሎ፣ ከክፍሌ አንደኛ ሆንሁ። ልቤ ከማንኛውም ዓይነት የሕክምና ሙያ እጅግ ርቆ ነበር፣ ቢሆንም ግን በሕክምና ትምህርት ከፍተኛ ማዕረግ እያገኘሁ ነበር። የተውከውን ነገር እርሱን ራሱን መልሶ እግዚአብሔር ሲሰጥህ የሚደነቅ ነገር አይደለም?

ከእግዚአብሔር ጋር ለመጓዝ እምነት ይጠይቃል። ይሆንብኛል ብዬ የገመትሁት ነገር ተቃራኒው ሆነ። ከእግዚአብሔር ጋር መጓዝ የሚመስለው ይህን ነው። ነፍሱን የሚያጠፋ ያገኛታል! ነፍሱን የሚጠብቅ ያጣታል። እምነት የማያስፈልግህ ጊዜ የለም። ሁልጊዜ ልናምን ይገባናል።

ከዚያን ጊዜ አንሥቶ እስካሁን፣ ሙሉ በሙሉ በአገልግሎት ውስጥ እገኛለሁ። ከዚያም ትንሽ ቆየት ብሎ፣ የመጀመሪያዋን እና እስካሁንም መጋቢያዋ የሆንኹትን ቤተ ክርስቲያን ተከልኩ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ከአራት መቶ በላይ የሆኑ ቤተ ክርስቲያኖች በመትከል ላይ ተሳትፌአለሁ። አንድ ጊዜ በጋና ውስጥ ብቻ ቢያንስ አንድ ሺ ቤተ ክርስቲያናትን ለመትከል ቃልኪዳን ገባሁ። እግዚአብሔር ይህን ቃልኪዳን የምፈጽምበት ጸጋ እንዲሰጠኝ እየጸለይሁ ነው። መንገዴን



ተያይዤዋለሁ! ከዚህ በኂላ ወደ ኂላ አልልም። የእርሱ ፈቃድ በሕይወቴ ይፈጸም!

በ1989 እ.ኤ.አ፣ ብቁ የሕክምና ዶክተር ሆንኹ። በ1990 እ.ኤ.አ የአንድ ዓመት አገልግሎቴን ጨረስኹ። የሕክምና ት/ቤት ጓደኞቼ ሁሉ ወደ ውጭ አገሮች መሄድ ጀመሩ። እግዚአብሔር በጋና ውስጥ እንድቆይ እንደጠየቀኝ ለኔ በጣም ግልጽ ነበር። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበሩት ሰዎች በጣም ጥቂት ነበሩ፤ ግን ከእነርሱ ጋር ለመቆየት ወሰንሁ። የድህነትን ኑሮ ለመኖር በራሴ ላይ ፈረድኩ። ለባለቤቴ ይህን ሃሳቤን ነገርኋት እርሷም ተስማማች። በመንገዴም ሁሉ እረዳችኝ። መቼም ቢሆን ቤት እና የመሳሰሉት ነገሮች እንደማይኖረኝ አወቅሁ። ብቻ አወቅሁት። ቢሆንም ግን፣ *"ጌታ ሆይ በሙሉ ልቤ እወድሃለሁ፣ አደርገዋለሁ። ራሴን ለአንተ አሳልፌ እሰጥሃለሁ።"* አልሁ።

ብዙ ዓመታት አለፉ ግን ከሁሉ የተሻለ ሆነ። እንዲህ አለ፣ "ጽድቅና *መንግሥቱን ፈልጉ ሌላው ሁሉ ይጨመርላችኋል።"*

> **ነፍሱን ሊያድን የሚወድ ሁሉ ያጠፋታልና፤ ስለ እኔ ነፍሱን የሚያጠፋ ሁሉ ግን እርሱ ያድናታል።**
>
> **ሉቃስ 9፡24**

## 3. በምድር ላይ እስካለህ ድረስ ልትፈጽማቸው የሚገቡ ሥራዎች አሉ

> **ፀጋው በእምነት አድኖአችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም። እኛ ፍጥረቱ ነንና፤ እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን።**
>
> **ኤፌሶን 2፡ 8-10**

እግዚአብሔር መልካም ሥራ ሰጥቶሃል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ በሕይወት ያለኸው ለዚያ ነው፡፡ አትሳሳት፣ በሕይወት ያለህበት ብቸኛ ምክንያት፣ የሆነ መልካም ሥራን ልትፈጽም ነው፡፡

በአንድ ወቅት አንድ እንግሊዛዊ ባለ ታክሲ በታክሲው ይዞኝ ሲሄድ በእግዚአብሔር እንደሚያምን ጠየቅሁት፡፡ እርሱም በእግዚአብሔር እንደማያምንና እኔም በእንደዚህ ዓይነት ነገር የማምን ከሆነ እንደሚገርመው ነገረኝ፡፡

በእግዚአብሔር እንደማምን ነገርኩት ፦ ከዚያም በመንግሥተ ሰማያት እና በሲኦል እንደማምን ጠየቀኝ፡፡ እኔም፦ "በእርግጥ አምናለሁ" ብዬ ነገርኩት፡፡

እንደገናም እንዲህ ሲል ጠየቀኝ፣ "መንግሥተ ሰማያት ጥሩ ቦታ ነው ብለህ ታምናለህ?" እኔም፣ "መንግሥተ ሰማያት ድንቅ ቦታና ሁላችንም አንድ ቀን ለመሄድ የምንጠባበቀው ቦታ ነው" ብዬ መለስኩለት፡፡

እርሱም በመቀጠል፣ "በመንግሥተ ሰማያት ያለው ሕይወት በምድር ላይ ካለው ሕይወት የሚሻል ይመስልሃል?" ብሎ ጠየቀኝ፡፡
"እርግጠኛ ነኝ ይሻላል" ፣ ብዬ መለስኩ፡፡

ከዚያም በሕይወት ዘመኔ ፈጽሞ የማልረሳው አንድ ጥያቄ ጠየቀኝ "በእርግጥ መንግሥተ ሰማይ ከምድር የሚሻል ከሆነ፣ ለምን አሁኑኑ ራሳችሁን ገድላችሁ ወደ መንግሥተ ሰማይ አትሄዱም?" ብሎ ጠየቀኝ፡፡

መልሱን ከመመለሴ በፊት፣ የምወርድበት ቦታ ደረስኩና ወረድሁ፡፡ እየሄድኩ ሳለሁ፣ ይህ ሰው የጠየቀኝን ጥያቄ ማውጣና ማውረድ ጀመርሁ፡፡ አባባሉ እውነት ይመስላል፡፡ እንዲህ ያለ ታላቅ ቦታ ከሆነ ለምን ወደ መንግሥተ ሰማያት አንሄድም?



ግን የእግዚአብሔር ቃል ለምን በዚህ ምድር ላይ መቆየት እንዳለብን ያሳየናል እዚህ ያለነው መልካም ሥራዎችን ለመሥራት ነው፡፡ በዚህ ምድር ላይ መልካም ሥራዎችን ልናደርግ ተሹመናል! በምድር ላይ ያለውን ሥራችንን ሳንፈጽም መሄድ አንችልም፡፡

አንድ ቀን ኬነት ሄገን የሥጋ ሞት አጋጠማቸው፡፡ መንፈሳቸው ከሥጋቸው ተነጥሎ ሲወጣ፣ እንዲህ የሚል ድምፅ ሰሙ፣ "ተመለስ፣ ተመለስ፣ በምድር ላይ ያለህን ሥራ አልጨረስኽም"፡፡ መንፈሳቸው ተመልሶ ወደ ሥጋቸው ገባና ከዚያ በኋላ ለብዙ ዓመታት ኖሩ፣ እግዚአብሔር እንዲሠሩ የጠራቸውን መልካሙን ሥራ ፈጸሙ፡፡

ሌላው ራሳችንን የማንገድልበት ምክንያት ራስን ማጥፋት ወንጀል ነው፡፡ ሕግን መተላለፍ እና በእግዚአብሔር ፈቃድ ላይ ማመፅ ነው፡፡

## 4. ጥበብ ሰማያዊ ነገርን ማሰብ እና ወደ ዘላለማዊ ሕይወት መቅረብን ማስተዋል ነው

በአንድ ወቅት፣ ከመጋቢዎቼ አንዱ ሊሰናበተኝ ወደ ቢሮዬ መጣ፡፡ እንድጸልይለት ፈለገ፡፡ ወደ ውጭ አገር የሚሄደውም በወንጌል መልእክተኛነት(ሚስዮናዊነት) ነበር፡፡ ከአጠገቤ ቁጭ እንዳለ፡፡ የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ላይ መጣና በቅባት ተናገርኩት፡፡ "ጥበበኛ ሰው እንድትሆን እንደሚሞት ሰው አስብ፡፡ በቅርቡ መንግሥተ ሰማያት መድረስህን አስብና ጥበበኛ ትሆናለ፡፡" አየህ፣ ሰዎች በአልጋ ላይ ሞታቸውን ሲጠባበቁ፣ የመንግሥተ ሰማያት እና የሲኦልን እውነትነት ከማያስቡ ሰዎች በተለየ ሁኔታ ያስባሉ፡፡

ለባለቤቴ የነገርኳትን አስታውሳለሁ፡፡ እንዲህ ስል ጠየቅኋት፣ "መንግሥተ ሰማያት ስደርስ እግዚአብሔር ምን የሚለኝ ይመስልሻል?" ምን ብላ እንደ መለሰችልኝ አላስታውስም ግን ሁሌ የሚያሳስበኝ ነገር ይህ ነው፡፡ ሰማያት በእኔ ደስ ይላቸዋል? እግዚአብሔር በእኔ ደስ

ተሰኝቷል? አንድ ቀን ጌታ ኢየሱስን ፊት ለፊት ሳየው ምን ይለኝ ይሆን?"

የሚያሳዝነው ግን ብዙዎቻችን የምናስበው ስለ ምድራዊ ነገሮች ብቻ ነው:: ገንዘብ፣ መኪና፣ ቪዛ፣ ሥልጣን፣ ተሰሚነት፣ እና ከሰዎች ክብርን ማግኘት:: እንደነኚህ ያሉ አስተሳሰቦች ጥበብ አይደሉም:: የእግዚአብሔርን ሥራ ሳትሠራ ብትሞት፣ ሞትህ የሰነፍ ይሆናል::

አትሳት፤ በምድር ላይ ያለህ ጊዜ ውስን ነው:: ከዛሬ በኋላ፣ ያለህ ዕድል በአንድ ቀን ይቀንሳል:: የምትገነባቸው ቤቶች እና የምታካብታቸው ቅሪቶች እውነተኛ ዋጋ የላቸውም:: ኢየሱስ፣ **"በምድር ላይ እታከማቹ"**፣ አለ:: ለምን እንዲህ አለ? ኢየሱስ ጥሩ ነገሮችን ማግኘታችንን ይቃወማል? በእርግጥ አይደለም! የላቀ ጥበብ እየሰጠን እንጂ - ዘላለማዊነትን እና ትንሣኤን እያሰብን እንድንኖር እንጂ:: ዘላለማዊነትን ባሰብን መጠን ይበልጥ ጠቢብ እንሆናለን!

እስቲ አሁን ጥቂት ስሌት ሥራ፣ ይህን መጽሐፍ ካነበብህ በኂላ ምን ያህል ዓመት በምድር ላይ ትኖራለህ:: ይህን በዘላለማዊ ሕይወት ከምትኖረው እጅግ ብዙ ዓመታት ጋር አመዛዝነው::

በአንድ ወቅት አባቴ እንዲህ አለኝ፣ የዕድሜህን የመጀመሪያ ሃያ አምስት ዓመታት የምታሳልፍበት ሁኔታ የሚቀጥሉትን የዕድሜህ አርባ አምስት ዓመታት ይወስናል:: በሃያ አምስት ዓመቴ የሕክምና ዶክተርና መጋቢ ነበርኩ:: የመጀመሪያዎቹ የዕድሜዬ ሃያ አምስት ዓመታት በእርግጥ በቀጣይነት የኖርኩባቸው ዘመናት ላይ ተፅዕኖ አሳድረዋል::

ይሁንና እኔ ደግሞ ከዚህ የላቀ ጥበብ ልስጥህ፡ "በምድር ላይ የምትኖራቸው ሰባ ዓመታት በዘላለማዊ ሕይወት የምትኖራቸውን በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዓመታት ይወስናሉ" እደዚያ፣ ሕይወት ምድራዊ ሕይወት ብቻ ነው ብሎ እንዳሰበው ጎልማሳ ባለ ጠጋ አትሁን::



እግዚአብሔር፣ "አንተ ሰነፍ፣ ዛሬ ነፍስህን እፈልጋለሁ" ሲለው እርሱ የተለያዩ ነገሮችን በማቀድ ላይ ነበር:: በዚያኑ ምሽት እንደ እርሱ ምድራዊ ዕቅድ ሳይሆን ጌታ ጠራው:: እግዚአብሔር አንተን የሚጠራበት ቀን አለው:: ከሥራዎችህ ጋር ተዘጋጅ:: ሥራህን አውቃለሁ!

## 5. በኅብረተሰቡ ውስጥ መልካም ሰው ከመሆን በላይ ለሆነ ነገር ተጠርተሃል

የተፈጠርነው 'መልካም' ሰው እንድንሆን ብቻ አይደለም:: መልካም ሥራዎችን ለመሥራት ተፈጥረናል:: እነኚህ መልካም ሥራዎች ደግሞ በእግዚአብሔር የተወሰኑ እንጂ በአንተ የተወሰኑ አይደሉም:: በሌላ አነጋገር፣ ልትሠራ የተገቡህን ሥራዎች እግዚአብሔር አስቀድሞ ወስኗል:: ማንም እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት አንዳች ሊያደርግ አይችልም፣ ያንተ ግብረገብነት፣ ያንተ ትክክለኛነት እና ያንተ ፍጹምነት እግዚአብሔርን ደስ ሊያሰኝ አይችልም:: እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት አድርግ ያለህን ማድረግ ነው::

ክፉና ደጉን ከምታሳውቀው ዛፍ ከበሉ በኋላ፣ ሰዎች "መልካም ወይም ክፉ" ብለው በሚያስቡት ነገር ይጨነቃሉ:: ለእኛ ትክክለኛው ነገር እግዚአብሔርን መታዘዝ ነው:: መልካም ነገሮችን ማድረግ፣ ግብረገብነት እና ትክክለኛ ነገሮችን ማድረግ ማለት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት ላይሆን ይችላል::

ሰይጣን በምድረ በዳ ወደ ጌታ ኢየሱስ ሲቀርብ፣ ኢየሱስን "መልካም ነገሮችን" እንዲያደርግ ሃሳብ አቀረበለት:: ኢየሱስ የተጠየቀው የእግዚአብሔርን ኃይል በመጠቀም ድንጋዩን ወደ ዳቦ እንዲቀይር ነበር፤ ግን አላደረገውም::

የእግዚአብሔርን ኃይል በመጠቀም ራሱን እንዲያድንም ተጠይቆ ነበር ግን አላደረገውም። ትክክለኛ ነገር ማድረግ ማለት እግዚአብሔርን መታዘዝ እንደሆን ያውቅ ነበር። ሰይጣን ሰዎችን "ትክክለኛ ነገር" እንዲያደርጉ ይጠይቃል፤ ነገር ግን ሁል ጊዜ ከበስተጀርባው ሌላ አጀንዳ አለው። ምንም እንኳ "መልካም ነገሮችን ብታደርግም ልክ ከእግዚአብሔር ትእዛዝ ስትወጣ ኃጢአት ውስጥ ገብተሃል።

## አኖሚያ

የኃጢአትን ፍች እንድትረዳ ላግዝህ። ኃጢአት ማለት የግድ ክፉ የሆነን ነገር ማድረግ ብቻ ላይሆን ይችላል። የሚገርምህ ነገር ግን የእግዚአብሔር ፈቃድ ያልሆነውን፣ መልካም ነገር ማድረግ ኃጢአት ነው። ቀደም ሲል እንዳልኩት፣ በቀላሉ ኢየሱስ ያላደረጋቸው ብዙ መልካም ነገሮች ነበሩ።

ኢየሱስ ረጅም ዕድሜ ሊኖር ይችል ነበር፤ ግን በሠላሳ ሦስት ዓመቱ በመስቀል ላይ በመሞት የአባቱን ፈቃድ ፈጸመ። ሰማኒያ ዓመት እስኪሞላው በመላው ዓለም እየዞረ ወንጌልን ቢሰብክ መልካም አልነበርምን? ኢየሱስ ያልፈወሳቸው ብዙ በሽተኞች ነበሩ። ኢየሱስ ለምን አልፈወሳቸውም? የታመመውን መፈወስ መልካም ነገር አልነበረም?

እዚህ ላይ፣ የኃጢአትን ዋነኛ ፍች ልንረዳ ይገባናል። ኃጢአት የእግዚአብሔርን ፈቃድ አለመቀበል ነው። **ኃጢአት የእግዚአብሔርን ዕቅድና ፈቃድ ስመቀበል እንቢ ማለት ነው። የእግዚአብሔርን ዕቅድ በራስ ዕቅድ መቀየር ነው።** የእግዚብሔርን ጥበብ በራስህ ጥበብ መተካት ነው!

"አኖሚያ" ማለት ይህ ነው። "አኖሚያ" የግሪክ ቃል ነው። "አኖሚያ"፣ ሕግን መተው ማለት ነው፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድና መንገድ መተው



ማለት ነው። አብዛኛውን ጊዜ ከእግዚአብሔር የተሻለ እንደምናውቅ ማሰባችን እንዴት ያሳዝናል።

*ኃጢአትን የሚያደርግ ሁሉ ዓመፅን ደግሞ ያደርጋል፣ ኃጢአትም አመፅ ነው*

1ኛ ዮሐንስ 3፡4

ከዚህ ጥቅስ፣ ሕግን መተላለፍ ኃጢአት እንደሆን እናያለን። "መተላለፍ" የሚለው ቃል "አኖሚያ" ከሚለው የግሪክ ቃል የተተረጎመ ነው። ይህ ማለት "ሕግን ተጻራሪ የሚያደርግ"ማለት ነው። የቫይን መዝገበ ቃላት ይህ ጥቅስ የኃጢአትን ትክክለኛ ትርጉም እንደሚያሳይ ይናገራል። ቫይን መዝገበ ቃላት በመቀጠል፤ "ይህ የኃጢአት ፍች የኃጢአት ዋነኛ ባሕሪ ሕግን አለመቀበል እንደሆነ ያስቀምጣል፤ ወይም የእግዚአብሔርን ፈቃድ አለመቀበል እና የራስን ፍቃድ መተካት" እንደሆነ ያሳያል።

ከዓመታት በፊት፣ እርሱን ለማገልገል ያለኝ ዕቅድ ለእግዚአብሔር እንደነገርሁት አስታውሳለሁ። ወደ ሥራ ዓለም በመግባት ለእግዚአብሔር ሥራ ብዙ ገንዘብ ለማምጣት ወሰንኩ። ከፍተኛ ገቢ ያለው ሰው በመሆን ለሥራው በሺዎች የሚቆጠር ገንዘብ እንደማዋጣ ለእግዚአብሔር ነገርሁት።

እንደዚህ ያለ ሐሳብ ያለው ሰው እኔ ብቻ አይደለሁም። እንደዚህ ያለ ተመሳሳይ ሐሳብ እንዳላቸው የገለጹልኝ ብዙ ሰዎች አግኝቼአለሁ። የሚገርመው ነገር ግን፣ እጅግ በጣም ጥቂቶች ናቸው፣ ለእግዚአብሔር መንግሥት ብዙ ገንዘብ የሚያመጡ፣ እርሱም ከተገኙ ነው። እኔ የሙሉ ጊዜ መጋቢ ነኝ ስለዚህ ሰዎች የሚያደርጉትን አውቃለሁ። እኔ የማውቃቸው ብዙዎቹ ሀብታሞች ለእግዚአብሔር መንግሥት የሚያደርጉት አስተዋጽዎ እምብዛም አይደለም። እንዲያውም፣ ጥቂት የወርቅ ሳንቲሞቻቸውን እንዲያመጡ መጎትጎት አለብህ።

እውነቱን ልንገርህ? እንደሚመስለኝ፣ በዚያ መንገድ ብሄድ ኖሮ (በእግዚአብሔር መንገድ ሳይሆን በራሴ መንገድ ብሄድ ኖሮ) ለእግዚአብሔር መንግሥት የምሰጠው በጣም ጥቂት ገንዘብ ይሆን ነበር። ሳስበው ምናልባት መጋቢዎችን እና ቤተ ክርስቲያናትን በገንዘብ አጠቃቀማቸው እተቻቸው ነበር። ምሕረት ጌታ ሆይ!

አየህ፣ እግዚአብሔር እኛ ከምናውቀው በላይ ያውቃል እናም እግዚአብሔር ወደ ሙሉ ጊዜ አገልግሎት ጠራኝ፤ እርሱ የሚሠራውን ያውቃል። እ.ኤ.አ በ1990 ጌታ የማደርጋቸውን ነገሮች ሁሉ አቁሜ የሙሉ ጊዜ አገልግሎት ሠራተኛ እንድሆን እንደጠራኝ በደንብ አስታውሳለሁ። የእኔ መንገድ ቢሆን ግን እግዚአብሔርን ዝም ለማሰኘት የተወሰነ ገንዘብ በሰጠሁት ነበር። ይቅር ይበለኝ!

ስለ ወደፊት አገልግሎቴ አላውቅም ነበር። አገልግሎትን በመተው የተጠራሁበትንና ያዘጋጀልኝን ሽልማት ባጣሁ ነበር።

## የአውራ ጣት ዋጋ

አንድ ጊዜ ፋብሪካ ውስጥ ሲሠራ አደጋ ደርሶበት አውራ ጣቱ የተቆረጠ ሰው አገኘሁ። ለጓደኞቹ ሲያሳያቸው በመደነቅ እመለከተው ነበር። የደረሰበትንና ለአውራ ጣቱ የተከፈለውን ድጎማ ነገረን።

በተዘበራረቀ ስሜት ለአውራ ጣቱ ስምንት ሺህ የእንግሊዝ ስተርሊንግ ፓውንድ እንደ ተከፈለው ነገረን። በዚያን ጊዜ፣ በባንክ ሂሳቤ ውስጥ ያለኝ አንድ ፓውንድ ብቻ ስለ ነበር ለራሴ "እንዴት የታደለ ሰው ነው አልሁኝ።"

ከዓመታት በኋላ፣ ጌታ ይህን ሰው አስታውሶኝ እና ጥቂት ስሌቶችን እንድሰሥራ ጠየቀኝ፡-

"ይህ ሰው ለአንድ አውራ ጣቱ ብቻ ስምንት ሺህ ፓውንድ ከተከፈለው፣ ሁለት አውራ ጣቶች ስንት ያወጣሉ"?

እኔም "አሥራ ስድስት ሺህ ፓውንድ።" አልኩ



ከዚያም እንዲህ ብሎ ጠየቀኝ፣ "አምስት ጣቶችስ ስንት ያወጣሉ?"

"ጌታ ሆይ አርባ ሺህ ፓውንድ" አልሁ።

በመቀጠልም፣ "አስር ጣቶች ስንት ያወጣሉ አለኝ?"

"ሰማኒያ ሺህ ፓውንድ" ብዬ መለስሁ

ከዚያም ጌታ እንዲህ ብሎ ጠየቀኝ፣ "አንድ ክንድ ስንት ያወጣል?"

"እጅግ ብዙ ገንዘብ" ፣ ብዬ መለስኩሁ

"አንድ እግር፣ አንድ ኩላሊት፣ አንድ ልብ እና አንጎልስ?"

"እርግጠኛ አይደለሁም።"

በመጨረሻም እንዲህ ብሎ ጠየቀኝ፣ "ሙሉ አካልህ ስንት ያወጣል?"

"በሚሊዮኖች የሚቆጠር" አልሁ።

የፈለገውን ያህል ገንዘብ ለእግዚአብሔር መንግሥት ባዋጣ፣ ሙሉ አካሌን፣ መንፈሴንና ነፍሴን ለአገልግሎት ከመስጠት ጋር እንደማይወዳደር አሳየኝ። በእኔ ትንሿ መረዳት፣ ብዙ ገንዘብ መስጠት ራስን የመስጠት ያህል እንደሆነ አስቤ ነበር።

## 6. መዳንህ ለመልካም ሥራዎች ነው

ብዙውን ጊዜ ስለ ብልጽግና እንሰብካለን፣ እንዴት ስኬታማ መሆን እንደሚቻል እናስተምራለን። ይሁን እንጂ፣ መዳናችን ለአንድ ዓላማ ነበር ነውም። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል "ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ እንጂ ከእናንተ አይደለም (ኤፌሶን 2:8)። እኛ (ክርስቲያኖች) ፍጥረቱ ነንና፤ እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን። (ኤፌሶን 8:10)።

ለዚህ ነው እስካሁን በሕይወት ያለነው። ልንሠራቸው የሚገቡን መልካም ሥራዎች አሉልን! ከእነኚህ መልካም ሥራዎች ውስጥ አንዱ ቤተ ክርስቲያናትን መትከል ነው። ወንጌልን ለመስበክ ወደ ገጠርና

ከተማዎች ልንሄድ ይገባናል። እግዚአብሔር መልዕክቱን ይዘው የሚሄድ ሰዎችን ይፈልጋል። እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ተካዮችን እየፈለገ ነው። እነኚህ መልካም ሥራዎች እግዚአብሔር በእርሱ ለሰጠን አዲስ ሕይወት ምክንያቶች ናቸው። ለእርሱ እንድንኖርና ዓላማውን እንድንፈጽም ነው። ሥራዎችህ ለእግዚአብሔር በጣም አስፈላጊ ናቸው። ይህ የመዳናችን ዋነኛ ምክንያት ነው። "**ሥራህን አውቃለሁ!**"

## 7. ሥራውን መሥራት የግል ችግሮችህን እንድታሸንፍ ይረዳሃል

ሰዎች ሲሰብኩና ሲያስተምሩ ችግሮች የሉባቸውም ማለት አይደለም። የእግዚአብሔርን ቃል ስናገለግል፣ እነኚህ ችግሮች እያነሱ ይሄዳሉ። በችግሮቻችን ላይ ከምናተኩር ዓይኖቻችንን ወደ መኸሩ ጌታ ልናነሳና በፊታችን ያለውን ልናይ ይገባናል። እንዘርጋና በዘመናችን በቤተ ክርስቲያን ያልተደረሱትን ሰዎች እንድረስ።

እግዚአብሔር ፍጹምና ምንም ችግር የሌለባቸውን ሰዎች ተጠቅሞ አያውቅም። ኖሃ የመስከር ችግር ነበረበት ግን እግዚአብሔር ተጠቀመበት። አብርሃም ከባድ የትዳር ችግር ነበረበት፣ እግዚአብሔር ግን ተጠቀመበት። ረዓብ፣ ጋለሞታዋ የሥነ ምግባር ችግር ነበረባት ግን እግዚአብሔር ተጠቀመባት። እግዚአብሔር ተጠቀመብህ ማለት የግል ችግሮች የሉብህም ማለት አይደለም!

"ይህ መዝገብ በምድራዊ ሸክላ ዕቃ ውስጥ አለን" (2ኛ ቆሮንቶስ 4:7)። የእግዚአብሔር ክብርና ቅባት በሰማያዊ ወይም በመላዕእክት ዕቃዎች ውስጥ አይደለም፣ በምድራዊ ዕቃዎች ውስጥ እንጂ። እኔ ሁል ጊዜ የማገለግለው የግል ችግሮች ሳይኖሩብኝ ቀርቶ አይደለም። የገንዘብ ችግር የነበረብኝ ጊዜዎች ነበሩ፣ ግን የእግዚአብሔርን ሥራ ሰሠርቼአለሁ። የትዳር ችግሮች የነበሩብኝ ጊዜ ነበር፣ ግን አሁንም



የእግዚአብሔርን ሥራ ሠርቼአለሁ። የታመምኩበት ጊዜ ነበር፣ በቀዶ ጥገና ሐኪሞች ቀዶ ጥገና ተደርጎልኛል፣ ግን አሁንም የእግዚአብሔርን ሥራ ሠርቼአለሁ።

ሰዎች ይመለከቱኝና ምንም ዓይነት ችግር ገጥሞኝ እንደማያውቅ ይገምታሉ። እንዲያውም፣ ምናልባት ከአንድ መካከለኛ ሰው የበለጡ ችግሮች አሉብኝ። ግን እግዚአብሔርን እንደሌሉ እንዲመስሉ ያደርጋቸዋል።

> ነገር ግን የኃይሉ ታላቅነት ከእግዚአብሔር እንጂ ከእኛ እንዳይሆን **ይህ መዝገብ በሸክላ ዕቃ ውስጥ አለን።**
>
> 2ኛ ቆሮንቶስ 4:7

ማንኛውም እግዚአብሔር የሚጠቀምበት ምድራዊ ሸክላ ከግል ችግሮቹ ጋር ተጣብቋል። እነኚህ ችግሮች እንዳሉ ሆነው እንጂ ፍጹም ሕይወት ስላለው አይደለም። የምሥራቹ አንተ በእግዚአብሔር ሥራ ላይ ስታተኩር፣ የግል ችግሮችህ ከስመው የእግዚአብሔር ክብር ታላቅነት መገለጡ ነው።

## 8. የአንዲት ቤተ ክርስቲያን ብርታት የሚለካው የወንጌል መልእክተኞችን በመላክ አቅሟ ነው።

በዘልማድ የቤተ ክርስቲያን አቅም የሚለካው በሚይዘው የሰው መቀመጫ ብዛት ነው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ ሰው በተቀመጠ መጠን፣ ታላቅ ይመስላል። ይሁን እንጂ፣ ቤተ ክርስቲያን የተፈጠረችው የወንጌል መልእክተኞችን ለመላክ ነው። ቤተ ክርስቲያንህ ሰዎችን ትልካለች? መጋቢዎች ወደ ቤተ ክርስቲያናቸው የመጡ ሰዎችን በመጥቀስ በኩራት መናገር ይወዳሉ። የሰው ስም በመጥቀስ፣ "የፀሐይ ሚኒስትር፣ የጨረቃና የኮከቦች ሚኒስትር በመጀመሪያው ፈረቃ አገልግሎቴ ላይ ተገኙ" ይላሉ።

"የፋይናንስ ሙስና ምክትል ሚኒስትር የፋይናንስ ኮሚቴ አባል ናቸው" አልፎ አልፎ ብቻ ነው መጋቢዎች ሰዎችን በወንጌል መልእክተኝነት (ሚስዮናዊነት) መላካቸውን የሚናገሩት፡፡ የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን እንዴት እንደምትሠራ አስተውል፡፡

> በአንጾኪያም ባለችው ቤተ ክርስቲያን ነቢያትና መምህራን ነበሩ፤ እነርሱም በርናባስ፤ ኔጌር የተባለው ስምዖንም፤ የቀሬናው ሉክዮስም፤ የአራተኛው ክፍል ገዥ የሄሮድስም ባለምዋል ምናሔ፤ ሳውልም ነበሩ፡፡ እነዚህም ጌታን ሲያመልኩና ሲጦሙ መንፈስ ቅዱስ፡- **በርባናስንና ሳውልን ለጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ** አለ፡፡ እነርሱም በመንፈስ ቅዱስ ተልከው ወደ ሴሌውቅያ ወረዱ ከዚያም በመርከብ ወደ ቆጵሮስ ሄዱ፡፡
>
> የሐዋርያት ሥራ 13፡1፤2፤4

## 9. *ሥራውን መሥራት የሕይወትን ከንቱነት እንድታሸንፍ ያደርግሃል*

> ከፀሐይም በታች የተሠራው ሥራ ሁሉ ከብዶብኛልና ሕይወትን ጠላሁ፤ ሁሉም ከንቱ ነፋስንም እንደ መከተል ነው፡፡ ከእኔ በኋላ ለሚመጣው ሰው እተወዋለሁና ከፀሐይ በታች የደከምሁበትን ሁሉ ጠላሁት፡፡ ጠቢብ ወይም ሰነፍ እንዲሆን የሚያውቅ ሰው ማን ነው? ከፀሐይ በታች በደከምሁበትና ጠቢብ በሆንሁበት በድካሜ ሁሉ ላይ ጌታ ይሆንበታል፤ ይህም ደግሞ ከንቱ ነው፡፡ እኔም ተመልሼ ልቤን ከፀሐይ በታች በደከምሁበት ድካም ሁሉ ተስፋ አስቆረጥሁት፡፡
>
> መክብብ 2 17-20

ሰለሞን በተደጋጋሚ ከሚጠቀምባቸው ቃላቶች ውስጥ አንደኛው ***ከንቱ*** የሚለውን ቃል ነው፡፡ ሰለሞን ሁሉንም ነገር ካገኘ በኂላ ***ሁሉም ነገር ከንቱ*** እንደሆነ ተረዳ፡፡ እግዚአብሔር ሌሎች ብዙ ሰዎች የሚያልሟቸውን ግን ሊያገኟቸው የማይችሉትን ብዙ ነገሮች ሰጠው፡፡ ሰለሞን ግን እያንዳንዱ ነገር ዋጋ እንደሌለውና ከንቱ እንደሆነ ተረዳ፡፡ **"ከንቱ ከንቱ የከንቱ ከንቱ ነው"** አለ፡፡



ሁሉም ነገር ከንቱ ነው፡፡ በሰለሞን አውደ ንባብ ውስጥ "***ከፀሐይ በታች***" ሁሉም ነገር ከንቱ ነው፡፡ "***ከፀሐይ በታች***" የሚለው ሐረግ በመክብብ መጽሐፍ ውስጥ በተደጋጋሚ ተገልጿል፡፡ ከፀሐይ በታች የሚገልፀው ከፀሐይ በታች ያሉትን ምድራዊ ፍጥረታት በሙሉ ነው፡፡

ያለን ምድራዊ ነገር ሁሉ ከንቱ ነው፡፡ እውነታው ያ ነው፡፡ መጋቢዎች እውነትን ሊያስተምሩና ሊሰብኩ ይገባቸዋል፡፡ የትኩረት አቅጣጫችን መንግሥተ ሰማያት እና የፍርድ ቀናችን መሆን አለበት፡፡ ቤተ ክርስቲያን ተካይ በዚህ ጥበብ የሚመላለስ ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን መትከል ከንቱ አይደለም፤ ምክንያቱም ዘላለማዊ ሽልማት ያስገኝልናል፡፡

## 10. *ሥራዎችህ ወደ መንግሥተ ሰማያት ይከተሉሃል፡፡*

ስትሞት፣ ምንም ነገር ተከትሎህ አይሄድም፡፡ ብዙ የቀብር ሥነ ሥርዓቶችን አካሂጃለሁ፡፡ በዚህ ምድር ላይ ተዋቂና ተወዳጅ በነበሩ ብዙ ሰዎች ሬሳ ሳጥን አጠገብ ቆሜአለሁ፡፡ የሰዎችን ግብዓተ መሬት ፈፅሜአለሁ፡፡ ይህን በተደጋጋሚ አይቼአለሁ፡፡ ማንም ሰው ከዚህ ምድር ምንም ነገር ይዞ አልሄደም፡፡ መኪናዎች ይቀራሉ፣ ቤቶች ይቀራሉ፣ ገንዘብም ይቀራል፡፡

> ከሰማይም፡- ከእንግዲህ ወዲህ በጌታ የሚሞቱ ሙታን ብፁዓን ናቸው፡፡ መንፈስ፡- አዎን፤ ከድካማቸው ያርፉ ዘንድ፤ **ሥራቸውም ይከተሳቸዋል** ይላል ብለህ ጻፍ የሚል ድምፅ ከሰማይ ሰማሁ፡፡
>
> ራእይ 14፡13

ይህን ዓለም ለቀህ ስትሄድ *ከሥራዎችህ* በቀር አንዳች ነገር አይከተልህም፡፡ በእግዚአብሔር ሥራ ላይ ልትሳተፍ ይገባሃል፡፡ በሕይወት ዘመንህ ቤተ ክርስቲያን ልትተክል ይገባሃል፡፡ በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ተሳታፊ መሆን አለብህ፡፡

እግዚአብሔር በሥራው ላይ ተካፋይ እንድትሆን እድል ይሰጥሃል እንጂ ለእግዚአብሔር አታስፈልገውም፡፡ እኔም አላስፈልገውም፡፡ መጋቢዎችም

አያስፈልጉትም። መጋቢዎች በጣም አስፈላጊ ቢሆኑ ኖሮ፣ አይሞቱም ነበር። ማንም ሰው ለእግዚአብሔር ብቁና ወሳኝ አይደለም። የእግዚአብሔር ምሕረት የሥራው ተካፋዮች እንድንሆን አድርጎናል። የእኛ ሥራው ውስጥ መጨመር እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ምሕረት ያሳያል!

## 11. ቤተ ክርስቲያን በመትከል ከተቺነት ትድናለህ

ከተመልካችነት መሳተፍ ይሻላል። አብዛኛውን ጊዜ ተመልካቾች ሁሉን ነገር ይተቻሉ። ለተወሰነ ጊዜ ያለ ሥራ ከተቀመጥህ፣ የቤተ ክርስቲያንህን ጥፋቶች ሁሉ ማየት ትጀምራለህ። መጋቢህ ሲሰብክ ጥፋቶቹን ትመለከታለህ። ጥቅሶችን ሲጠቅስ ስሕተቱን ትመለከታለህ። ቅባቱ ከወትሮ መቀነሱን ትመለከታለህ። ብዙም ሳትቆይ፣ የቤተ ክርስቲያንህን ጉድለቶች በሙሉ ጠንቅቀህ ታውቃለህ። ቀስ በቀስም ወደ ተቺነትና ስሕተቶችን ፈላጊ ወደ መሆን ውስጥ ትወድቃለህ። በሰማይ አጋንንቶች ያገኙሀል።

## 12. ቤተ ክርስቲያን ትከል ምክንያቱም እግዚአብሔር አስተማሪ እንድትሆን ይጠብቅብሃል።

የእግዚአብሔርን ቃል የምታስተምር ልትሆን የሚገባበት ጊዜ ይመጣል። ሰዎችን ልታስተምር ይገባል፣ የምትሰጠው ነገር ሊኖርህ ይገባል።

> **በዚህ ጊዜ አስተማሪዎች ልትሆኑ ሲገባችሁ፣ ገና የእግዚአብሔርን ቃል** የመጀመሪያ ትምህርት የሚያስተምራችሁ ሰው ያስፈልጋችኋል፤ የሚያስፈልጋችሁም ጠንካራ ምግብ ሳይሆን ወተት ነው።
>
> ዕብራውያን 5፡12

አስተማሪ ልትሆን የሚገባበት ጊዜ ይመጣል። አስተማሪ ልትሆን በሚገባበት ጊዜ ሳትሆን ብትቀር፣ በመንፈሳዊ ዕድገትህ ውስጥ የሆነ ችግር አለ ማለት ነው።



አንድ ቀን ለስብከት ስንወጣ በቡድናችን ውስጥ የነበረችን አንዲት እኅት በንጋት አደባባይ ስብከታችን ላይ እንድተሰብክ ጠየቅኋት እርሷም "እንዴት መስበክ እንደሚገባኝ አላውቅም። ከዚህ በፊት ሰብኬ አላውቅም፣ መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ አላውቅም" አለችኝ።

ከዚያም እንዲህ አልኳት፣ "መስበክ ትችያለሽ"። እኔ ያልኋትን ሁሉ እንድትደግመው ነገርኋት። ብዙም ሳይቆይ፣ መስበክ ጀመረች። በዚያ ማለዳ ሙሉውን ስብከት ሰበከች። ዛሬም ድረስ ጌታን በማገልገል ላይ ትገኛለች። ሙከራ ብታደርግ ብቻ ልታደርግ የምትችለውን ብታይ ትደነቃለህ።

*ከዚህም ሁሉ በላይ፣ ልጄ ሆይ፣ ተግሣጽን ስማ ብዙ መጻሕፍትን መጻፍ ፍጻሜ የለውም።*

*ምዕራፍ 3*

# የቤተ ክርስቲያን ተካዮች ሥራ

. . . ይህ አሳብ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን።
በእምነት፣ በጸጋ ድናችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ በሥራ አይደለም፤ ምክንያቱም፣ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀልንን መልካም ሥራ እንድንሠራ በክርስቶስ ኢየሱስ የተፈጠን የእግዚአብሔር እጅ ሥራዎች ነን።

ኤፌሶን 2:8-10
(አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

መጽሐፍ ቅዱስ ሥራችን እንደማያድነን ግልጽ አድርጎ ተናግሯል። በመልካም ሥራዎቻችን ወደ መንግሥተ ሰማያት አንሄድም። ከሲኦልም የዳንነው በመልካም ሥራዎቻችን አይደለም። መዳናችን በጸጋው ነው። ደህንነታችን ከጌታ ነው። ደህንነትን ለማግኘት አንዳች ልታደርግ አትችልም። ለመንግሥተ ሰማያት የሚያበቃ መልካምነት የለህም! የእኛ ፍጽምና ብቁ አይደለም። ሥራዎቻችን ብቁ አላደረጉንም ለመንግስተ ሰማያት በፍጹም ብቁ አይደለም።

እንዲህ ተብሎ እንደተጻፈ፤ ጻድቅ ማንም የለም፤ አንድም እንኳ፤

ሮሜ 3:10
(አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

ሁላችን እንደ ረከሰ ሰው ሆንናል፤ የጽድቅ ሥራችን እንደ መርገም ጨርቅ ነው፤
ሁላችን እንደ ቅጠል ረግፈናል፤ ኃጢአታችንም እንደ ነፋስ ጠራርጎናል።

ኢሳይያስ 64:6
(አዲሱ መደበኛ ትርጉም)



አስተውል! በኤፌሶን መጽሐፍ ውስጥ "መዳን በሥራ እንዳልሆነ" ቢናገርም በዚህ አውደ ንባብ ውስጥ "ለመልካም ሥራ እንደ ተፈጠርን" ይናገራል። ይህ ማለት ደህንነትን ካገኘን በኋላ፣ ክርስቶስ ወደ አዘጋጀልን መልካም ሥራ ውስጥ እንገባለን ማለት ነው።

ብዙ ክርስቲያኖች በሥራ ሳይሆን በጸጋ እንደዳኑ ስለሚያውቁ ዘና ብለው ይቀመጣሉ። ወደ መንግሥተ ሰማያት መግባት ፍጻሜያቸው እንደሆነ ያስባሉ። ዘና ብለን ተቀምጠን ወደ መንግሥተ ሰማያት መጋለብ ነው ይላሉ። ወደ መንግሥተ ሰማያት ስለ መጋለባችን እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን። ስንደርስ ግን፣ ጥያቄዎችን እንጠይቃለን!

"አድርግ ያልሁህን ነገሮች አድርገሃል? ያዘጋጀሁልህን መልካም ሥራዎች አድርገሃል?" ኢየሱስ ይጠይቃል።

## ሁለቱ ፍርዶች

እግዚአብሔር እኛን የሚፈርደው ሌላውን ዓለም እንደሚፈርድ አይደለም። ለአማኞች ሌላ ፍርድ አዘጋጅቷል። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሁለት ዓይነት የፍርድ ዙፋኖች ይናገራል። ነጩ ዙፋን ዓለም የሚፈረድበት ነው። ክርስቲያኖች የክርስቶስ የፍርድ ወንበር በሚባል ሌላ ወንበር ይፈረዳሉ።

ነጩ ዙፋን የመንግሥተ ሰማያት ከፍተኛው ችሎት ነው። ይህ ወደ ሲኦል እንድትሄድ ወይም እንዳትሄድ የሚፈረድበት ሥፍራ ነው። አማኞች የሚፈረዱበት ግን ሌላ የፍርድ ወንበር አለ።

### 1. ነጩ ዙፋን

ከዚህ በኋላ ታላቅ ነጭ ዙፋንና በእርሱም ላይ የተቀመጠውን አየሁ። ምድርና ሰማይ ከፊቱ ሸሹ፤ ስፍራም አልተገኘላቸውም። ሙታንን፣ ታላላቆችንና

> ታናናሾችን በዙፋኑ ፊት ቆመው አየሁ፤ መጻሕፍትም ተከፈቱ። ሌላም መጽሐፍ፣ እርሱም የሕይወት መጽሐፍ ተከፈተ፤ ሙታንም በመጻሕፍቱ ተጽፎ በተገኘው መሠረት እንደ ሥራቸው መጠን ተፈረደባቸው። ባሕርም በውስጡ የነበሩትን ሙታን ሰጡ፤ እያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን ተፈረደበት።
>
> ራእይ 20፡11-13

## የሕይወት መጽሐፍ እና የሥራዎች መጽሐፍ

ስምህ ከሁሉ በላይ አስፈላጊ በሆነው በሕይወት መጽሐፍ ውስጥ መገኘቱ መሠረታዊ ጉዳይ ነው። ይህ ወደ መንግሥት ሰማያት መግባትህን ይወስናል።

ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ የሠራናቸው ሥራዎች ሁሉ የተመዘገቡባቸው መጽሐፍቶች እንዳሉ ያሳየናል። ይህ የሥራዎች መጽሐፍ ነው! ይህ መጽሐፍ ይገለጣል። ይህ የሥራዎቻችንን መዛግብት ይዟል። ተተክለው የነበሩ ቤተ ክርስቲያናትን ማኅደር ይዟል። ሙታን ከእነኚህ መጽሐፍት ውስጥ እንደ ሥራቸው መጠን ይፈረዳሉ።

### 2. የክርስቶስ የፍርድ ወንበር

> ስለዚህ በሥጋ ብንኖርም ወይም ከሥጋ ብንለይም አላማችን እርሱን ደስ ማሰኘት ነው። ሁላችንም በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት እንቀርባለንና፤ እያንዳንዱም ሰው በሥጋው ለሠራው በጎ ወይም ክፉ ሥራ ተገቢውን ዋጋ ይቀበላል።
>
> 2ኛ ቆሮንቶስ 5፡9-10
>
> (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

## የስንፍና ተራራ

አማኞች በሥጋቸው ለሠሩት ሥራ ፍርድን ይቀበላሉ። የኢየሱስን ሥራዎች ልንሠራ ይገባናል። ዋጋ የምንሰጣቸው ነገሮች ልክ በምንሞትበት ቅስበት ዋጋ ያጣሉ። የተሰበሰበና የተከማቸ ነገር ሁሉ የስንፍና ተራራ ይሆናል።



የተከማቸው ሀብታችን፣ ቤቶቻችን፣ ዲግሪዎቻችን፣ ልብሶቻችን እና ጫማዎቻችን ሁሉ እምነት የለሽ መሆናችንን ሊመሰክሩ ይቆማሉ። በፍጹም በትንሣኤ አናምንም! ከሙታን እንደምንነሳሣ እና እንደገና ዘላለማዊ ሕይወት እንደምንኖር በፍጹም አናምንም። በዚያን ቀን የተከማቹ ጠፊ ንብረቶቻችን ይመሰክሩብናል። እንዲህ ብለው በመናገር ለሰማያት ያውጃሉ፡- "እምነት የለሽ ነበር። አልታዘዘህም። አላመነም፣ ልቡ በምድራዊ ሀብት ላይ ነበር!"

## የፍሬዎች ቅርጫት

አንድ ቀን ድንገት ራስህን በመንግስሥተ ሰማያት ታገኘዋለህ። በዚያን ቀን፣ በእጅህ ምን ይኖር ይሆን? ለእግዚአብሔር ክብር የፍሬዎች ቅርጫት፣ ወይስ በአንተ ላይ የሚመሰክሩብህን የስንፍና ተራሮች? ውድ ወዳጄ ወደ ሰማያት የሚከተልህ አንድ ነገር ብቻ ነው፣ እርሱም መልካም ሥራዎችህ።

> ከሰማይም፡- ከእንግዲህ ወዲህ በጌታ የሚሞቱ ሙታን ብፁዓን ናቸው። መንፈስ፡- አዎን፤ ከድካማቸው ያርፉ ዘንድ፤ ሥራቸውም ይከተላቸዋል ይላል ብለህ ጻፍ የሚል ድምፅ ሰማሁ።
>
> ራእይ 14፡13

ከብዙ ዓመታት በፊት በ1982 እ.ኤ.አ፣ በሕክምና ትምህርት ቤት ውስጥ ነበርሁ። ለመጀመሪያ ጊዜ የሰውነት ክፍሎች ጥናት (አናቶሚ) ክፍል የገባሁበትን ቀን አስታውሳለሁ። ብዙ የሚጻፍ ነገር ነበር። ብዙ ማስታወሻዎችን ጻፍን። ፕሮፌሰሩ ትምህርታዊ መግለጫውን ሲቀጥል፣ ሁሉንም ነገር መጻፍ ይጠበቅብኝ ይሆን ብዬ ግራ ተጋባሁ። 'ይህ ሁሉ ነገር፡ አስፈላጊ ነው?'፣ ብዬ ራሴን ጠየቅሁ።

መምህሩ የሰውነት ክፍሎች ጥናት(አናቶሚ) መግቢያ ሰፊና ጥልቅ ዘገባውን ቀጠለ። እንደ፡- "ፕሮኔሽን፣ ሳፒኔሽን ኤክስተርናል ሮቴሽን፣

ኢንተርናሽናል ሮቴሽን፣" . . . ወዘተ፣ የመሳሰሉ የተለያዩ የአናቶሚ ቃላቶችን አስተማረን። የዚያን ቀን የያዝኩት ማስታወሻ ደብተሬን ሊሞላ ምንም አልቀረውም።

በትምህርቱ ክፍለ ጊዜ፣ ጓደኛዬን እንዲህ ብዬ ጠየቅሁ፣ "ካሎሪን፣ ትክክለኛው ቦታ ያለን ይመስልሻል?"
እርሷም፣ "አይመስለኝም"፣ ስትል መለሰችልኝ። ትምህርት ቤቱን ለቃ መሄድ እንዳለባት ስታስብ እንደነበር ነገረችኝ እኔም ይህንኑ ሳስብ ነበር። ይህን ዓይነቱን የሰባት ዓመት መከራ መገመት አልቻልንም። በምንም ዓይነት መንገድ ሰባት ዓመት ሊያልቅ አይችልም ብዬ አሰብኩ። ሰባት ዓመት መታገሥ አንችልም በጣም ይበዛል!

በኋላ ግን ዓመታት ቀስ በቀስ አልፈው ትምህርታችንን ጨረስን። ሰባት ዓመታት አያልቁም ብዬ አስቤ ነበር ግን ደረሱ አለፉም። አሁን ወደ ሕክምና ትምህርት ቤት ከገባሁበት ጊዜ ጀምሮ ሃያ ሁለት ዓመት ሆኗል። ያንን ጥያቄ ከጠቅሁ ሃያ ሁለት ዓመት ሆኗል።

ለማሳየት እየሞከርኩ ያለሁት ሩቅ የሚመስለውን፣ ግን ድንገት ቶሎ የሚደርስብንን፣ የዘላለም ሕይወትን ነው። ሰባት ዓመት በፍጹም አይደርስም ብዬ አስቤ ነበር። አንዳንዶቻችን ዘላለማዊው ሕይወት በፍጹም እንደማይደርስ እናስባለን። በሙታን ትንሣኤ ከሞት ስለመነሣት አናምንም። በሁለተኛው የሕይወታችን ምዕራፍ አናምንም። በምድር ላይ የሚኖረን ጊዜ አጭር ነው ደግሞም በጣም በቅርቡ ሁላችንም በመንግሥተ ሰማያት እንሆናለን። ለምን በምድር ላይ ለዘላለም እንኖራለን ብለን አስብን በማለት እንገረማለን!

*ከዚህም ሁሉ በላይ፣ ልጄ ሆይ፣ ተግሣጽን ስማ ብዙ መጻሕፍትን መጻፍ ፍጻሜ የለውም።*



*ምዕራፍ 4*

# ቤተ ክርስቲያን መትከል እና የኢየሩሳሌሟ ቤተ ክርስቲያን

በአዲስ ኪዳን ውስጥ በጥንቃቄ መታየት እና ዋጋ ሊሰጣቸው የሚገቡ ሁለት ቤተ ክርስቲያናት ነበሩ። የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን እና የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን።

## ስለ ኢየሩሳሌሟ ቤተ ክርስቲያን ሁሉም ሰው ሊያውቅ የሚገባው ዐሥር ነገሮች

1. የኢየሩሳሌሟ ቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን ነበረች።
2. ዋነኞቹ ሰዎች መሠረታቸውን በኢየሩሳሌሟ ቤተ ክርስቲያን አድርገው ነበር። ሐዋርያት እንኳ ዋናው መቀመጫቸው ይህች ቤተ ክርስቲያን ነበረች።
3. ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ የሚለውን የመጀመሪያ የኢየሱስን ትእዛዝ የተቀበለች ቤተ ክርስቲያን ነበረች።
4. በጣም የበለጸገችና ያበበች ቤተ ክርስቲያን ነበረች

**ከመካከላቸውም አንድ ችግረኛ አልነበረም፤ ምክንያቱም መሬትም ሆነ ቤት የነበራቸውን ሁሉ እየሸጡ ዋጋውን አምጥተው፣ በሐዋርያት እግር ሥር በማስቀመጥ ለእያንዳንዱ በሚያስፈልገው መጠን ያካፍሉት ነበር።**

የሐዋርያት ሥራ 4፡34-35
(አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

5. በቤተ ክርስቲያን ታላቅ እድገት ነበር

ቃሉን የተቀበሉትም ተጠመቁ፤ በዚያም ቀን ሦስት ሺህ የሚያህሉ ሰዎች ነፍስ ተጨመሩ፤

የሐዋርያት ሥራ 2፡41

6. በቤተ ክርስቲያን ታላቅ አንድነት ነበር

ያመኑት ሁሉ በአንድነት ነበሩ፤ ያላቸውንም ሁሉ የጋራ አደረጉ።

የሐዋርያት ሥራ 2፡44
(አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

7. እግዚአብሔር በገጠማቸው ችግርና አዳጋች ነገር ሁሉ ላይ ድል ሰጣቸው።

ለምሳሌ ያህል፣ ጴጥሮስና ዮሐንስ ከሊቀ ካህኑ እና ከሽማግሌዎች ማረፊያ ቤት ተለቀቁ። መለኮታዊ በሆነ የመላእክት ጣልቃ-ገብነት ከእስር ቤት አመለጡ።

ከዚህም የተነሣ ሊቀ ካህናቱና አብረውት የነበሩት የሰዱቃውያን ወገን ሁሉ በቅናት ተሞሉ፤ ሐዋርያትንም ይዘው ማረፊያ ቤት ከተቷቸው። ይሁን እንጂ የጌታ መልአክ በሌሊት የእስር ቤቱን ደጆች ከፍቶ አወጣቸውና፣...

የሐዋርያት ሥራ 5፡17-19
(አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

8. የእግዚአብሔር ኃይል በታላቅ ሁኔታ በቤተ ክርስቲያን ተገልጦ ነበር። በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ ለመጋቢው የዋሹ ሰዎች ወዲያው ሞቱ፡

ጴጥሮስም፦ ሐናንያ ሆይ፤ መንፈስ ቅዱስን ታታልልና ከመሬቱ ሽያጭ ታስቀር ዘንድ ሰይጣን በልብህ ስለ ምን ሞላ? ... ሐናንያም ይህን ቃል ሰምቶ ወደቀ ሞተም በሰሙትም ሁሉ ላይ ታላቅ ፍርሃት ሆነ።

የሐዋርያት ሥራ 5፡3፣5



9. ዛሬ እንዳሉ ብዙ ቤተ ክርስቲያናት ሳይሆን፣ ለድሆች ግድ ይላቸው ነበር

...ለእያንዳንዱ በሚያስፈልገው መጠን ያካፍሉት ነበር።

የሐዋርያት ሥራ 4፡35
(አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

10. ነገር ግን መቅሰፍት እስኪበተንባቸው ድረስ የተሰጣቸውን ቤተ ክርስቲያን የመትከል መመሪያ አልታዘዙም

በዚያን ቀንም በኢየሩሳሌም ባለች ቤተ ክርስቲያን ላይ ታላቅ ስደት ሆነ ሁሉም ከሐዋርያትም በቀር ወደ ይሁዳና ወደ ሰማሪያ አገሮች ተበተኑ።

የሐዋርያት ሥራ 8፡1

ምናልባት መልካም ገጽታዎቻቸው ሁሉ ታዛዥ ያልሆኑ ቤተ ክርስቲያንነታቸውን ሸፍኖት ሊሆን ይችላል። አንድ በጣም ተስፋ የሚጣልበት ወጣት መጋቢ፣ ምናልባት ጴጥሮስን ይተካል ተብሎ ይገመት ነበር፣ ድንገት ሞተ፣ የዚያን ጊዜ ነቁ።

ይህ ለኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን እንዴት ያለ ፍንዳታ ይሆን! ይህ እስኪሆን ድረስ ሁሉ ነገር በትክክል እየሄደ ነበር። እስከዚያን ጊዜ ድረስ የተፈጠረ ችግር ሁሉ ለበጎ ሆኖ ነበር። ይህኛው ችግር እስኪመጣ ድረስ የመጣን ችግር እንደምንም በእግዚአብሔር ኃይል ማሸነፍ ተችሎ ነበር። ድንገት የሞተ መጋቢ እጃቸው ላይ ነበር።

እስጢፋኖስም፦ ጌታ ኢየሱስ ሆይ፣ ነፍሴን ተቀበል ብሎ ሲጠራ ይወግሩት ነበር።

የሐዋርያት ሥራ 7፡59

ይህ ለኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ሕይወት የለውጥ መነሻ ነጥብ ሆነ። ቤተ ክርስቲያን በዚህ ነውጥ ውስጥ እያለች፣ ዓለም ስደትን አስነሳባት።

በዚያን ቀን በኢየሩሳሌም በነበረችው ቤተ ክርስቲያን ላይ ታላቅ ስደት ተነሣ፣ ...

የሐዋርያት ሥራ 8፡1
(አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

በመጨረሻ ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔርን እንድትታዘዝ ያደረጋት ስደት ነበር። በሰላምና አንጻራዊ በሆነ ስኬት በቀላሉ መታለል ይቻላል። “ለነገሩማ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፣” ‘ሰላምና ደኅንነት ነው ሲሉ፣ ያን ጊዜ ምጥ እርጉዝን እንደ ሚይዛት ጥፋት በድንገት ይመጣባቸዋል ከቶም አያመልጡም።’ (1ኛ ተሰሎንቄ 5:3)።

በሁኔታዎችና አንጻራዊ በሆነ ብልጽግና ልንመራ አይገባንም። እነኚህ የእግዚአብሔርን በረከቶች አያመላክቱም። ሰላምና ብልጽግና የእግዚአብሔር በረከት ምልክቶች ቢሆኑ ኖሮ ሐዋርያው ጳውሎስ ታላቅ ኃጢአተኛ በሆነ ነበር ምክንያቱም ብዙ ተሠቃይቷል።

በአገልግሎቱ ውስጥ ምን ያህል ችግሮች እንደነበሩበት ልብ በል።

> የክርስቶስ አገልጋዮች ናቸውን? እንደ እብድ ሰው ልናገርና እኔ እበልጣቸዋለሁ፤ ደግሞ ብዙ ጊዜ በሥራ ደክሚአለሁ፣ ብዙ ጊዜ ታስሬለሁ፣ ብዙ ጊዜ ተገርፌአለሁ፤ ብዙ ጊዜ ለሞት ተቃርቤአለሁ። አይሁድ ለአርባ ጅራፍ አንድ የቀረው አምስት ጊዜ ገርፈውኛል። ሦስት ጊዜ በዱላ ተደብድቤአለሁ፤ አንድ ጊዜ በድንጋይ ተወግሬአለሁ፤ ሦስት ጊዜ የመርከብ አደጋ ደርሶብኛል፤ አንድ ሌሊትና ቀን በባሕር ላይ አድሬአለሁ፤ ብዙ ጊዜ በጉዞ ተንከራትቻለሁ፤ ደግሞም ለወንዝ ሙላት አደጋ፣ ለአሕዛብ አደጋ፣ ለከተማ አደጋ፣ ለገጠር አደጋ፣ ለባሕር አደጋ እንዲሁም ለሐሰተኞች ወንድሞች አደጋ ተጋልጬ ነበር። ብዙ ጥሬአለሁ፤ ብዙ ደክሚአለሁ፤ ብዙ ጊዜ እንቅልፍ አጥቻለሁ፤ ተርቤአለሁ፤ ተጠምቻለሁ፤ ብዙ ጊዜ ምግብ ሳልቀምስ ኖሬአለሁ፤ በብርድና በራቁትነት ተቆራምጃለሁ።
>
> 2ኛ ቆሮንቶስ 11:23-27
>
> (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

የጳውሎስን የሕይወት ፍልስፍና ልብ በል። ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የምንገባው በመከራ ውስጥ ብቻ ነው።

> **. . . ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት በብዙ መከራ ማለፍ አለብን. . .**
>
> የሐዋርያት ሥራ 14:22
>
> (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)



## ሦስት የቀብር ሥነ ስርዓቶች

ከዓመታት በፊት፣ በአገልግሎቴ ውስጥ አስደንጋጭ ነገር ገጠመኝ። በአንድ ዓመት ውስጥ፣ ሦስት መጋቢዎቼ ለማመን በሚያስቸግር ሁኔታ ሞቱብኝ። የመጀመሪያው አርብ ቀን ኦክቶበር 2000 እ.ኤ.አ ምሽት ላይ ሞተ። ባለቤቱ ደውላ እንደታመመ እና ክሊኒክ ውስጥ እንዳለ ነገረችን። በአንድ ሰዓት ውስጥ ከአንድ ዶክተር መጋቢዬ በሞባይል ስልኬ ላይ ሌላ ጥሪ ደረሰኝ።
“ቢሾፕ፣ መጋቢ ቻርልስ ሞቷል።” አለችኝ እኔም፣ “የምታወሪው ይገባሻል?” አልኳት ይህን የስልክ ጥሪ ስቀበል የት እንደነበርሁ በትክክል አስታውሳለሁ። ጆሮዎቼን ማመን ተሣነኝ። ፍጹም ደኅና ሰው ነበር። ከአንድ ቀን በፊት እንኳ እኔ ቤት ምሣ በልቷል።

በቀጥታ ወደ ክሊኒኩ አመራሁ እዚያም ስደርስ ለሰባት ወር በትዳር አብራው የቆየችውን ሚስቱን በእንባ ተሞልታ በኮሪደሩ ላይ አገኘኋት። በጣም ተደናግጣ ምን እንደሆነ እንኳ አታውቅም ነበር። ወደ ክፍሉ ስገባ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ፣ በአገልግሎቴ ውስጥ ልጆቼ ከሆኑት ውስጥ አንደኛውና ተስፋ የሚጣልበት የ27 ዓመት ወጣት፣ በአልጋ ላይ ሞቶ አየሁ።

ያ በሕይወቴ ውስጥ በጣም አሳዛኝና የሐዘን ምሽት ነበር። ሚስቱ በባሏ አስክሬን ላይ እንባዋን ስታፈስ ሳይ፣ ይህ የደረሰብን ምን አድርገን ይሆን? ብዬ ግራ ተጋባሁ። በቀብሩ ሥነ ስርዓት ላይ፣ ራሳችንን በጌታ አበርትተን ባለቤቱን ለማጽናናት ሞከርን። በዓመት ውስጥ መጋቢዎችን ወደ መቅበር እና መበለቶቻቸውን ወደ ማጽናናት እመለሳለሁ ብዬ አልገመትሁም ነበር።

ከሁለት ሳምንት በኋላ፣ ከመጋቢዎቼ ውስጥ አንዱ በጠና እንደታመመ የሚገልጽ ሌላ የስልክ ጥሪ ደረሰኝ። በመጀመሪያ፣ የታከመው በግል ሆስፒታል ውስጥ ነበር፤ በኋላ ግን ወደ ትልቅ ሆስፒታል ከፍተኛ ክትትል የሚደረግበት ክፍል አስገባነው። ሕይወቱን ለማትረፍ ያደረግነው ትንቅንቅ እና ከቦታ ወደ ቦታ ያደረግነውን ሩጫ አስታውሳለሁ፣ ብዙ ዶክተሮች እንዲያዩት ለማድረግ ሞከርን።

ሕይወቱን ለማትረፍ የደም ናሙናዎች ይዤ ተሯሯጥሁ። ያ ሁሉ ምንም አልፈየደም። በጥቂት ቀናት ውስጥ፣ ራሱን ሳተ፤ እናም ቆየት ብሎ ከሆስፒታል ሌላው መጋቢ ቻርልስ እንደሞተ ተረዳሁ። ልቤ ወደቀና ተስፋ መቁረጥ ገባብኝ። ወደ ቤቴ ስሄድ ኃይሌ ሁሉ ተሟጦ ነበር። ሌላ ተስፋ የሚጣልበት መጋቢ መበለቱንና ሕፃናት ልጆቹን ትቶ ሞተ።

በዚህ በቃ ብዬ አስቤ ነበር፣ ግን ጥቂት ወራት በኋላ፣ ደቡብ አፍሪካ ውስጥ በማገልገል ላይ እያለሁ፣ የስልክ ጥሪ መጣልኝ። ዋነኛና ተቀዳሚ ረዳቶቼ ከሆኑት መጋቢዎች አንደኛው ከጋና ሲደውልልኝ ፕሪቶሪያ ውስጥ ወዳረፍኩበት ሆቴል ክፍሌ በቀጥታ ገባሁ። "መጋቢ ፊሊስቸር ሞቷል" አለኝ። "ምን . . . እንዴት . . . መቼ . . .?"፤ ብዬ ተንተባተብሁ። በዚህን ጊዜ፣ የሆነ ችግር እንዳለ ተረዳሁ። አየህ፣ እኛ ልክ እንደ ኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ነን ማለት ይቻላል። ብዙዎቹ የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ባሕርያት በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ሊገኝ ይችላል። ተባርከናል፣ እያደግን ነው፣ እየበለጸግን ነው፣ ኃይለኞች ነን፣ 'አስሄድነው' እንደሚሉት ነው። ይህ ክስተት ነበር በመጨረሻ እግዚአብሔር በሕይወቴ ውስጥ ያለውን ቤተ ክርስቲያን የመትከል ትኩረቴን የሳበው።

በተሳሳተ መንገድ አትረዳኝ። እግዚአብሔር ከዚያ ቀደም ብሎም ከሁለት መቶ በላይ ቤተ ክርስቲያናት ለመመሥረት ተጠቅሞብኛል። ቤተ



ክርስቲያን በመትከል ላይ ነበርን ግን በደረስንበት ደረጃ ዘና ብዬ ነበር። ወደ አዲስ ግዛቶች መግባት ያስፈራኝ ነበር። ሰዎችን ወደ የትኛውም ቦታ ለመላክ እምብዛም ፍቃደኛ አልነበርሁም። ተቀይሬ ነበር፣ ወደ ኋላ በማፈግፈግ ላይ ነበርሁ፣ ግን አይታወቀኝም ነበር።

አንዱን ሰው፣ "ሂድ ስለው የሚሄድ"፣ ለማድረግ የምፈራ ጄኔራል ነበርኩ። እነኚህን የበለጸጉ መጋቢዎችና ሠራተኞችን ወደ ቤተ ክርስቲያን በጣም ወደ ሚያስፈልጋቸው አካባቢዎች ለመላክ አልቻልሁም ነበር። አሁን ትኩረቱ ሌላ ነበር። የ"ኢየሩሳሌም ብልጽግና" ወደ አዕምሮዬና ወደ ልቤ ገብቶ ነበር። በእነኚህ አንዳንድ ከተሞችና ገጠሮች ሰዎች ምን ዓይነት ሕይወት እንደሚኖራቸው አስብ ነበር። ልጆቻቸው የት ትምህርት ቤት ይገባሉ? እነኚህ ወጣት ሰዎች ቤት ለመሥራትና መኪና ለመግዛት በቂ ገንዘብ ይኖራቸዋል?

ጌታ እንዲህ ብሎ ጠየቀኝ፣ እነኚህ አንተ ወደ አገልግሎት ስትገባ ግምት ውስጥ ያስገባሃቸው ነገሮች ናቸው? ጌታ አሁንም እንዲህ ብሎ ጠየቀኝ እነኚህን የግለሰቦች ደኅንነቶችንና ምቾቶችን ግምት ውስጥ ብናስገባ ኖሮ ቤተ ክርስቲያናችን ዛሬ የደረሰችበት ትደርስ ነበር? በልቤ ወደ ኋላ እንዳፈገፈግሁ ተረዳሁ።

ብዙ ሰዎች የወንጌል መልእክተኛ በመሆን መላክ ከባድ እንደሆነ ያስባሉ። ግን ሰዎችን ወደ ጉስቁልናና ሞት ሊያመጣ ወደሚችል ቦታ የሚልክ ሰው መሆን የባሰ ይፈታተናል። ግን ቤተ ክርስቲያን መትከልን በተመለከተ ሁሉንም ለመላክና እንደገና ወደ ኋላ ላለማለት ቆረጥሁ።

የእግዚአብሔር መንፈስ፣ 'ላክ፣ ላክ፣ ላክ፣' ሲል ይሰማኛል። አንድ ጊዜ ጌታ ገሠፀኝ። ብዙ ሰው ታሠለጥናለህ ግን ብዙ ሰው አትልክም አለኝ። ሥልጠናዬን ከአላላኬ ጋር እንዳመጣጥን ተናገረኝ።

የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ወደ ኋላ ቤተ ክርስቲያን ወደ መትከል አገልግሎት መጣች ግን ከትልቅ ችግር በኋላ ነበር።

> ሳውልም በእስጢፋኖስ መገደል ተስማምቶ ነበር። በዚያ ቀን በኢየሩሳሌም በነበረችው ቤተ ክርስቲያን ላይ ታላቅ ስደት ተነሣ፤ ከሐዋርያትም በስተቀር አማኞች በሙሉ በይሁዳና በሰማርያ አውራጃዎች ሁሉ ተበተኑ፤ የተበተኑትም በሄዱበት ሁሉ ቃሉን ሰበኩ፤
>
> የሐዋርያት ሥራ 8፡1፣4
> (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

*ከዚህም ሁሉ በላይ፣ ልጄ ሆይ፣ ተግሣጽን ስማ ብዙ መጻሕፍትን መጻፍ ፍጻሜ የለውም።*



*ምዕራፍ 5*

# ቤተ ክርስቲያን መትከል እና የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን

> በአንጾኪያ ባለችው ቤተ ክርስቲያን ነቢያትና መምህራን ነበሩ እነርሱም በርናባስ፣ ኔገር የተባለው ስምዖንም፣ የቀሬናው ሉኪዮስ፣ የአራተኛው ክፍል ገዥ የሄሮድስም ባለምዋል ምናሔ፣ ሳውልም ነበሩ። እነዚህም ጌታን ሲያመልኩና ሲጦሙ መንፈስ ቅዱስ፦ በርናባስንና ሳውልን ለጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ አለ። በዚያን ጊዜም ከጦሙ ከጸለዩም ወእጃቸውንም ከጫኑ በኋላ አሰናበቱአቸው።
>
> የሐዋርያት ሥራ 13፡1-4

## ስለ አንጾኪያዋ ቤተ ክርስቲያን ልታውቅ የሚገባህ ሰባት ነገሮች

### 1. በአንጾኪያ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን የአዲስ ኪዳን ዋነኛ ቤተ ክርስቲያን እየሆነች መጣች።

አንዳንድ ደቀ መዛሙርት ከቆጵሮስና ፊንቄ ወደ አንጾኪያ በመሄድ በዚያ ቤተ ክርስቲያን ጀመሩ። በመጀመሪያ አንጾኪያ የኢየሩሳሌሙ አገልግሎት ተቀጥያ ነበረች።

> በእስጢፋኖስም ላይ በተደረገው መከራ የተበተኑት እስከ ፊንቄ እስከ ቆጵሮስም እስከ አንጾኪያም ድረስ ዞሩ፣ ቃሉንም ለአይሁድ ብቻ እንጂ ለአንድ ስንኳ አይናገሩም ነበር።
>
> የሐዋርያት ሥራ 11፡19

**2. አማኞች ለመጀመሪያ ጊዜ "ክርስቲያን" ተብለው የተጠሩት በአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ነበር።**

ባገኘውም ጊዜ ወደ አንጾኪያ አመጣው። በቤተ ክርስቲያንም አንድ ዓመት ሙሉ ተሰበሰቡ፤ ብዙ ሕዝብንም አስተማሩ ደቀ መዛሙርትም መጀመሪያ በአንጾኪያ ክርስቲያን ተባሉ።

የሐዋርያት ሥራ 11:26

**3. የመጀመሪያው መንፈሳዊ መነቃቃት(ሪቫይቫል) የተመዘገበው በአንጾኪያ ነው።**

በዚህ መንፈሳዊ መነቃቃት(ሪቫይቫል) ምክንያት በርናባስ ለእርዳታ ተላከ። በኢየሩሳሌም ያለችው ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር በአንጾኪያ እየሠራ ያለውን ነገር ሰምታ በአንጾኪያ ላለው ሥራ በርናባስን በደስታ ላከች።

ወሬውም በኢየሩሳሌም ባለችው ቤተ ክርስቲያን ስለ እነርሱ ተሰማ፤ በርናባስንም ወደ አንጾኪያ ላኩት።

የሐዋርያት ሥራ 11:22

**4. በርናባስ ጳውሎስ እንዲቀላቀል ወሰነ**

**5. ሐዋርያው ጳውሎስ የአንጾኪያዋን ቤተ ክርስቲያን ዋና መቀመጫው አደረጋት።**

ምናልባት በ'ዓለም አቀፍ አንጾኪያ መቅደስ' ከ'ኢየሩሳሌም ክርስቲያን ማዕከል' ይልቅ የቤትነት ስሜት ሳይሰማው አይቀርም።

**6. በአንጾኪያ ብዙ ነቢያትና የወንጌል መልእክተኝነት (የሚስዮናዊነት) አሳብ ያላቸው ብዙ ሰዎች ነበሩ። የኢየሩሳሌሟ ቤተ ክርስቲያን ነቃ ያለ ወንጌል ስርጭት የመውጣትና የወንጌል መልእክተኝነት ሥራ አልነበራትም።**



በአንጾኪያም ባለችው ቤተ ክርስቲያን ነቢያትና መምህራን ነበሩ፤ እነርሱም በርናባስ፣ ኒጌር የተባለው ስምዖንም፣ የቀሬናው ሉክዮስም፣ የአራተኛው ክፍል ገዥ የሄሮድስም ባለምዋል ምናሔ፣ ሳውልም ነበሩ።

የሐዋርያት ሥራ 13:1

**7. የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን የመንፈስ ቅዱስን ድምፅ ሳትዘገይ ታዘዘች። ምርጥ የተባሉትን ሐዋርያቶቻቸውን ቤተ ክርስቲያን ለመትከል በወንጌል መልእክተኝነት በድፍረት ላኩ።**

እነዚህም ጌታን ሲያመልኩና ሲጦሙ መንፈስ ቅዱስ:- በርናባስንና ሳውልን ስጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ አለ።

የሐዋርያት ሥራ 13:2

ጳውሎስና በርናባስ በአንጾኪያ በነበሩበት ጊዜ ብዙ ኃይል አልተመለከቱም። ሲወጡ ነበር ድንቅና ተዓምራትን የተለማመዱት የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍን ስናነብ የምናያቸው ተአምራቶች ጳውሎስና በርናባስ ቤተ ክርስቲያን ለመትከል ሲወጡ የተደረጉ ተአምራቶች ናቸው።

በአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን እና በኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን መካከል ያለው ትልቁ ልዩነት ለኢየሱስ ትእዛዝ የሰጡት ምላሽ ላይ ነው። የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን የሰማችው ቤተ ክርስቲያን የመትከል ትእዛዝ ልክ የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን የሰማችውን ትእዛዝ ነበር። የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ምሳሌን እንከተል! ቤተ ክርስቲያን የመትከል ትዕዛዝን ወዲያውኑ እንታዘዝ! ቤተ ክርስቲያን የመትከል ሥራ ውስጥ ለመግባት ስደትና ችግር እስኪመጣ መጠበቅ አያስፈልግም።

*ከዚህም ሁሉ በላይ፣ ልጄ ሆይ፣ተግሣጽን ስማ ብዙ መጻሕፍትን መጻፍ ፍጻሜ የለውም።*

## ምዕራፍ 6

# መስበክ፣ ማስተማር እና ቤተ ክርስቲያናትን መትከል

መስበክ፣ ማስተማር እና መፈወስ ቤተ ክርስቲያናትን ለመቅርጽ ቁልፍ የሆኑ እንቅስቃሴዎች ናቸው:: ጌታ ኢየሱስ እነኚህን እንብዛም ግንዛቤ ያላገኙ መንገዶች ቤተ ክርስቲያን ለመመሥረት አባቱ የመረጣቸው መንገዶች መሆናቸውን ተረድቶ ነበር::

በኢየሱስ አገልግሎት ውስጥ፣ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ቤተ ክርስቲያናት በዓለም ዙሪያ ሁሉ አብበዋል:: በእውነት ይህች የእግዚአብሔር እጅ ናት፣ ይህ ደግሞ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያኑን የሚመሠርትበት መንገድ ነው::

> ኢየሱስም በምኩራቦቻቸው እያስተማረ፣ የመንግሥትንም ወንጌል እየሰበከ፣ በሕዝብም ያለውን ደዌና ሕመም ሁሉ እየፈወሰ፣ በከተማዎችና በመንደሮች ሁሉ ይዞር ነበር::
>
> ማቴዎስ 9:35

ብዙ ገንዘብ መጠቀም፣ አስተዳደራዊ ጥበብ፣ የስጦታዎች አያያዝና ትምህርት ቤቶችን፣ ሆስፒታሎችን መገንባት የኢየሱስን የሦስት ዓመት ተኩል አገልግሎት ያህል በፍጹም አላፈራም::

በሚቀጥሉት ጥቂት ምዕራፎች፣ የስብከት፣ የማስተማር፣ እና የፈውስ አገልግሎቶችን እዘረዝራለሁ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ በሺዎች የሚቆጠሩ



ቤተ ክርስቲያናትን በተለያዩ ሕዝቦች፣ ባህሎችና ቋንቋዎች ውስጥ ማፍለቅ የተጠቀመበትን መንገድ አሳያለሁ::

በቃ፣ ዘለቄታ ያላት ቤተ ክርስቲያን ተወልዳለች:: ሁለት ሺህ ዓመታት የሦስት ዓመት ስብከት፣ ማስተማር እና ፈውስ ሊያጠፋ አልቻለም:: በሚቀጥሉት ምዕራፎች ውስጥ ስለ ስብከት እና ማስተማር ስታነብ፣ የሚጠበቅብህ እግዚአብሔር እምነትን በውስጥህ እንዲገነባ መፍቀድ ብቻ ነው:: በዚህ በተዋረደ እና 'የሞኝነት' ቤተ ክርስቲያን የመቅረጽ መንገድ ማመን አለብህ:: ትልቁ ግራ መጋባት ኢየሱስ ካደረገው በተሻለ መንገድ አደርጋለሁ ብሎ ማሰብ ነው::

> ደቀ መዝሙር እንደ መምህሩ ባሪያም እንደ ጌታው መሆኑ ይበቃዋል:: . . .
>
> ማቴዎስ 10:25

ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር ሰው ቢሆን ምን ያደርጋል ብዬ እገረማለሁ:: በዓለም ላይ ብዙ ችግሮችና በቂ ያልሆኑ መፍትሔዎች አሉ:: በአጠቃላይ፣ እግዚአብሔር መልካም ነገሮችን እንደሚያደርግና የሰዎችን ችግር እንደሚፈታ እናውቃለን:: እግዚአብሔር አጠር ላለ ጊዜ ወደዚህ ምድር ቢመጣ ሊያደርጋቸው ይችላል ተብሎ የሚታሰቡ ነገሮች እነኚህ ናቸው::

## ለእግዚአብሔር የቀረቡ ዘጠኝ አስተያየቶች

1. ምናልባት እግዚአብሔር የተለያዩ ትላልቅ ዩኒቨርስቲዎችን ቢያቋቁም
2. ምናልባት እግዚአብሔር ከዓለም ትልቁንና ለብዙ ሕመምተኛ ሰዎች አገልግሎት የሚሰጥ ሆስፒታል ቢገነባ::
3. ምናልባት እግዚአብሔር በሺዎች ለሚቆጠሩ ገጠሮች የመጠጥ ውሃ ቢያዘጋጅ

4. ምናልባት እግዚአብሔር ትልቁን የሃይድሮ ኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ግድብ ቢገነባ
5. ምናልባት እግዚአብሔር ለስደተኞችና ለተፈናቀሉ የዓለም ሕፃናት አገልግሎት የሚሰጥ የእርዳታ ማስተባበሪያ ማዕከል ቢያቋቁም
6. እግዚአብሔር ሰው ቢሆን፣ ምናልባት ብዙ የሙት ልጆች ማሳደጊያ(ኦርፋንኤጅ) ማዕከሎችን ይገነባ ነበር
7. እግዚአብሔር ሰው ቢሆን ኖሮ ምናልባት ትልቅ የንግድ ተቋም አቋቁሞ ሥራውን በገንዘቡ ይደግፍ ነበር።
8. እግዚአብሔር ሰው ቢሆን፣ ዕድሜያቸው ለትምህርት የደረሰ ሕፃናት አገልግሎት ለመስጠት ትምህርት ቤቶችን ያቋቁም ነበር። ይህ በዓለም ላይ ያለውን ማይምነት በመቀነስ ብዙ ሰዎች እንዲሻሻሉ ያደርጋል።
9. እግዚአብሔር ሰው ቢሆን፣ ተጽዕኖ ለማምጣትና ዓለምን ለመርዳት ወደ አንድ የፖለቲካ ድርጅት ውስጥ ይገባ ነበር። ምናልባት የተሻለ ፕሬዘዳንት በመሆን ዓለምን ይረዳ ነበር።

ግን እግዚአብሔር ሰው ሆኖ ነበር። እግዚአብሔር አጠር ላለ ጊዜ በሰው አምሳል ተገልጦ ነበር።

> በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ይህ አሳብ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን። እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቆጠረውም፣ ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ፣ በምስሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ፣ ለሞትም ይኸውም የመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ።
> በዚህም ምክንያት ደግሞ እግዚአብሔር ያለ ልክ ከፍ ከፍ አደረገው ከስምም ሁሉ በላይ ያለውን ስም ሰጠው ይህም በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ፣ መላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው።
>
> ፊሊጲስዮስ 2፡5-11



እግዚአብሔር ሰው እንደሆነ በምን እናውቃለን? እግዚአብሔር በእርግጥ ሰው እንደሆነ ምን ማረጋገጫ አለን? በእነኚህ ምክንያቶች እናውቃለን።

1. እግዚአብሔር ሰው ለመሆን፣ ወደዚህ ዓለም መግቢያው ያልተለመደ መሆን ነበረበት። እናም በእርግጠኝነት፣ ከብዙ ያልተለመዱ ሁኔታዎች ጋር ኢየሱስ ከድንግል ተወልዷል።

> እነሆ፣ ድንግል ትፀንሳለች ልጅም ትወልዳለች፣ ስሙንም አማኑኤል ይሉታል። የተባለውም ይፈጸም ዘንድ ይህ ሁሉ ሆኗል፣ ትርጓሜውም፡- እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የሚል ነው።
>
> ማቴዎስ 1፡23

ከ109 በላይ የሚሆኑ ትንቢቶች በኢየሱስ ወደዚህ ዓለም መምጣት ተፈጽመዋል።

2. እግዚአብሔር ሰው ቢሆን፣ ተነግረው የማይታወቁ ታላላቅ ቃሎችን በተናገረ ነበር። ምናልባትም ቃሎቹ ከቶውንም የማይረሱ ይሆኑ ነበር። ይህ ነው በትክክል የሆነው። ምንም እንኳ ኢየሱስ መጽሐፍ ጽፎ ባያውቅም ወይም በካሴት ባይቀረጽም፣ ቃሎቹ በዘመናት መካከል እያስተጋቡ ነው።

> እንደ ጻፎቻቸው ሳይሆን እንደ ባለ ሥልጣን ያስተምራቸው ነበርና።
>
> ማቴዎስ 7፡29

3. እግዚአብሔር ሰው ቢሆን፣ ኃጢአት የሌለበትና ፍጹም ይሆን ነበር፣ በእርግጠኝነት፣ ኢየሱስ ፍጽሞ ሰው ነበር። ኃጢአትን አላደረገም።

> እርሱም ኃጢአት አላደረገም፣ ተንኮልም በአፉ አልተገኘበትም።
>
> 1ኛ ጴጥሮስ 2፡22

4. እግዚአብሔር ሰው ቢሆን፣ በሰው ዘር ላይ ለዘመናት ተጣብቀው የሚገኙ ችግሮችን ባሸነፈ ነበር። ሕመምንና በሽታን ድል ባደረገ ነበር። ይህን ነው ኢየሱስ በትክክል ያደረገው። ሁሉም ዓይነት በሽታዎችና ሕመሞች ከጌታ ፊት ተወግደው ነበር።

በዚያ ምሽት በአጋንንት የተያዙ ብዙ ሰዎችን ወደ ኢየሱስ አመጡ፤ እርሱም መናፍስትን በቃሉ አስወጣ፤ በሽተኞችንም ሁሉ ፈወሰ።

ማቴዎስ 8፡16

5. እግዚአብሔር ሰው ቢሆን፣ እርሱ የፈጠራቸውን ነገሮች መቆጣጠር ይችል ነበር። ኢየሱስም ያደረገው ይህንኑ ነው። በነፋስና በዝናብ ላይ ኃይሉን ተጠቅሟል። በፈጠረው ባሕር ላይ እንኳ ተራምዷል።

ደቀ መዛሙርቱም በባሕር ላይ ሲሄድ ባዩት ጊዜ፦ ምትሐት ነው ብለው ታወኩ በፍርሃትም ጮኹ።

ማቴዎስ 14፡26

6. ለአጭር ጊዜ ቆይታ እግዚአብሔር ሰው ቢሆን፣ ምድርን ቢጎበኝ፣ ጊዜውም ምንም አጭር ቢሆን፣ ሁልጊዜ እንደታወሰ ይኖራል። እግዚአብሔር የጎበኘን ጊዜ እየተባለ ይታወሳል። በእርግጥ የክርስቶስ ጉብኝት በፍጹም ተዘንግቶ አያውቅም። እውነትም የኢየሱስ መምጣት እና መመለስ በመላው ዓለም በየዓመቱ ይከበራል። ከክርስቶስ ጉብኝት ሁለት ሺህ ዓመት በኋላ፣ ፋሲካ እና ገና ዛሬም በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚከበሩ በዓላት ናቸው።



7. እግዚአብሔር ሰው ቢሆን፣ የሰውን ልጅ ትልቅ ጠላት ሞትን ድል ባደረገ ነበር። ጌታ ኢየሱስ እንደሚሞትና ከሦስት ቀን በኋላ እንደሚነሣ በቀስታ ተንቢዮ ነበር። ሞትን የማይፈራ ይመስል ነበር። እኛ ወደዚያ እንዳንሄድ ሞትን፣ መቃብርን እና ሲኦልን ድልነሣ።

አሁን ግን ሞትን ደምስሶ በወንጌል አማካይነት ሕይወትንና ኢመዋቲነትን ወደ ብርሃን ባወጣው በመድኃኒታችን በክርስቶስ ኢየሱስ መምጣት ተገልጦአል።

2ኛ ጢሞቴዎስ 1፡10

(አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

8. እግዚአብሔር ሰው ቢሆን ለሰው ልጆች ሁሉ ከፍተኛውን መልካም ነገር በማድረግ ጊዜውን እንደሚያሳልፍ እናውቃለን።

እግዚአብሔር የናዝሬቱ ኢየሱስን በመንፈስ ቅዱስ በኃይልም ቀባው፤ እርሱም መልካም እያደረገ ለዲያቢሎስም የተገዙትን ሁሉ እየፈወሰ ዞረ፤ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነበርና፤

የሐዋሪያት ሥራ 10፡38

## ከፍተኛው መልካም ነገር

ውድ ወዳጄ፣ ክርስቶስ በምድር ላይ በነበረው አጭር ቆይታ በምን ዓይነት እንቅስቃሴዎች ላይ ራሱን እንዳሰማራ ራሳችንን እንጠይቅ። ትምህርት ቤቶችን እና ሆስፒታሎችን መገንባት ነበር? ወላጅ አልባ ሕፃናትን ማሳደጊያ ተቋም መገንባት እና የኤሌክትሪክ እና የውሃ አቅርቦቶችን ማዘጋጀት ነበር? መልሱ አይደለም ነው! ኢየሱስ ያደረጋቸውን ነገሮች አራቱን ወንጌላት በማንበብ ልናውቅ እንችላለን። በተለይም፣ የክርስቶስን ምድራዊ እንቅስቃሴዎች አጠቃሎ የሚያሳይ አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ አለ። በጥንቃቄ እንድታነበው እፈልጋለሁ።

ኢየሱስም በምኩራቦቻቸው እያስተማረ፣ የመንግሥትንም ወንጌል እየሰበከ፣ በሕዝብም ያለውን ደዌና ሕመም ሁሉ እየፈወሰ፣ በከተማዎችና በመንደሮች ሁሉ ይዞር ነበር።

ማቴዎስ 9፡35

ይህ ጥቅስ እግዚአብሔር በምድር ላይ በነበረበት ወቅት የተሰማራው በመስበክ፣ በማስተማር እና በመፈወስ ላይ እንደ ነበር ያሳየናል። እነኚህ ሦስት ሥራዎች ለሰው ዘር ከሁሉ በላይ ጠቃሚ ነበሩ ማለት ይቻላል። ለዚያ ነው ራሱን በእነኚህ ላይ ያሰማራው። ለዚህ ዓለም ይበልጥ የተሻለ ነገር የተሠራው በክርስቶስ ኢየሱስ ስብከት፣ ማስተማር እና መፈወስ ነበር። ከእነኚህ የተሻለ ወይም በይበልጥ የሚረዳ ነገር ቢኖር ኖሮ፣ ባደረገው ነበር። ይህ ስብከት፣ ማስተማር እና ፈውስ በሺህዎች የሚቆጠሩ ቤተ ክርስቲያኖችን ወልዷል።

**በእርግጠኝነት መደምደም የምንችለው ነገር በዚህ ምድር ላይ ላለ ማንኛውም ኅብረተሰብ ሊሰጥ የሚችል ከሁሉ በላይ አስፈላጊ እና ከፍተኛው እገዛ ስብከት፣ ማስተማር እና መፈወስ ነው።** በእርግጥ ማናችንም ብንሆን ከእግዚአብሔር ይበልጥ ጥበበኛ ወይም ሩ ኅሩኅ ነኝ ብለን የምናስብ አይመስለኝም።

ብዙ ጊዜ ሰዎች ለምን የሕክምና ሙያን ትተህ ወደ አገልግሎት ገባህ ብለው ሲጠይቁኝ ይገርመኛል። እንደሚመስለኝ እነኚህ ሰዎች ማንኛውም ሰው ለኅብረተሰቡ ሊሰጥ የሚችለው ከፍተኛው እገዛ ሕክምና ነው ብለው ያስባሉ።

የሕክምና ሙያ በጣም የከበረና የበጎ አድራጎት ሥራ እንደሆነ እስማማበታለሁ፤ ያለ ዶክተሮች ምን ማድረግ እንችላለን? ግን ኢየሱስ



ለሰው ዘር ልንሰጠው የምንችለው ከፍተኛና ምርጥ የእርዳታ ዓይነት አሳይቶናል።

በአገልግሎት ውስጥ ያሉ መጋቢዎች ላይ የመስበክ፣ የማስተማር እና የመፈወስ ሚናቸውን እንዲተዉ ብዙ ጊዜ ግፊት ሲደረግባቸው ያሳዝናል። ዓለማዊ የሆነ ሥራ መሥራት ይበልጥ እንደሚጠቅም እስኪሰማቸው ድረስ ብልጣብልጥ የሆነ ሥነልቦናዊ ተጽዕኖ ይደረግባቸዋል። ከፍተኛው የሽንገላ ዓይነት ከእግዚአብሔር ይበልጥ ጠቢብ ነኝ ብሎ ማሰብ ነው። ትልቁ ግራ መጋባት ክርስቶስ ካደረገው በላይ ተጽዕኖ ማምጣት እችላለሁ ብሎ ማሰብ ነው።

ዓለም የሚያስፈልገው ስብከት፣ ማስተማር እና ፈውስ እንደሆን የመረዳት ጊዜው አሁን ነው። ዓለም ሰባኪዎችን እየጠበቀች ነው። ዓለም አስተማሪዎችን እየጠበቀች ነው። እግዚአብሔር ፈቃዱን የሚያደርጉ የሰባኪዎችንና የአስተማሪዎችን ሠራዊት እያስነሣ ነው። በበመስበክ፣ በማስተማር እና በመፈወስ ጌታ ኢየሱስ በሺህዎች የሚቆጠሩ ቤተ ክርስቲያናትን አምጥቷል፣ እነኚህም በሺህዎች ለሚቆጠሩ ዓመታት ዘልቀዋል።

ቤተ ክርስቲያን፦ UN (የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት)፣ WHO(የዓለም ጤና ድርጅት) UNHCR(የተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽን) ቢጨፈለቁ ከሰጡት በላይ አድርጋለች። በእርግጠኝነት ቤተ ክርስቲያን ከብዙ መንግሥታት ይልቅ የተሻለ መልካም ነገር አድርጋለች። ይህ ሁሉ መልካም ነገር የኢየሱስ የሦስት ዓመት ተኩል ስብከት፣ ማስተማር፣ እና መፈወስ ውጤት ነው።

ቤተ ክርስቲያን አግባብነት የሚኖራት በማኅበራዊ ሥራዎች ላይ ስትሳተፍ ነው የሚሉ ሰዎችን በፍጹም አልቀበላቸውም። ቤተ

ክርስቲያን ትክክል የምትሆነው በስብከት፣ በትምህርት እና በመፈወስ ላይ ስትሰማራ ነው። እግዚአብሔር የሚያደርገው ይህንን ነው፣ እኛም ልናደርግ የሚገባን ይህንኑ ነው። የእግዚአብሔር ጥበብ ለሰው ሞኝነት ነው። እግዚአብሔር ሰው በስብከት ሞኝነት ይድን ዘንድ መረጠ።

> **በእግዚአብሔር ጥበብ ምክንያት ዓለም እግዚአብሔርን በጥበብዋ ስላላወቀች፤ በስብከት ሞኝነት የሚያምኑትን ሊያድን የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ሆኖአልና።**
>
> **1ኛ ቆሮንቶስ 1፥21**

ሰዎች ዶክተር ብሆን ለኅብረተሰቡ ምን ያህል ጠቃሚ እሆን እንደነበር ይነግሩኝ ነበር፣ እኔ ግን እላችኋለሁ አሁን በሰባኪነቴ ይበልጥ እጠቀማለሁ። በማንም ሰው ላይ ካለው ጥሪ ይልቅ የሰባኪነት ጥሪ ታላቅ እንደሆን አምናለሁ። የሰውን ልጅ ከሁሉ በተሻለ መንገድ ልንረዳ የምንችለው በመስበክ፣ በማስተማር እና ለፈውስ በመጸለይ ነው። ለዚህ ነው ለስብከት ኃይል፣ አስተማሪ የመሆን ጸጋ እና በሽተኞችን የመፈወስ ጸጋ እንዲሰጥህ መጸለይ ያለብህ። እግዚአብሔር ሰው ሲሆን፣ ራሱን ለስብከት ሰጠ።

> ***ከዚህም ሁሉ በላይ፤ ልጄ ሆይ፤ ተግሣጽን ስማ ብዙ መጻሕፍትን መጻፍ ፍጻሜ የለውም።***



*ምዕራፍ 7*

# ስብከት ለምን ኃያል ሆነ

## 1. ስብከት የሰውን ችግር ሥረ መሠረት ይመታል

### ኃጢአት የሐዘኖችን ሁሉ ሥር ነው

ዓለም ወደ ሲኦል በመሄድ ላይ ባሉ ኃጢአተኞች ተሞልታለች። የፈለገውን ያህል መልካም ሰው ሁን፣ ኃጢአቶችህ ግን ለእግዚአብሔር የተገለጡ ናቸው። በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ነኝ ብሎ የሚያስብ ማንኛውም ሰው በከፍተኛ ሽንገላ እየተሠቃየ ነው።

በእግዚአብሔር ቀኝ እንድንቆም የሚያደርገን ብቸኛ ነገር የኢየሱስ ደም ነው። የሚያሳዝነው ነገር ግን በከፊል ፍጹማን እንደሆንን እና መንግሥተ ሰማያት የመግባት መብት እንዳለን ተደርጎ የሚሰጥ እና የክርስቶስ አካልን ወደ ሽንገላ ውስጥ የሚከት ትምህርት መስጠቱ ነው።

እንደምታከብራቸው የማውቀውን ጥቂት ሰዎች ምሳሌ ልስጥህ። እግዚአብሔርን እያወቁ ሲሄዱ ይበልጥ ትሑት እየሆኑና ከእግዚአብሔር ጋር መቆማቸውን እንኳ እርግጠኛ እንዳልነበሩ ታስተውላለህ።

### ሐዋርያው ጳውሎስ

ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ራሱ ያለው አመለካከት እየቀነሰ መጣ። ከከፍተኛ ሐዋርያነት ወደ ከሁሉ የባሰ ኃጢአተኝነት ወረደ። ይህ እውነተኛ ትሕትና ዕድገት ነው።

i. በመጀመሪያ፣ ከማናቸውም ሐዋርያት እንደማያንስ አድርጎ ራሱን ተመለከተ

> . . . ከዋነኞቹ ሐዋርያት በምንም አልጎድልምና፡፡
>
> 2ኛ ቆሮንቶስ 12፡11

ii. በኋላ ደግሞ ከእነኚሁ ሐዋርያት ሁሉ የሚያንስ እንደሆነ ተመለከተ

> እኔ ከሐዋርያት ሁሉ የማንስ ነኝና፣ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ስላሳደድሁ ሐዋርያ ተብዬ ልጠራ የማይገባኝ
>
> 1ኛ ቆሮንቶስ 15፡9

iii. ትንሽ ቆየት ብሎ፣ ራሱን ከሐዋርያት ጋር ማወዳደሩን ተወና **ከቅዱሳን ሁሉ እንደሚያንስ ቆጠረ፡፡**

> ምንም እንኳ **ከቅዱሳን ሁሉ** ያነስሁ ብሆንም፣ የማይመረመረውን የክርስቶስን ባለጠግነት ለአሕዛብ እሰብክ ዘንድ ይህ ጸጋ ለእኔ ተሰጠኝ፡፡
>
> ኤፌሶን 3፡8
> (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

iv. በመጨረሻም፣ በሕይወቱ ማብቂያ እና ከመጨረሻዎቹ መልእክቶቹ በአንዱ፣ ራሱን ከሐዋርያት ወይም ከቅዱሳን ጋር ለማወዳደር አልሞከረም፡፡ ከኃጢአተኞች ዋነኛ መሆኑን ደመደመ፡፡

> **ኃጢአተኞችን** ሊያድን ክርስቶስ ወደ ዓለም መጣ የሚለው ቃል የታመነና ሁሉ እንዲቀበሉት የተገባ ነው፡፡ **ከኃጢአተኞችም ዋና እኔ ነኝ፡፡**
>
> 1ኛ ጢሞቴዎስ 1፡15

## ኢዮብ

ኢዮብ ትክክለኛ እና ፍጹም የሆነ ሰውና ከክፉ የራቀ እንደሆነ በእግዚአብሔር ተገልጿል፡፡ ቢሆንም ግን ኢዮብ ከእግዚአብሔር ጋር ሲገናኝ በእርግጥ በጣም መጥፎ ሰው እንደሆነ ተረደ፡፡ "ራሴን እንቃለሁ"



> ሁሉን ታደርግ ዘንድ ቻይ እንደሆንህ፣ አሳብህም ይከለከል ዘንድ ከቶ እንደማይቻል አወቅሁ፡፡ ያለ እውቀት ምክርን የሚሰውር ማን ነው? ስለዚህ እኔ የማላስተውለውን፣ የማላውቀውንም ድንቅ ነገር ተናግሬአለሁ፡፡ እባክህ፣ ስማኝ፣ እኔም ልናገር፡፡ እጠይቅህማለሁ፣ አንተም ተናገረኝ፡፡ መስማትንስ በጆሮ በመስማት ሰምቼ ነበር፤ አሁን ግን ዓይኔ አየችህ **ስለዚህ ራሴን እንቃለሁ** በአፈርና በአመድ ላይ ተቀምጬ እጸጸታለሁ፡፡
>
> ኢዮብ 42፡2-6

## ጴጥሮስ

ጌታ አንድ ቀን ሲገለጥ ሐዋርያው ጴጥሮስ አሣ በማጥመድ ላይ ነበር፡፡ አጠገቡ የቆመው ኢየሱስ መሆኑን ሲያውቅ፣ የኃጢአተኝነት ስሜት ተሰምቶት እንዲህ አለ፣ "እኔ ኃጢአተኛ ሰው ነኝ"፡፡ የእግዚአብሔር መገኘት ሁልጊዜ ጥልቅ የሆነውን ብልሹነታችንን ይገልጠዋል፡፡

> ስምዖን ጴጥሮስ ግን ባየ ጊዜ በኢየሱስ ጉልበት ላይ ወድቆ፡- **ጌታ ሆይ፣ እኔ ኃጢአተኛ ነኝና ከኔ ተለይ አለው፡፡**
>
> ሉቃስ 5፡8

## ዳንኤል

ዳንኤል በጌታ እጅግ የተወደደ ቅዱስ ነብይ ነበር፡፡ ይሁንና በጌታ ፊት ሲቀርብ፣ እንዲህ አለ

> ራእዩን ያየሁት እኔ ዳንኤል ብቻ ነበርሁ፤ ከእኔ ጋር የነበሩት ሰዎች አላዩም፣ ነገር ግን ታላቅ ፍርሀት ስለ ወደቀባቸው ሸሽተው ተደበቁ፡፡ ስለዚህ ይህን ታላቅ ራእይ እያየሁ ብቻዬን ቀረሁ፤ ምንም ጉልበት አልነበረኝም፡፡ **መልኬ እጅጉን ገረጣ** ኃይልም አጣሁ፡፡ ከዚያም የቃሉን ድምፅ በሰማሁ ጊዜ፣ በግምባሬ በምድር ላይ ተደፍቼ በከባድ እንቅልፍ ተዋጥሁ፡፡ እነሆም፣ አንድ እጅ ዳሰሰኝ፤ እየተንቀጠቀጥሁም በእጄና በጉልበቴ አቆመኝ፣ እርሱም፣ "እጅግ የተወደድህ ዳንኤል ሆይ፤ አሁን ወዳንተ ተልኬአለሁና፣ የምነግርህን አስተውል፣ ቀጥ ብለህም ቁም" አለኝ፡፡ ይህን ሲለኝም፣ እየተንቀጠቀጥሁ ተነሥቼ ቆምሁ፡፡
>
> ዳንኤል 10፡7-11
> (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

ይህ ሁሉ ማንም ጻድቅ እንደሌለ ያረጋግጥልናል፣ አንድ ስንኳ፡፡ ተብሎ እንደተጻፈ፡-

**ጻድቅ የለም፤ አንድ ስንኳ**

**ሮሜ 3፡10**

ዓለምን ሁሉ እያጠፋ ያለው በዓለም ላይ የሰፈነው ኃጢአት ነው፡፡ በዓለም ላይ ያሉ ችግሮች ሁሉ ምክንያት ኃጢአት ነው፡፡ የዋይታችን ሥር ኃጢአት ነው፡፡ ለዚህ ነው ለሰው ልጆች ችግር ሁሉ መድኃኒቱ ስብከት የሚሆነው፡፡ ስብከት የሰው ልጅን ችግር ከሥረ- መሠረቱ ይነቅላል፡፡

## ኃጢአት ሰዎችን ሁሉ ወደ ሞታቸው ይመራል

**ስለዚህ ኀጢአት በአንድ ሰው በኩል ወደ ዓለም እንደ ገባ ሁሉ፣ ሞትም በኀጢአት በኩል ገብቶአል፤ በዚሁ መንገድ ሞት ወደ ሰዎች ሁሉ መጣ፤ ምክንያቱም ሁሉም ኀጢአትን ሠርተዋል፤ ሕግ ከመሰጠቱ በፊት ኀጢአት በዓለም ላይ ነበር፤ ነገር ግን ሕግ በሌለበት ኀጢአት አይቆጠርም፡፡ ይሁን እንጂ ከአዳም ËUa ሽእስከ S<c? ሕግን በመጣስ ኀጢአት ባልሠሩት ላይ እንኳ ሞት ነገሠ፤ አዳም ይመጣ ዘንድ ላለው አምሳሉ ነበር፡፡**

**ሮሜ 5፡12-15**

በኃጢአት ምክንያት ሞት ወደ ሰዎች ሁሉ ደረሰ፡፡ በሕይወታችን ውስጥ ያለው ኃጢአት ወደ ሞት ይመራናል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ኃጢአት ከተፈጸመ በኋላ ሞትን እንደሚያመጣም ይናገራል፡፡

**ምኞትም ከፀነሰች በኋላ ኀጢአትን ትወልዳለች፤ ኀጢአትም ካደረገች በኋላ ሞትን ትወልዳለች፡፡**

**ያዕቆብ 1፡15**

ሞት የሰው ልጆች ሊያመልጡት የማይቻል ፍጻሜ ነው፡፡ ሞታችን የሚያሳየው እውነታ የኃጢአት መኖርን ነው፡፡ የሆነ ሰው ሲሞት ባየሁ



ጊዜ ሁሉ፣ ኃጢአት ሥራውን እንደፈጸመች እወቅ፡፡ ሞት የኃጢአት ብቸኛ ውጤት እንደሆነ እወቅ፡፡

## ከሞት ምክንያቶች ሁሉ በስተጀርባ ኃጢአት አለ

የኃጢአት መኖር፣ ታዋቂ ለሆኑት እንደ፡- ካንሰር፣ ኤች.አይ.ቪ፣ የማይድኑ በሽታዎች፣ ሕመሞች፣ አደጋዎች እና እርጅና፣ ሁሉ በር ይከፍታል፡፡ በዚህ፣ ዓለም ያሉ በሽታዎች ሁሉ ከኃጢአተኝነታችን ጋር ሊፈረጁ ይችላሉ፡፡

እንደምታስተውለው፣ የሰው ልጅን ለመርዳት የሚደረግ ሙከራ ሁሉ የኃጢአትንና ሞትን መኖር ሊያጠፋ አልቻለም፡፡ ስለዚህ ሞት ለተፈረደበት የሰው ልጅ ሕይወትን የሚሰጥ ብቸኛ መፍትሔ ስብከት ነው፡፡

**በእርሱ ሕይወት ነበረች፣ ሕይወትም የሰው ብርሃን ነበረች፡፡**

**ዮሐንስ 1፡4**

የትኛውም ሆስፒታል ሕይወትን ሊሰጥህ ቃል አይገባልህም፡፡ የትኛውም ሕክምና ሕይወት ሊሰጥህ አይችልም፡፡ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሞት ችግርህን ሊቀርፍ አይችልም፡፡ ሁላችንም የሞት ፍርድ ተፈርዶብናል እናም ሕይወትን ሊሰጠን የሚችል ኢየሱስ ብቻ ነው፡፡ ኢየሱስ፣ "ሕይወት እንዲሆንላችሁ መጣሁ"፣ አለ፡፡

## የሞት ፍርድ

በአሜሪካ ውስጥ የሞት ፍርድ ስለ ተፈረደበት ወጣት የተሠራ ጥናታዊ ፊልም እንዳየሁ አስታውሳለሁ፡፡ ይህ ፊልም ፖሊስ ገድለሃል ተብሎ ስለ ተወነጀለ ጥቁር አሜሪካዊ የተሠራ አሳዛኝና ስሜትን የሚፈነቅል እውነተኛ ታሪክ ነበር፡፡ ይህ ሰው ፖሊሱን እንዳልገደለ የእምነት ክህደት ቃሉን የሰጠ ሲሆን ብዙ ሰዎችም ወንጀለኛ እንዳልሆነና በእውነት ንፁሕ ሰው እንደሆነ አምነዋል፡፡

አስደናቂ የሆነ ጥናታዊ ፊልም ነበር። ይህን ሰው የሞት ፍርድ ሲፈጽም እስከ ደረሰበት ጥቂት ደቂቃዎች ድረስ በፊልም ቀርጸዉት ነበር። ቤተሰቡና ጓደኞቹ የመጨረሻውን እራት አብረውት እንዲበሉ ተጋብዘው ነበር።

በመጨረሻም መሰናበቻቸው ጊዜ ደረሰና አንዳቸውም ሳይቀሩ አቅፈው ተሰናበቱት። ከዚያም በኋላ ከመጋቢውና ከጠበቃው ጋር ሊነጋገር ወደሚችልበት ባዶ ክፍል ወሰዱት። በአንድ ሰዓት ውስጥ፣ የሞት ፍርድ ተፈጸመ።

የሞት ፍርዱ ከተፈጸመ በኋላ ጠበቃውና መጋቢው ቃለ መጠይቅ ተደረገላቸው። መጋቢው የተጠየቀውን አንድ ጥያቄ አስታውሳለሁ።

"የነበረው የመጨረሻ ቃልህ ምን ነበር?" ብሎ አንድ ሰው ጠየቀው መጋቢውም እንዲህ ሲል መለሰ፣ "ሁላችንም በሞት ፍርድ ሥር እንዳለን ነገርሁት፣ ልዩነቱ ብዙዎቻችን የሞት ፍርዳችንን የምንቀበልበትን ቀን አለማወቃችን ነው።"

እነኚህን ቃላት ሳወጣና ሳወርድ፣ እንዴት እውነት እንደሆኑ ለራሴ አሰብሁ። እውነትም በሞት ፍርድ ሥር ነን። ወደድንም ጠላንም ሁላችንም እንሞታለን። የጊዜ ሁኔታ እንጂ የሞት ፍርዳችን ይደርስብናል። ከዚህ የሞት ፍርድ ሊያድነንና አዲስ ሕይወት ሊሰጠን የሚችል ኢየሱስ ብቻ ነው። ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፣ "እኔ መንገድ፣ እውነትና ሕይወት ነኝ።"

ለዚህ ነው ስብከት በጣም አስፈላጊ የሆነው። ይህ ነው ስብከትን ከሌሎች ዓይነቶች የሰው እርዳታዎች ልዩ የሚያደርገው። ስብከት ለተፈረደበት ሰው ሕይወትን ያመጣል! ኢየሱስ እንዲህ አለ፣ "እኔ የነገርኳችሁ ቃል መንፈስ ነው ሕይወትም ነው (ዮሐንስ 6:63)።"



## 2. ስብከት የእግዚአብሔር ኃይል እንዲለቀቅ ያደርጋል

**በወንጌል አላፍርምና አስቀድሞ ለአይሁዳዊ ደግሞም ለግሪክ ሰው ለሚያምኑ ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነውና።**

**ሮሜ 1:16**

**ቃሉን ላከ ፈወሳቸውም ከጥፋታቸውም አዳናቸው።**

**መዝሙር 107:20**

በአንድ ወቅት ከስዊዘርላንድ ተጋብዞ የመጣ ሰባኪ ስለ ቤተ ክርስቲያኔ አንድ አስተያየት ሰጠ። እንዲህ በማለት:- "ቤተ ክርስቲያንህ እንደ አንድ ግዙፍ የወጣቶች ቡድን ነው"። በመቀጠልም:- "በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ብዙ ወጣቶች አሉ"፤ አለ።

እስከዚያን ጊዜ ድረስ፣ ቤተ ክርስቲያናችን በወጣቶች የተሞላች መሆኗን አላስተዋልሁም ነበር። አንድ ሰው ቤተ ክርስቲያኔ በወጣቶች የተሞላች መሆኗን ሲናገር እንደ አድናቆት አልቆጥረውም ነበር።
ይሁን እንጂ ፣ጊዜው እየገፋ ሲሄድ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ወጣቶችን ለማግኘት የእግዚአብሔር ኃይልን እንደሚጠይቅ ተረዳሁ።

ታያለህ፣ ወጣቶች በጉልበትና በከፍተኛ ጉጉት የተሞሉ ናቸው። በወጣቶች ውስጥ ብቻ የሚገኙ አንዳንድ መሻቶች አሉ። ቤተ ክርስቲያን በወጣቶች የተሞላች በምትሆንበት ጊዜ፣ የእግዚአብሔር ኃይል መገኘት ምልክት ነው።

ፖሊስ ወጣቶችን መለወጥ አይችልም። የሥነ ምግባር ደንቦች ያልተገሩ ወጣቶችን ሊገድቡ አይችሉም። ዛሬ ዛሬ ወደ እስር ቤት የመግባት ፍርሃት ሰዎችን የሚገታ አይመስልም። ይሁን እንጂ፣ እጅግ በጣም የደነደነ ኃጢአተኛን ሊለውጥ የሚችል ኃይል ያለው አንድ ነገር አውቃለሁ። ወላጆችን፣ መምህራንን፣ አማካሪዎችን ባአጠቃላይ ማንንም ሰው የማይሰሙ ሰዎች በእግዚአብሔር ቃል "ታስረው" ለዘላለም

ሲለወጡ አይደንቅም? በእውነት፣ የመስቀሉ ስብከት የእግዚአብሔር ኃይል ነው።

እግዚአብሔርን ማገልገል የጀመርሁት ገና በልጅነቴ ነው። እግዚአብሔርን የተከተልሁት በሙሉ ልቤ ነው። እንደ እኔ ያለውን ወጣት ሙያውን ትቶ ሰባኪ እንዲሆን የሚያደርገው ምንድር ነው? ይህ የእግዚአብሔር ኃይል ሲሠራ ነው።

ስብከት ሁልጊዜ ኃይልን ይለቃል ይህ ኃይል ደግሞ ሰዎችን የመለወጥ ችሎታ አለው። ለዚያ ነው ሰባኪ መሆን ያለብህ። ይህ የሚሆንበት ምክንያት ስብከት ኃይልን የመልቀቅ ችሎታ ስላለው ነው።

## 3. ስብከት ተስፋ ይሰጣል

> በመጽናትና መጻሕፍት በሚሰጡት መጽናናት ተስፋ ይሆንልን ዘንድ አስቀድሞ የተፈጸፈው ሁሉ ለትምህርታችን ተጽፎአልና።
>
> ሮሜ 15፡4

ብዙ ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመጡት በጭንቀላታቸው ውስጥ ተስፋ አስቆራጭ ሁኔታዎች ተንጠልጥለው ነው። የእግዚአብሔር ቃል ወደ እነርሱ ሲመጣ፣ ተስፋ መቁረጥ እና ተስፋ ቢስነት ይወገዳሉ። ጠንካራ ነፋስ እንደመጣበት ገለባ፣ ተስፋ መቁረጥ እና ሀዘን እንዲበኑ ይገደዳሉ። የተስፋ ቃል ስብከት ሰዎችን ሕያው ያደርጋል።

## ከተስፋ የተነሳ በሕይወት የቆየችው አይጥ

በአንድ ወቅት በጨለማ ክፍል ውስጥ በውሃ የተሞላ ባልዲ ውስጥ በተከተተች አይጥ ላይ የተደረገውን የሙከራ ጥናት አነበብሁ። በዚህ ክፍል ውስጥ ሙሉ በሙሉ ምንም ብርሃን አልነበረም። ከሦስት ደቂቃ ያህል ቆይታ በኋላ፣ አይጧ በባልዲ ውስጥ ሰጠመች።



ተመሳሳይ ክብደት እና መጠን ያላት ሌላ አይጥ ደግሞ በዚሁ የባልዲ ውሃና ጨለማ ክፍል ውስጥ እንድትቀመጥ ተደረገ። አሁን ግን፣ ትንሽ የብርሃን ጨረር እንዲገባ ተደረገ። ሁለተኛዋ አይጥ ከመስጠሟ በፊት ሦስት ቀን ያህል በመዋኘት ለመቆየት ቻለች። በሁለቱ አይጦች መካከል ያለው ልዩነት ምንድር ነው?

ሁለተኛዋ አይጥ ያየችው ትንሽ የብርሃን ጭላንጭል እጅግ ብዙ ተስፋ ሰጣት። የመኖር ተስፋ ሳታቋርጥ እንድትዋኝ አደረጋት። ይህ አስደናቂ ታሪክ ተስፋ እንዴት የሰውን ልጅ ተአምራቱን እስኪቀበል ሊያኖረው እንደሚችል ያሳያል።

ስለ ተስፋ እንብዛም አናወራም፣ ግን ያለ ተስፋ እምነት ሊኖር አይችልም። እምነት ተስፋ ስለ ምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ ነው። ሰዎች በስብከት አማካይነት ተስፋን ሲቀበሉ። እምነት ይገነባል።

## 4. ስብከት ሕይወት ያድናል

> በእግዚአብሔር ጥበብ ምክንያት ዓለም እግዚአብሔርን በጥበብዋ ስላላወቀች በስብከት ሞኝነት የሚያምኑትን ሊያድን የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ሆኖአልና።
>
> 1ኛ ቆሮንቶስ 1፡21

እግዚአብሔር ሰዎች በስብከት ሞኝነት ይድኑ ዘንድ መርጧል። ስብከት ሕይወት ያድናል።

## የዮናስ ቅባት

በመጨረሻው ዘመን፣ ሰባኪው የዮናስ ቅባት በሰዎች ላይ ይለቀቃል። የዮናስ ቅባት ልባቸው የደነደነ ኃጢአተኞችን ወደ እግዚአብሔር መንገድ ለመመለስ ብቃት ነበረው። ነነዌ የክፉ ሰዎች ከተማ ነበረች እናም ዮናስ በመጀመሪያ በዚያ ለመስበክ ፈርቶ ነበር። በኋላ ግን ከተማው በሙሉ በዮናስ ስብከት ተለወጠ። ዮናስ አንዳችም ተአምራት አላደረገም።

ማንንም በመንፈስ አልገደለም ወይም እንግዳ የሆነ የመንፈስ መገለጥ አልነበረውም ይሁን እንጂ፣ ከተማውን በሙሉ መለወጥ የቻለ ጠንካራ የስብከት ቅባት ነበረው፡፡

የስብከት ቅባት በሕይወትህ ላይ ሲመጣ አያለሁ! ለሺህዎች ትሰብካለህ! ስብከትህን ሲሰሙ የሰዎች ልብ ይለወጣል፡፡ ሰዎች ወደ ስብከት አገልግሎትህ ሲመጡ ይድናሉ፡፡ የዘፍጥረት መጽሐፍ ሰዎች ከአሁኑ ዘመን ይልቅ እጅግ ብዙ ዘመን ይኖሩ እንደነበር ያሳየናል፡፡

> **ሄኖክም የኖረበት ዘመን ሁሉ ሦስት መቶ ስድሳ አምስት ዓመት ሆነ፡፡**
>
> **ዘፍጥረት 5:23**

> **ማቱሳላም የኖረበት ዘመን ሁሉ ዘጠኝ መቶ ስድሳ ዘጠኝ ዓመት ሆነ ሞተም፡፡**
>
> **ዘፍጥረት 5:27**

> **ላሜሕ የኖረበት ዘመን ሁሉ ሰባት መቶ ሰባ ሰባት ዓመት ሆነ ሞተም፡፡**
>
> **ዘፍጥረት 5:31**

ኃጢአት በጨመረ መጠን፣ ሕይወት እያጠረ ይመጣል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ሕይወትን እንዴት በመቶዎች ከሚቆጠሩ ዕድሜ ወደ መቶ ሃያ ዓመት እንዳሳጠረ በግልጽ ይናገራል፡፡

> **እግዚአብሔርም፦ መንፈሴ በሰው ላይ ለዘላለም አይኖርም፤ እርሱ ሥጋ ነውና ዘመኖቹም መቶ ሃያ ዓመት ይሆናሉ አለ፡፡**
>
> **ዘፍጥረት 6:3**

እንዲያውም ሕይወት ይባስ ብሎ ከመቶ ሃያ ወደ ሰባ ያጠረ ይመስላል፡፡



> **የዕድሜአችን ዘመን ሰባ ዓመት፣ ቢበዛም ሰማንያ ነው፤ ከዚያ በላይ ከሆነም ድካምና መከራ ብቻ ነው፤ ቶሎ ያልፋልና፤ እኛም ወዲያው እንነጕዳለን፡፡**
>
> **መዝሙር 90:10**
>
> **(አዲሱ መደበኛ ትርጉም)**

የቀድሞው ትውልድ 'አራት መቶኛ' የልደት በዓላቸውን ያከብሩ ነበር፡፡ በመቶ ሃምሳ ዓመታቸው ልጅ ይወልዱ ነበር፡፡ በዛሬው ዘመን አንድ ሰው ሰማኒያ ዓመት ሲሞላው ከልክ በላይ እንደሰታለን፡፡ አንድ ሰው አርባ ዓመት ሲሞላው ትልቅ ሰው ይመስላል፡፡ ለምንድር ነው ሰውነታችን እንዲህ በቶሎ የሚደክመው?

> **እንዲህም ሆነ ሰዎች በምድር ላይ መብዛት በጀመሩ ጊዜ ሴቶች ልጆች ተወለዱላቸው፤ የእግዚአብሔር ልጆችም የሰውን ሴቶች ልጆች መልካሞች እንደ ሆኑ አዩ ከመረጡአቸውም ሁሉ ሚስቶችን ለራሳቸው ወሰዱ፡፡ እግዚአብሔርም፦ መንፈሴ በሰው ላይ ለዘላለም አይኖርም፤ እርሱ ሥጋ ነውና ዘመኖቹም መቶ ሃያ ዓመት ይሆናሉ አለ፡፡**
>
> **ዘፍጥረት 6:1-3**

ከእግዚአብሔር ልጆች ጋር በተደረገ ዝሙት ምክንያት ዘጠኝ መቶ ዓመት ወደ አንድ መቶ ሃያ ተቀነሰ! ዝሙት የሰዎችን ዕድሜ በስምንት መቶ ዓመት ቀነሰ፡፡ በዝሙት ምክንያት 90% የሚሆነው ሕይወታቸው ተወሰደ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ፣ "ኃጢአት ከተፈጸመ በኋላ ሞትን ያመጣል" ሲል ይናገራል፡፡ አስበው በዝሙት ምክንያት ስምንት መቶ ዓመት ተቀነሰ፡፡ ኃጢአት ምን ያህል ሕይወታችንን እንደሚያሳጥር ታያለህ?

እንደምታየው፣ ችግሩ መንፈሳዊ እንጂ ሥጋዊ አይደለም፡፡ ለዚያ ነው ሥጋዊ መድኃኒት ለሰው ልጅ መፍትሔ ሊሆን ያልቻለው፡፡ የኃጢአት ችግር ነው፡፡፡ መፍትሔው የተሰቀለውን ክርስቶስ ኢየሱስን መስበክ ነው፡፡

“ኃጢአት ሲፈጸም”፣ የሞት ወኪሎች እነርሱም፡፡ የልብ ሕመም፣ የሳንባ ሕመም፣ ካንሰር፣ ሲክል ሴል ሕመም፣ የቆዳ በሽታዎች ኤች.አይ.ቪ፣ ዕጢ፣ አደጋ፣ ጦርነት፣ የኩላሊት ሥራ ማቆም ሞታችንን ያስናዳሉ፡- ወይ ኩላሊት ሥራውን እንዲያቆም በማድረግ ወይም በመኪና አደጋ፡፡ እያንዳንዱ ሰው የሞት ፍርዱን የሚቀበልበት የተለያየ መንገድ አለው፡፡

ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም ሲመጣ፣ ውስብስብ የሆኑ ችግሮችን እንደሚጋፈጥ ያውቅ ነበር፡፡ ለዚያ ነው እንዲያው ዝም ብሎ ሁሉንም ያልፈወሰው፡፡ ችግሩ ጥልቅ እንደነበር ያውቅ ነበር፡፡

ለምን አንዳንድ ሕመሞች በእያንዳንዱ ሰዎች ላይ እንደተጣበቁ ያውቅ ነበር፡፡ ጉዳዩ የመታመም ጉዳይ ብቻ አልነበረም፡፡ ከዚያ የበለጠ ነገር እንዳለ ያውቅ ነበር!

ጌታ ሁኔታችንን ሲመለከት፣ ከሁሉ በላይ ሊረዳን የሚችልበትን መንገድ አሰበ፣ ሕይወታችንን ሊያረዝም የሚችለውን የተሻለ መንገድ፡፡ እግዚአብሔር በሕግ ከታሰርንባቸው ነገሮች፤ ሊያድነን የሚችለውን የተሸለ መንገድ ዐቀደ ለዚያ ነው ሊሰብክ፣ ሊያስተምር እና ሊፈውስ የመጣው፡፡ እግዚአብሔር ሰዎችን ያድን ዘንድ የስብከት ሞኝነትን መረጠ፡፡

ስብከት እና ማስተማር ችግሮችህን ይፈታሉ፡፡ ከሁሉ በፊት፣ መንፈስህ ድኗል፡፡ ወደ ሲኦል መውረድ የለብህም፡፡ እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን! በስብከት ኃይል፣ ነፍስህ ከዘላለም ፍርድ ትድናለች፡፡

ስብከት ነፍስህን በኃይለኛ ሁኔታ ሲያድን፣ ሌላውም የሕይወትህ ክፍል ላይም አዎንታዊ ተጽዕኖ ያመጣል፡፡ ነፍስህ ስትበለጽግ፣ በዚህ ደህንነት በጤንነትህም ላይ አዎንታዊ ተፅዕኖ ያመጣል፡፡ ከነፍስህ ደህነት በኋላ የገንዘብህ ሁኔታም ለውጥ ያመጣል፡፡ የእግዚአብሔር ቃል ችግሮችህን ሁሉ ከውስጥ መፈወስና መፍታት ይጀምራል፡፡



**ወዳጅ ሆይ፣ ነፍስህ እንደሚከናወን፣ በነገርህ ሁሉ እንዲከናወንልህና ጤና እንዲኖርህ እጸልያለሁ፡፡**

**3ኛ ዮሐንስ 2**

በተፈጥሮአዊ አስተሳሰብ፣ አንድ ሰው ዝሙትን ለማቆም ቢወስን፣ በኤች.አይ.ቪ የመበከሉን ዕድል እንደሚቀንስና ብሎም የመሞትን ዕድል እንደሚያጠብ መገንዘብ ትችላለህ፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል ስትሰማ፣ እናም የተለያዩ ሰዎችን ከማሳደድ ይልቅ ለማግባት ስትወስን፣ ለብዙ በሽታዎች የመጋለጥ ዕድልህን ትቀንሳለህ፡፡ ስብከትና ትምህርት ልንገምተው ከምንችለው በላይ በብዙ መንገድ ሕይወታችንን ያድናል፡፡

ከእግዚአብሔር ቃል የተነሣ፣ ማጨስና መጠጣት እናቆማለን፡፡ ይህ ሕይወታችንን ወዲያውኑ በብዙ ዓመታት ይጨምራል፡፡ እንደ እግዚአብሔር ቃል ስትኖር እንደ ካንሰር፣ የልብ በሽታ፣ ኤች አይ ቪ፣ ጎኖሪያ እና ጭንቀት ከመሳሰሉት አደጋዎች ሁሉ በጣም የራቅህ ትሆናለህ፡፡

የስብከት ካሴት ሕይወትህን ሊያድን ይችላል፡፡ የስብከት ካሴቶችን በማድመጥ አምናለሁ፡፡ ከስብከት ካሴት ያገኘኸው ቃል “ላገኙት ሕይወት፣ ለሥጋቸውም ሁሉ ፈውስ” እንደሆነ ትገነዘባለህ፡፡

**ልጄ ሆይ፤ ንግግሬን አድምጥ . . . ለሚያገኙአት ሕይወት፤ ለሥጋቸውም ሁሉ ፈውስ ነውና፡፡**

**ምሳሌ 4፡20,22**

ራስህን ለስብከት ስጥ እናም ለብዙ በረከቶች ትቀበላለህ፡፡ ኢየሱስ የመጣው ሊሰብክና ሊያስተምር ነው፡፡

**ቃሉን ላከ ፈወሳቸውም፤ ከጥፋታቸውም አዳናቸው፡፡**

**መዝሙር 107፡20**

ፈውሶች ምልክት ብቻ ነበሩ። ሰዎች ለምልክት ብቻ ሲመጡ ክፉዎች ናችሁ ይላቸው ነበር። ስብከቱን ሳንወድ ምልክቶችንና ድንቆችን ብቻ መውደድ መጥፎ ነገር እንደሆነ አስተምሮናል።

> እርሱ ግን መልሶ እንዲህ አላቸው፡፡ ክፉና አመንዝራ ትውልድ ምልክት ይሻል፤ ከነቢዩም ከዮናስ ምልክት በቀር ምልክት አይሰጠውም፡፡
>
> ማቴዎስ 12፥39

ስብከት ቤተ ክርስቲያናትን ይጀምራል! እግዚአብሔር ብዙ ሰባኪዎችን ይፈልጋል! ስብከት እና ትምህርት ትዳርህን ይፈውሳል። የጸብን አዝማሚያ በመቀነስ፡- ሰላምን ያመጣል። ስብከት ፍቺን ይከላከላል። ስብከት ሕይወትን ይለውጣል!

> *ከዚህም ሁሉ በላይ፣ ልጄ ሆይ፣ ተግሣጽን ስማ ብዙ መጻሕፍትን መጻፍ ፍጻሜ የለውም፡፡*



## ምዕራፍ 8

# ማስተማር ኃያል ነገር የሆነው ለምንድር ነው

አንድ ቀን ኢየሱስ በመቅደስ ውስጥ ሲያስተምር አጋንንቱ "እባክህ ተወን" ብሎ ጮኸ። ቃሉ ኃያል ነው አጋንንቶችን በቀጥታ ያጠቃል።

> ወደ ቅፍርናሆምም ገቡ ወዲያውም በሰንበት ወደ ምኩራብ ገብቶ አስተማረ፡፡ እንደ ባለሥልጣን ያስተምራቸው ነበር እንጂ እንደ ጻፎች አይደለምና በትምህርቱ ተገረሙ፡፡ በዚያን ጊዜም በምኩራባቸው ርኩስ መንፈስ ያለው ሰው ነበር እርሱም፡- የናዝሬቱ ኢየሱስ ሆይ፣ ከአንተ ጋር ምን አለን? ልታጠፋን መጣህን? ማን እንደ ሆንህ አውቄአለሁ የእግዚአብሔር ቅዱስ ብሎ ጮኸ፡፡
>
> ማርቆስ 1፥ 21-24

ራስህን ቃሉን ለመማር ካዘጋጀህ ለሕይወትህ ፈውስን ያመጣልሃል። ኢየሱስ ያደረገው ማስተማር ብቻ አልነበረም። ሰዎች ሲሰሙት ከመጡ በኋላ፣ ከበሽታዎቻቸው ፈወሳቸው።

> ወሬው ግን አብዝቶ ወጣ፤ ብዙ ሕዝብም ሲሰሙትና ከደዌአቸው ሲፈወሱ ይሰበሰቡ ነበር፤
>
> ሉቃስ 5፥15

በወንጌል ውስጥ ሕዝቡ ሲያስተምር ሊሰሙት እንደመጡ የሚገልጹ ብዙ ቦታዎች አሉ። እግዚአብሔር ኃይለኛ አስተማሪ አድርጎ የሚያስነሣህ

ምክንያት የብዙ ሰዎች ሕይወት ላይ ተጽዕኖ እንድታመጣ ነው፡፡ እግዚአብሄር ኃይለኛ ሰባኪ እና አስተማሪ አድርጎ ያስነሳሃል፡፡

> ከእነርሱም ጋር ወርዶ በተስተካከለ ስፍራ ቆመ፤ ከደቀ መዛሙርቱም ወገን ብዙ ሕዝብ ነበር፤ ደግሞም ሊሰሙትና ከደዌአቸው ሊፈወሱ ከይሁዳ ሁሉ ከኢየሩሳሌምም ከጢሮስና ከሲዶና ባሕር ዳርም የመጡ ብዙ ሰዎች ነበሩ፤
>
> ሉቃስ 6፡17

ኢየሱስ ሁልጊዜ በፈውስ ከማገልገሉ በፊት ቃሉን ያስተምር ነበር፡፡ ቃሉን ካስተማረ በኋላ፣ የታመሙትን ይፈውስ ነበር፡፡ ይህንን የሚያደርግበት ምክንያት የእግዚአብሔር ቃል የሕመምህን ሥር ስለሚያጠቃ ነው፡፡ እግዚአብሔር የጉስቁልናህን ሥር ያገኘዋል፡፡ ሰዎች ለቃሉ የተጋለጡ ሲሆኑ፣ ሁልጊዜ ፈውስ ይመጣል፡፡

> ልጄ ሆይ፤ ንግግሬን አድምጥ ወደ ቃሌም ጆሮህን አዘንብል፡፡ ለሚያገኙአት ሕይወት፤ ለሥጋቸውም በሥጋቸውም ሁሉ ፈውስ ነውና፡፡
>
> ምሳሌ 4፡20፤22

ኢየሱስ እንዲህ አለ፣ "እኔ የነገርኳችሁ ቃል፣ መንፈስ ነው ሕይወትም ነው"፣ (ዮሐንስ 6፡63)፡፡ ቃሉን ስትሰማ ሕይወት ወደ አንተ ይመጣል፡፡ እግዚአብሔር የተባረከ ይሁን! በቃሉ ትምህርት ውስጥ፣ መንፈስህ ሕያው ይሆናል፡፡ ራስህን ለቃሉ ትምህርት መስጠትህን መቀጠል በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

በስብከትም ሆነ በትምህርት ውስጥ፣ ቃሉ እንደሚፈውሰንና እንደሚያድነን እንገነዘባለን፡፡

በስብከት እና በትምህርት መካከል ያለው ልዩነት ምንድር ነው?



## በስብከት እና በማስተማር መካከል ያሉ ልዩነቶች

ሀ. በስብከት አማካኝነት ቃሉ ወደ እኛ ሲመጣ፣ ነፍሳችን ትገለገላለች፡፡

ለ. ቃሉ በትምህርት ሲመጣ፣ ባብዛኛው ተቀባይ የሚሆነው አዕምሮአችን ነው፡፡

ሐ. ትምህርት ከስብከት ይልቅ ዘለቄታዊ ውጤት አለው፡፡

መ. አንዳንድ ጊዜ ትምህርትን ለመያዝ ያስቸግራል፡፡ ስብከት ቶሎ ይገባል ግን ቶሎ ይደበዝዛል፡፡

ሠ. ስብከት ስሜትን የሚነካ እና የሚያነቃንቅ ነው፡፡

ረ. ስብከት ከትምህርት ይልቅ፣ ላይ ላዩን የሚስብ ነው፡፡

ሰ. ትምህርት የስብከትን ያህል ታዋቂነት የለውም፡፡ ስብከትን በግራ ትምህርትን ደግሞ በቀኝ ባስቀምጥ፣ ብዙ ሰዎች ስብከትን ይመርጣሉ፡፡

ሸ. ብዙ ሰዎች ሰባኪ ከአስተማሪ ይልቅ ኃይለኛ የእግዚአብሔር ሰው እንደሆነ አድርገው ያስባሉ፡፡ ሕዝብ የድጋፍ ድምፅ እንዲሰጥ ቢጠየቅ፣ ይበልጥ የሚስበው ሰባኪ ስለሆነ ሰባኪውን ይመርጣል፡፡

ቀ. አስተማሪዎች ብዙውን ጊዜ ቤተ ክርስቲያናቸው ቀስ እያለ የሚያድግ ነው፡፡ ይህ የሚሆንበት ምክንያት በመልክ በመልኩ እና ደረጃ በደረጃ የሚሰጥ ስለሆነ ነው፡፡ ቤት ስትገነባ፣ ጡቦቹ መልክ ያለውና ዘላቂ የሆነ ቤት እስኪወጣቸው ድረስ በዘዴ ይደራደራሉ፡፡

## የማስተማር ሦስት ቀጥተኛ ውጤቶች

### 1. ቃሉን ማስተማር ብርሃን ያመጣል

አጋንንቶች የሚኖሩት በጨለማ ውስጥ ነው፡፡ የጭንቀት፣ ያለ ዕድሜ ሞት እና የጉስቁልና አጋንንቶች የሚኖሩት በጨለማ ውስጥ ነው፡፡ ትዕቢትም የጨለማ ዓይነት ነው፡፡ ለዚያ ነው ትዕቢት ባለበት ክፉ መንፈስ የሚኖረው፡፡ እግዚአብሔር ይባረክ፡፡ ቃሉ ብርሃን ነው፡፡

ሕግህ ለእግሬ መብራት፣ ለመንገዴ ብርሃን ነው።

መዝሙር 119፡105

የቃሉ ትምህርት ሲሰጥ፣ ብርሃን በልባችን ላይ ይመጣል። በጨለማ የሚኖሩ አጋንንቶች፣ እንዲሸሹ ይገደዳሉ። የቃሉ ትምህርት ሲሰጥ፣ መንፈሳዊ ብርሃን ይበራል (ስፍራውን ይወርሳል)። ለዚያ ነው ትምህርት ሲሰጥ ሰዎች ሊፈወሱ የሚችሉት። የቃሉ ትምህርት ሲሰጥ፣ ሕይወትህ ይለወጣል። ሰይጣን ይህን ያውቃል እናም ለዚህ ነው ትምህርትን እንዳትሰማ የሚፈልገው።

ለዚያ ነው የስብከት ካሴት እንዳይኖርህ የሚፈልገው። የስብከት ካሴት ሕይወትህን ለዘላለም ሊለውጥ ይችላል፤ አንድ የስብከት ካሴት ወደ መንግሥተ ሰማያት ሊያስገባህ ይችላል! አንድ የስብከት ካሴት ወደ መጋቢነት ሊለውጥህ ይችላል! አንድ የስብከት ካሴት ከፈትነት ወደ ደስተኛ ባለትዳርነት ሊለውጥህ ይችላል! የስብከት ካሴት መረጋጋትን ሊሰጥህ ይችላል፣ ከእብደት ወደ አዕምሮህ በመመለስ ጤንነትን ሊሰጥህ ይችላል። ሰይጣን ትምህርትን ከሚሰጠው ብርሃን የተነሣ ይጠላዋል።

ከዓመታት በፊት፣ በኮሬል ቡ የሕክምና ትምህርት ቤት ሆስፒታል ውስጥ የሕክምና አገልግሎቴን በመስጠት ላይ እያለሁ፣ የምኖረው በዚያ ከሚገኙት ሆስቴሎች በአንዱ ውስጥ ነበር። በዚያን ወቅት ማደሪያ ክፍሌ በአይጦች የተሞላበት ጊዜ ነበር።

በየምሽቱ ወደ ክፍሌ ስገባ፣ ልክ መብራቱን ድንገት ሳበራ፣ እነኚህ አይጦች በኮርኒሱ ጥግ ወደሚገኝ አንድ ጉድጓድ ለመግባት ይሽቀዳደማሉ። አይጦችን ስለምጠላ(ያውም እነኚህ ትላልቆች ናቸው) ወገቤ ይንቀጠቀጣል። እነኚህ አይጦች እኔ በማልኖርበት እና መብራቱ በሚጠፋበት ጊዜ በመስክ ላይ የመቧረቂያ ጊዜአቸው ይሆናል። ግን ልክ መብራቱን በማበራበት ጊዜ፣ እንደተጋለጡ ይሰማቸውና ይሸሻሉ።



የቃሉ ብርሃን ወደ ሕይወታችን በሚመጣበትም ጊዜ ልክ እንደዚሁ ነው። አጋንንቶች ስለሚጋለጡ ለመሸሽ ይገደዳሉ። ልክ እንደዚህ ነው የእግዚአብሔር ቃል የሚሠራው። ቃሉ በሕይወታችን ውስጥ ባለው ጨለማ ውስጥ ባሉትና በገቡት አጋንንቶች ላይ ብርሃኑን ይፈነጥቃል!

የእግዚአብሔር ቃል ብርሃን ከሕይወትህ ውስጥ ሲጠፋ(ወደ ቤተ ክርስቲያን ካልሄድህ፣ ወይም ቃሉ በሕይወትህ ውስጥ ካላኖርህ) አጋንንቶች ወረራ ሊያካሂዱብህ ነፃ ይሆናሉ። አጋንንቶች በሰዎች ውስጥ ጨለማን ይፈልጋሉ። የይቅር አለማለት፣ የመራርነት፣ የጥላቻ፣ የመጎምጀት፣ የመዋሸት፣ የትዕቢት፣ ያለመታዘዝ፣ የኃጢአት ወይም የቁጣን ጨለማ ይፈልጋሉ። ለዚያ ነው መጽሐፍ ቅዱስ ለሰይጣን ስፍራ እንዳንሰጥ የሚመክረን። የእነኚህ ጨለማዎች መኖር ለአጋንንቶች እንቅስቃሴና ሥራ በር ይከፍታል።

ለዲያብሎስም ፈንታ አትስጡት።

ኤፌሶን 4፡27

የቃሉን ብርሃን ስትለብስ ከሰይጣን አሠራር ነፃ ትሆናለህ።

## 2. የቃሉ ትምህርት በሥራ ላይ ያለ ሰይፍ ነው

. . . የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው

ኤፌሶን 6፡17

የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና፣ የሚሠራም፣ ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው፤

ዕብራውያን 4፡12

ማስተማር ኃያል ነው። አጋንንትን፣ የአእምሮ በሽታዎችን፣ ዕውርነትን፣ ርኩሰትን፣ ትዕቢትን፣ ድንቁርናን፣ መጎምጀትን፣ መንፈሳዊ ችግሮችንና ድህነትን ያባርራል።

አጋንንቶች በቃሉ ሰይፍ መጎዳት ስለማይፈልጉ ትምህርቱን ወደ ውስጥህ እንዳታስገባ የሚቻላቸውን ሁሉ ያደርጋሉ። ለዚያ ነው አንዳንድ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ትምህርቱን እንዳትሰማ እንድትተኛ የሚያደርጉህ። ከፊውስ በፊት መስማት ይቀድማል!

. . . ደግሞም ሊሰሙትና ከደዌአቸው ሊፈወሱ . . . የመጡ ብዙ ሰዎች ነበሩ

ሉቃስ 6፡17

### 3. ቃሉን ማስተማር ዘርን መዝራት ነው

ዘሪው ቃሉን ይዘራል።

ማርቆስ 4፡14

ቃሉን ስትሰማ ዘሩ ይዘራል። ሰባኪው፣ "ትባረካላችሁ ትበለጽጉማላችሁ"፣ ሲል ብትሰማ፣ በሕይወትህ ውስጥ ዘሩ ይዘራል። አስተማሪ ቃላት፣ የሚያድጉና ታላቅ ዛፍ የሚሆኑ፣ ዘሮች ናቸው።

በቤተ ክርስቲያኔ ውስጥ ያሉ ብዙ ሰዎች መጋቢ መሆን የሚፈልጉት ከዘራሁት ዘር የተነሣ ነው። የዘራኸውን ያንኑ ታጭዳለህ። እንዲሁ በሕይወታችን እንኳ ስለ ልጆቻችን የምንናገራቸው ነገሮች እያደጉ ሲሄዱ በሕይወታቸው ውስጥ ይፈጸማል። ልጅህን መልአክ እያልክ ስትጠራ ማራኪ መንፈስ ያለው በመሆን ያድጋል ተቃራኒውን ካልክም እንደዚያው።

ጉባዔህን ሁልጊዜ መልካም ይሆንላችኋል ስትላቸውና ጌታ ጠባቂያቸውና የቀኛቸውም ጥላ እንደሆነ ስትነግራቸው፣ እነኚህ ተስፋዎች ይፈጸማሉ። እግዚአብሔር ረዳትህ ነው፣ በሕይወት ትኖራለህ አትሞትም፣ መልካምም ይሆንልሃል። አይኖረኝም ብለህ ያሰብከው ልጅ ይኖርሃል!

*ከዚህም ሁሉ በላይ፣ ልጅ ሆይ፣ ተግሣጽን ስማ ብዙ መጻሕፍትን መጻፍ ፍጻሜ የለውም።*



*ምዕራፍ 9*

# ቤተ ክርስቲያን መትከል እና የድንኳን አገልግሎት

ቤተ ክርስቲያን የመትከል አንዱ ታላቅ ቁልፍ የድንኳን አገልግሎት ነው። የድንኳን አገልግሎት መጋቢዎች እና ወንጌላዊያን ለሚሰጡት አገልግሎት ያለ ክፍያ የሚደክሙበት መሥዕዋትነት ነው። የሥራው ከፍተኛነት፣ በድንኳን አገልግሎት ካልታገዘ፣ ሊተከሉ የሚችሉ ቤተ ክርስቲያናት በጣም ጥቂት ብቻ ይሆናሉ።

ብዙ አገልግሎቶች ካለባቸው ከፍተኛ ወጪ የተነሳ ባሉበት ለመቆም ተገደዋል። በአጠቃላይ ቤተ ክርስቲያን ለእግዚአብሔር ሥራ የሚያስፈልጉ ሰዎችን ሁሉ መቅጠር ፈጽሞ **አትችልም**።

የድንኳን ወይም የትርፍ ጊዜ አገልግሎት በአንዳንድ አካባቢዎች እምብዛም አይታወቅም። በአንዳንድ ባሕሎች ሁሉም ሰው ለሚሰጠው አገልግሎት ሁሉ ሊከፈለው ይገባል። ኦርጋን ተጫዋቹ ሊከፈለው ይገባዋል! ጊታር ተጫዋቹ ሊከፈለው ይገባዋል! የድምፅ መሣሪያ ተቆጣጣሪው ሊከፈለው ይገባዋል መጋቢውም ለሚሰጠው አገልግሎት ሁል ጊዜ ከፍተኛ ደሞዝ ይፈልጋል።

ውድ ወዳጄ፣ አብዛኛው የደረሰ መከር ያለው በዓለም ድሃ አካባቢዎች ነው። እንዴት የዓለም ድሃ ሕዝቦችን በጉስቁልናቸው ውስጥ መድረስ

ይቻላል? አብዛኞቹ እነኚህ ሕዝቦች መጋቢዎች እና ወንጌላዊያን ለሚሰጡት መልካም አገልግሎት መክፈል አይችሉም። ቤተ ክርስቲያን የመትከል ሥራ ቀጣይነት እንዲኖረው የማይከፈላቸው መጋቢዎችና ወንጌላዊያን አገልግሎት ወሳኝ ነው።

የክርስትና የመሥዕዋትነት ተፈጥሮ ሲመቻመች ቤተ ክርስቲያን የመትከል ሥራ ይስተጓጎላል። ቤተ ክርስቲያን የተወለደችው በክርስቶስ መሥዋዕትነት ነበር። ቤተ ክርስቲያን ያደገችው በሐዋርያዊ መሥዕዋትነት ነው። አሁንም እንደገና፣ ቤተ ክርስቲያን የምታድገው በመሥዕዋትነት ብቻ ነው። በሚቀጥሉት ሁለት ምዕራፎች ውስጥ፣ ስለ ድንኳን አገልግሎት አካፍልሃለሁ። እኔን በተመለከተ፣ የቤተ ክርስቲያን ተከላ በሰፊው ማካሄድ የሚቻለው በድንኳን አገልግሎት ብቻ ነው።

## ስለ ድንኳን አገልግሎት ልታውቅ የሚገባህ ሰባት ነገሮች

ጳውሎስ አቴንስን ለቆ ወደ ቆሮንቶስ ሄደ፣ በዚያም የጳንጦስ ተወላጅ የሆነውን፣ አቂላ የተባለውን አይሁዳዊ አገኘ። ከዚህም ትንሽ ቀደም ብሎ፣ አይሁድ ሁሉ ከሮም እንዲወጡ ቀላውዴዎስ ባዘዘው መሠረት ከሚስቱ ከጵርስቅላ ጋር በቅርብ ጊዜ ከኢጣሊያ የመጣ ነበር። ጳውሎስም ሊያያቸው ወደ እነርሱ ሄደ፣ ድንኳን ሰፊዎች እንደነበሩ አወቀ። **ጳውሎስም ድንኳን ሰፊ ነበር።** ከእነርሱ ጋር ተቀምጦ አንድ ላይ መሥራት ጀመረ

> **በየሰንበቱም ከአይሁድና ከግሪክ ሰዎች ጋር በምኩራብ ውስጥ እየተነጋገረ ሲያሳምናቸው ይኖር ነበር።**
>
> የሐዋርያት ሥራ 18:4
> (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

1. በእርግጥ የድንኳን አገልግሎት የትርፍ ጊዜ አገልግሎት ነው። የድንኳን አገልግሎት ዓለማዊ ሥራን ከእውነተኛ አገልግሎት ጋር



አጣምሮ የመሥራት ችሎታ ነው። የዚህ አገልግሎት ጥሩ ምሳሌ የጳውሎስ አገልግሎት ነበር። የድንኳን አገልግሎት ተብሎ የተጠራበትም ምክንያት ጳውሎስ ድንኳን ሰፊ ስለነበር ነው።

2. ዓለማዊ ሥራን ከአገልግሎት ጋር ማጣመር ይቻላል። ይህ አገልግሎት ራስህን እየረዳህ የምታገለግልበት ነው። ምናልባት እንዲህ ብለህ ትጠይቅ ይሆናል፣ "እግዚአብሔር አገልግሎት እንዲህ እንዲሆን ይፈልጋል?" "መጽሐፍ ቅዱስ ወንጌልን የሚሰብኩ በወንጌል ይኑሩ አይልምን?"

> እንዲሁም ደግሞ ወንጌልን የሚሰብኩ ከወንጌል ቀለብ እንዲቀበሉ ጌታ ደንግጓል።
>
> 1ኛ ቆሮንቶስ 9:14

እኔ የሕክምና ተማሪነትን ከአገልግሎት ጋር አጣምሬአለሁ። የእግዚአብሔር ቃልን ከሙያቸው ጋር ያጣመሩና ስኬታማ የሆኑ ብዙ ሰዎችን አውቃለሁ።

ጳውሎስ ታላቅ የሆነ የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ተካይ ነበር። ራሱን ድንኳን በመሥራት ሥራ እየደገፈ ለጌታ ታላቅ ነገሮችን ማድረግ የቻለ ሰው ነበር። የድንኳን አገልግሎት ዛሬም ቢሆን ቤተ ክርስቲያን ለመትከል ይበልጥ ወሳኝ ነው።

3. በአዲስ ኪዳን የድንኳን አገልግሎት ምርጥ ምሳሌ ሐዋርያው ጳውሎስ ነው። የብሉይ ኪዳን ምርጥ ምሳሌ ደግሞ ነቢዩ ዳንኤል ነው።

ዳንኤል ሦስት ሥራዎች ነበሩት፡

i. የባቢሎን ግዛት ፓርላማ አባል ነበር

> ንጉሡም ዳንኤልን በከፍተኛ ሥልጣን ላይ አስቀመጠው፤ እጅግ ብዙ ስጦታዎችንም ሰጠው፤ የመላው ባቢሎን አውራጃ ገዥ አደረገው፤ በባቢሎን ጠቢባን ሁሉ ላይም አለቃ አድርጎ ሾመው።
>
> ዳንኤል 2:48 (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

ii. የቤልሻዛር ሁለተኛ ምክትል ፕሬዘዳንት ነበር

> ከዚህ በኋላ በቤልሻዛር ትእዛዝ ዳንኤልን ሐምራዊ መጎናጸፊያ አለበሱት፣ የወርቅ ሐብል በዐንገቱ ላይ አጠለቁለት፣ የመንግሥቱም ሦስተኛ ገዥ ሆኖ ተሾመ፡፡
>
> ዳንኤል 5፡29
>
> (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

iii. በዳሪዮስ ዘመን ጠቅላይ ሚኒስትር ነበር

> ዳርዮስ በመንግሥቱ ሁሉ ላይ እንዲገዙ አንድ መቶ ሃያ መሳፍንን መሾም ፈለገ፣ በእነዚህም ላይ ሦስት የበላይ አስተዳዳሪዎችን አደረገ፣ ከእነርሱም አንዱ ዳንኤል ነበረ፡፡ ንጉሡ ጉዳት እንዳይደርስበት፣ መሳፍንቱ ተጠሪነታቸው ለሦስቱ የበላይ አስተዳዳሪዎች እንዲሆኑ ተደረገ፡፡
>
> ዳንኤል 6፡1-2
>
> (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

4. አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔር ፈቃድ የድንኳን አገልጋይ እንድትሆን ሲሆን አንዳንድ ጊዜ ደግሞ እግዚአብሔር የሙሉ ጊዜ አገልጋይ እንድትሆን ይፈልጋል፡፡ በአንድ ወቅት ሙሉ በሙሉ በአገልግሎቱ መደገፍ አስፈላጊ ሲሆን በሌላ ጊዜ ደግሞ ራስህን በራስህ መደገፍ ይኖርብሃል፡፡ ሁልጊዜ የመንፈስ ቅዱስ ምሪት መከተል በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ትክክለኛው ነገር ስህተት(አኖሚያ) ሊሆን መቻሉ አይደነቅም፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር ብኋልና?

ጳውሎስ እንዲጠግብም እንዲራብም በጌታ መታዘዙን ይናገራል፡፡

> መዋረድንም አውቃለሁ መብዛትንም አውቃለሁ፡፡ በእያንዳንዱ ነገር በነገርም ሁሉ መጥገብንም መራብንም መብዛትንና መጉደልን ተምሬአለሁ፡፡
>
> ፊልጵስዩስ 4፡12

5. በመጨረሻው ዘመን የድንኳን አገልግሎት ዋነኛ አገልግሎት ይሆናል፡፡ የጳውሎስ አገልግሎት ዛሬም ሕያው ነው፡፡ አንዳንድ ሰዎች አገልግሎትን ሊደግፉ የሚችሉበት የተሻለ መንገድ እንደ ጳውሎስ



በመሆን ነው፡- በሳምንቱ የሥራ ቀናት ሥራ መስራት እና 'በየሰንበቱም ሁሉ በምኩራቡ አይሁድን ማስረዳት፡፡'

> እርሱም እንደ እነርሱ ድንኳን ሰፊ ስለነበረ፣ ከእነርሱ ጋር ተቀምጦ በተመሳሳይ ሥራ ተሰማራ፡፡ በየሰንበቱም ከአይሁድና ከግሪክ ሰዎች ጋር
> በምኩራብ ውስጥ እየተነጋገረ ሊያሳምናቸው ይጥር ነበር፡፡
>
> የሐዋሪያት ሥራ 18፡3-4
>
> (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

6. ጳውሎስ የድንኳን አገልግሎትን የተለማመደው ሌሎች የርሱን መልካም ምሳሌ እንዲከተሉ ነው፡፡

> "አሁንም ለእግዚአብሔር፣ እንዲሁም ሊያንጻችሁና በቅዱሳት ሁሉ መካከል ርስት ሊያወርሳችሁ ለሚችለው ለጸጋው ቃል አደራ እሰጣችኋለሁ፡፡ የማንንም ብር ወይም ወርቅ ወይም ልብስ አልተመኘሁም፣ እነዚህ እጆቼ ለእኔና ከኔ ጋር ላሉት በሚያስፈልገን ነገር እንዳገለገሉን እናንተ ራሳችሁ ታውቃላችሁ፡፡ በጉልበታችን ደከምን ችግረኞችን መርዳት እንዳለብን ባደረግሁት ሁሉ አሳይቻችኋለሁ፣ 'ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብፁዕ ነው' ያለውን የጌታ የኢየሱስን ቃል እናስታውስ፡፡" ይህን ካለ በኋላ፣ ተንበርክኮ ከሁሉም ጋር ጸለየ፡፡
>
> የሐዋሪያት ሥራ 20፡32-36
>
> (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

> የእኛን ምሳሌ እንዴት መከተል እንደሚገባችሁ እናንተ ራሳችሁ ታውቃላችሁና፡፡ ከእናንተ ጋር ለነበርንበት ጊዜ ሥራ ፈቶች አልነበርንም፣ ነገር ግን ከእናንተ በአንዳችሁም ላይ ሸከም እንዳንሆን ሌሊትና ቀን እንደከምና እንሠራ ነበር፤ ይህን ያደረግነው ምሳሌነታችንን እንድትከተሉ ብለን እንጂ የሚያስፈልገንን ነገር ከእናንተ ለማግኘት ሥልጣን ሳይኖረን ቀርቶ አይደለም፡፡
>
> 2ኛ ተሰሎንቄ.3፡7-9

እየተናገርኩ ያለሁት ስለ ፍሬያማ እና ዘለቄታ ስላለው አገልግሎት ነው፡፡ ጳውሎስ ለእግዚአብሔር ምንም የማይሠራ አገልጋይ አልነበረም፡፡

በርግጥ የተቀባ እና ኃይለኛ ቤተ ክርስቲያን ተካይ ነበር፡፡ ይህን መልካም ምሳሌ ለመከተል ለተጠሩ ጊዜው አሁን ነው፡፡

7. የድንኳን አገልግሎት ልክ እንደ ሙሉ ጊዜ አገልግሎት ፍሬያማ ሊሆን ይችላል፡፡ ሐዋሪያው ጳውሎስ ከሌሎች ሐዋሪያት ያንስ ነበር ሊል የሚችል አንድም ሰው አላውቅም፡፡ አብዝቶ ደክሟልም ተጉዟልም፡፡ ከማንም በላይ ብዙ ቤተ ክርስቲያኖችን ተክሏል፡፡ በእውነት ውጤታማ፣ የተቀባ እና ፍሬያማ መጋቢ ነበር፡፡

> *ከዚህም ሁሉ በላይ፣ ልጄ ሆይ፣ ተግሣጽን ስማ ብዙ መጻሕፍትን መጻፍ ፍጻሜ የለውም፡፡*



*ምዕራፍ 10*

# እንዴት እና መቼ ወደ ድንኳን አገልግሎት መግባት እንደሚቻል

## 1. በአንዳንድ አካባቢዎች የአገልግሎት ሥራን ልትፈጽም እና ልትኖር የምትችልበት ብቸኛ መንገድ ሲሆን

ከሁለት መቶ ዓመታት በፊት የወንጌል መልእክተኞች(ሚስዮናዊያን) ከሲውዘርላንድ ወደ ጋና ሲላኩ፣ በተልእኮ መስካቸው ራሳቸውን መርዳት ነበረባቸው፡፡ አብዛኞቹ ገበሬዎች፣ መምህራን ወዘተ ሆኑ፡፡ ለእነኚህ የወንጌል መልእክተኞች በባንክ በኩል ገንዘብ የሚላክበት ምንም መንገድ እንዳልነበረ ግልጽ ነው፡፡ አገልጋዮች በአንዳንድ ቦታዎች ለመኖር ዓለማዊ ሥራ ሕጋዊ መሠረትን እንደሚሰጣቸው መገንዘብ ይኖርባቸዋል፡፡ በአንዳንድ አገሮች ውስጥ ዓለማዊ ሥራ በአገሪቱ ውስጥ ለመኖር ሕጋዊ ስለሚያደርጋቸው ብቻ እየሠሩ የሚኖሩ መጋቢዎች አሉኝ፡፡

ለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ማንኛውንም ነገር ለመስራት ዝግጁ ነን? በባዕድ አገር ለመኖርና ለማገልገል ዓለማዊ ሥራ መሥራት ካለብህ ታደርገዋለህ? ወይስ ያን ማድረግ ይበዛብሃል?

ነቢዩ ዳንኤል እንዴት በባቢሎን የበለጸገ ይመስልሃል? የፓርላማ አባልነቱን ስለጠበቀ ነው፡፡

## 2. የድንኳን አገልግሎት ሸክም ከመሆን ያድንሃል

**ደግሞም የማንንም እንጀራ በነጻ አልበላንም፤ ነገር ግን ከእናንተ በአንዳችሁም ላይ ሸክም እንዳንሆን ሌሊትና ቀን እንደከምና እንሠራ ነበር፤**

**2ኛ ተሰሎንቄ.3፡8**
**(አዲሱ መደበኛ ትርጉም)**

የሙሉ ጊዜ አገልጋይ መሆን በትንሽ ጉባዔ ላይ ሸክም የሚሆንበት ጊዜ አለ። አንዳንድ ጊዜ በጉባዔ ውስጥ ያለ ሰው ሁልጊዜ አንተን መርዳት ስላለበት ሸክም ልትሆንበት ትችላለህ። በአንዳንድ ሰዎች ቤት ውስጥ መቆየት የማልፈልግበት ጊዜ አለ። ይህ የሚሆንበት ምክንያት የእኔ በዚያ መኖር ለተቀበለኝ ሰው ሸክም እንደሆንሁበት ስለሚሰማኝ ነው።

አንድ ቀን ልንሰብክ ወጥተን በጣም አምሽተን ተመለስን። እኩለ ሌሊት አልፎ ነበር። የተቀበለችን ሴት በጣም እንቅልፍ ተጫጭኗትና ደክሟት ከክፍሏ ወጣች።

"እናንተ ሰዎች መጣችሁ? ስንት ሰዓት ሆነ?" በማለት አጉተመተመች ሰዓታችንን ስናይ ለካ ከሌሊቱ ወደ ሰባት ሰዓት ሆኗል። ከዚያም፤ "ምግብ እንድሠራላችሁ ትፈልጋላችሁ?" ብላ ጠየቀችን ለራሴ እንዲህ ብዬ አሰብሁ፤ "በእርግጥ መብላት እፈልጋለሁ። ተርቤአለሁ ቀኑን በሙሉ አልበላሁም።" ግን ውስጤ እያጉረመረመ ሳያስታውቅብኝ መልስ ሰጠሁ።

ተቀባያችንም እንዲህ በማለት ቀጠለች፤ "ማቀዝቀዣ ውስጥ ዓሳ አለ፣ ከበረዶ ቤት አውጥቼ ላበስልላችሁ እችላለሁ።"
እኔ ፀጥ ብዬ ነበር እርሷ ግን ቀጠለችና፣ "ሩዝም አለኝ ላዘጋጅላችሁ እችላለሁ" አለች።
እንደገናም እንዲህ ስትል ጠየቀች፣ "ምግብ እንድሠራላችሁ ትፈልጋላችሁ?"



ለራሴ እንዲህ ብዬ አሰብሁ፣ "አንድ ክርስቲያን ከሌሊቱ ሰባት ሰዓት ሰው ዓሣ ከበረዶ ቤት አውጥቶ ካቆየ በኋላ እንዲያበስልለት እና ሩዝ እንዲቀቅልለት መጠየቅ ይችላል?" ለዚህች ውድ እንግዳ ተቀባያችን ሸክም መሆን እንደሌለብኝ ወሰንሁ።
የህፍረቴን ፈገግ ብዬ፣ "ኦ ምንም አይደል" አልሁ።
ባዶ ሆዴን ወደ መኝታዬ ሄድሁ። በቀላሉ ለተቀበለችን ሴት ሸክም መሆን አልፈለግሁም።

ከዚያ በኋላ በሰዎች ላይ ሸክም ላለመሆን በምጓዝበት ጊዜ በምስጢር ምግብ መያዝ እንዳለብኝ ተማርሁ። ጳውሎስ የሚናገረው ስለዚህ ነበር። አገልግሎቱ በማንም ላይ ሸክም እንዲሆን አይፈልግም ነበር።

## 3. የድንኳን አገልግሎት በቤተ ክርስቲያን ሳይከፈልህ በአገልግሎት ውስጥ እንድትቆይ ያስችልሃል

**ደግሞም የማንንም እንጀራ በነጻ አልበላንም፤ ነገር ግን ከእናንተ በአንዳችሁም ላይ ሸክም እንዳንሆን ሌሊትና ቀን እንደከምና እንሠራ ነበር፤**

**2ኛ ተሰሎንቄ 3፡8**
**(አዲሱ መደበኛ ትርጉም)**

## ለመጋቢዎች መክፈል አገልግሎትን የሚያደናቅፍበት አራት መንገዶች

ሀ. የሕንፃ ፕሮጀክቶች ይጓተታሉ ወይም ይቆማሉ
ለ. ቤተ ክርስቲያን የሚያስፈልጓትን ዕቃዎች መግዛት አትችልም
ሐ. የወንጌል መልእክተኞችን(ሚሲዮናዊያንን) መላክ አይቻልም
መ. ያልበሰሉ የቤተ ክርስቲያን አባላት ለመጋቢዎች የተወሰነ መጠን ያለው ገንዘብ ለምን ሊከፈላቸው እንደሚገባ ስለማይረዱ በአዲስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ችግር ሊፈጥሩ ይችላሉ። አንዳንድ ሰዎች ለእግዚአብሔር የሚሠሩ ሰዎች ሊባረኩ እንደሚገባቸው አያስቡም።

መጋቢዎች ሕይወታቸውን በተቻለ መጠን የግላቸው እንዲያደርጉ እመክራለሁ::

## 4. የድንኳን አገልግሎት ከሰዎች ሁሉ ነፃ እንድትሆን ያደርግሃል

> እኔ ነጻ ሰው ነኝ፤ የማንም ባሪያ አይደለሁም፤ ነገር ግን ብዙዎችን እመልስ ዘንድ ራሴን ለሰው ሁሉ ባሪያ አደርጋለሁ::
>
> 1ኛ ቆሮንቶስ 9:19
> (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

ብዙዉን ጊዜ ገንዘብ የሚሰጡ ሰዎች ከሚሰጡት የገንዘብ ልገሳ መጠን የተነሣ የሚያመጡት ጠባይ አለ:: መጋቢዎች ከቤተ ክርስቲያን አባላት አሉታዊ ዝንባሌ ነፃ መሆን ይገባቸዋል:: ነቢያቶች፣ "ከፊታቸው የተነሣ አትፍራ::" የሚል ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶዋቸዋል:: የዚህ ምክንያት የሰዎች አገላለጽ ብዙውን ጊዜ ስለሚያስፈራራን ነው:: የድንኳን አገልይነታችን የሰዎች ስጦታ እና ልገሳ እንዳያስፈልገንና ብሉም መጥፎ ዝንባሌን የሚያስወግድበት ጊዜ ይኖራል::

> ወንጌልን መስበኬ አያስመካኝም፤ የምሰብከው ግዴታዬ ስለሆነ ነው፤ ወንጌልን ባልሰብክ ግን ወዮልኝ:: በፈቃደኝነት ብሰብክሽልማት አለኝ፤ በፈቃደኝነት ካልሆነ ግን፣ የምፈጽመው ተግባር የተጣለብኝን ዐደራ መወጣት ብቻ ይሆናል:: ታዲያ ሽልማቴ ምንድን ነው? ሽልማቴማ ወንጌልን ስሰብክ በመብቴ ሳልጠቀም ወንጌልን ያለ ክፍያ መስበክ ነው:: እኔ ነፃ ሰው ነኝ፣ የማንም ባሪያ አይደለሁም፣ ነገር ግን ብዙዎችን እመልስ ዘንድ ራሴን ለሰው ሁሉ ባሪያ አደርጋለሁ::
>
> 1ኛ ቆሮንቶስ 9:16-19
> (በአዲሱ መደበኛ ትርጉም)



## 5. የድንኳን አገልግሎት የገንዘብ አቅምህ ፈቀደም አልፈቀደም ወደ አገልግሎት መግባት እንድትችል ያደርግሃል

> ወንጌልን መስበኬ አያስመካኝም፤ የምሰብከው ግዴታዬ ስለሆነ ነው፤ ወንጌልን ባልሰብክ ግን ወዮልኝ:: በፈቃደኝነት ብሰብክ ሽልማት አለኝ፣ በፈቃደኝነት ካልሆነ ግን፣ የምፈጽመው ተግባር የተጣለብኝን ዐደራ መወጣት ብቻ የሆናል:: ታዲያ ሽልማቴ ምንድን ነው? ሽልማቴማ ወንጌልን ስሰብክ በመብቴ ሳልጠቀም ወንጌልን ያለክፍያ መስበክ ነው::
>
> 1ኛ ቆሮንቶስ 9:6-18
> (በአዲሱ መደበኛ ትርጉም)

ጳውሎስ፤ 'ወንጌልን ባልሰብክ ግን ወዮልኝ' አለ:: አንዳንድ ጊዜ ምርጫ የለንም! ደመወዝ ኖረም አልኖረም ፈቃዱን ልንፈጽም ይገባናል::

ልክ እንዲያ ነው የሚሰማኝ:: ምርጫ ያለኝ አይመስለኝም:: እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ወስኜአለሁ:: ቃሉን ከመስበክ ውጭ ሌላ ነገር ባደርግ፣ እግዚአብሔር የሚያጠፋኝ ይመስለኛል:: ሌሎች መጋቢዎችም ይህንኑ ሲሉ ሰምቼአለሁ::

አንድ ጊዜ አንድ መጋቢ እንዲህ አለ ፣"አገልግሎት ውስጥ ከመግባቴ በፊት፣ እግዚአብሔር እንደጠራኝ አውቅ ነበር:: በአንድ ወቅት ወደ አገልግሎት ባልገባ ኖሮ እግዚአብሔር ይገድለኝ እንደነበር ተሰማኝ::" ጨምሮም፣ "ለዚያ ነው ዛሬ በሙሉ ጊዜ አገልግሎት ውስጥ ያለሁት" አለ::

## 6. የድንኳን አገልግሎት በዚህ ታላቅ አገልግሎት ውስጥ ሚና መጫወትህን ያረጋግጥልሃል

ይህን ሁሉ የማደርገው፣ ከወንጌል በረከት እካፈል ዘንድ፣ ስለወንጌል ብዬ ነው፤

1ኛ ቆሮንቶስ 9:23

(አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

ብዙዎቻችን የትርፍ ጊዜ አገልጋይ ካልሆንን በቀር መንግሥቱን በመገንባት ውስጥ ምንም አስተዋጽዎ ላናደርግ እንችላለን:: ሁሉም ሐዋርያት ናቸው? ሁሉም ነቢያቶች ናቸው? ሁሉም ወንጌል ሰባኪዎች ናቸው? ሁሉም መጋቢዎች ናቸው? በእርግጥ አይደለም! ግን እግዚአብሔር ይባረክ፣ በድንኳን አገልጋይነት ራስህን እየረዳህ ለአገልግሎት ትልቅ አስተዋጽዎ ማበርከት ትችላለህ::

## 7. አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ሥራቸውን እየሠሩ ደመወዝ ሳይከፈላቸው በትርፍ ጊዜ ከሚያገለግሉ ሰዎች ጋር መቀራረብ ይችላሉ

እግዚአብሔር ምሕረትን የተሞላ ነውና ሰዎች ሁሉ ይድኑ ዘንድ መንገድን ያበጃል:: በሙሉ ጊዜ አገልጋዮች ላይ የራሳቸው ግምት ያላቸውና ከእነርሱም መቀበል የሚያስቸግራቸው አንዳንድ ሰዎች አሉ:: የድንኳን አገልጋዮች አገልግሎት ውስጥ የገቡት ለገንዘብ ብለው አይደለምና ከእነርሱ መቀበል ይቀላቸዋል::

## 8. የድንኳን አገልግሎት ውስጥ ለመግባት፣ መሥዋዕትነት ይጠይቃል

የድንኳን አገልግሎት መሠረታዊ ተፈጥሮው መሥዋዕትነት ነው:: ብዙ ሰዎች እንደሚያስቡት ሳይሆን፣ አገልግሎቱ አድካሚና የሚያስጨንቅ ነው:: የሚከፈላቸው አገልጋዮች እንኳ ዋጋ ከፈሉ ይባላል::



ብዙ መጋቢዎች የማያቋርጥ የጉባዔው ፍላጎት የቤተሰብ ሕይወታቸው ውስጥ ጣልቃ ስለሚገባ የቤተሰብ ሕይወት የላቸውም:: በበዓል ወቅት፣ መጋቢው ከቤተሰቡ ጋር ከማሳለፍ ይልቅ፣ የተለያዩ የቤተ ክርስቲያንና ማኅበራዊ ተግባሮች ላይ ይገኛል:: የመጋቢው ልጆች ዐመፀኛ እስኪሆኑ ድረስ ማንም ሰው ግድ አይሰጠውም::

አገልግሎትን የሚጠሉ ብዙ የመጋቢዎች ልጆች አሉ:: አገልግሎት ወላጆቻቸውን እንደሰረቀባቸው ይሰማቸዋል:: ከዚህ በተጨማሪ፣ መጋቢውና ባለቤቱ ከያዙት ኃላፊነት ባሕርይ የተነሣ ብዙ ጫና አለባቸው:: የማንኛውም መንፈሳዊ ጥቃት ዒላማ ነው፣ ብዙ ሰዎች ይህን አይረዱም::

በአንድ ወቅት፣ እስራኤላዊያን ከሶሪያ ጋር ለመዋጋት ሲወጡ፣ የሶሪያው ንጉሥ ለጀኔራሎቹ እና ለሻንበሎቹ ይህን የሚገልጽ ትእዛዝ ሰጠ:: እንዲህ አላቸው:- "ከማንም ጋር አትዋጉ:: ከትልቁም ከትንሹም ጋር አትዋጉ፣ ንጉሡን ብቻ ተዋጉ::

በዚህ ጊዜ የሶሪያ ንጉሥ ሠላሳ ሁለቱን ሠረገላ አዛዦች፣ "ከራሱ ከእስራኤል ንጉሥ በቀር ትንሽም ይሁን ትልቅ ከማንም ጋር እንዳትገጥሙ" ሲል አዞአቸው ነበር፤

1ኛ ነገሥት 22:31

(አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

ከዚህ ትእዛዝ ማየት እንደምትችለው ከእስራኤል ንጉሥ በቀር ዒላማው ማንም ላይ አላነጣጠረም ነበር:: ንጉሡ የሚወክለው የጥቃቱ ዒላማ የሚሆነውን መሪ ወይም መጋቢውን ነው::

አንድ ሰው ያለ ክፍያ የአገልግሎትን መሥዋዕትነት ሲቀበል፣ እጥፍ መሥዋዕትነትን ይቀበላል::

እኔ ነጻ ሰው አይደለሁምን? ሐዋርያስ አይደለሁምን? ጌታችንን ኢየሱስን አላየሁትምን? እናንተስ በጌታ የድካሜ ፍሬዎች አይደላችሁምን? ለሌሎች ሐዋርያ ባልሆን እንኳ ለእናንተ ግን በእርግጥ ሐዋርያ ነኝ፤ ምክንያቱም በጌታ የሐዋርያነቴ ማኅተም እናንተ ናችሁ::

ለሚመረምሩኝ የምሰጠው መልስ ይህ ነው፡፡ ለመሆኑ፣ የመብላትና የመጠጣት መብት የለንምን? እንደ ሌሎች ሐዋርያት፣ እንደ ጌታ ወንድሞችና እንደ ኬፋ ሁሉ፣ እኛስ አማኝ ሚስት ይዘን የመዞር መብት የለንምን? ወይስ ጥረን ግረን መኖር ያለብን እኔና በርናባስ ብቻ ነን?

ለመሆኑ በገዛ ገንዘቡ በወታደርነት የሚያገለግል ማን ነው? ወይን ተክሎ ፍሬውን የማይበላ ማን ነው? መንጋ እየጠበቀ የከብቱን ወተት የማይጠጣ ማን ነው? ይህን የምናደርገው እንደ ሰው አስተሳሰብ ነውን? የኦሪትስ ሕግ ይህንኑ ይል የለምን? በሙሴ ሕግ፣ "የሚያበራየውን በሬ አፉን አትሰር" ተብሎ ተጽፎአልና፡፡ ለመሆኑ እግዚአብሔርን ያሳሰበው የበሬ ጉዳይ ነውን? ይህን የተናገረው በእርግጥ ስለ እኛ አይደለምን? የተጻፈው በትክክል ስለ እኛ ነው፤ ዐራሹ የሚያርሰው፣ አበራዩ የሚያበራየው ከምርቱ ድርሻ እንዳለው ተስፋ በማድረግ ነውና፡፡ እኛ በእናንተ መካከል መንፈሳዊ ዘር ዘርተን ከሆነ ለሥጋ የሚሆን ነገር ብናጭድ ትልቅ ነገር መሆኑ ነውን? ሌሎች ይህን መብት ከእናንተ ማግኘት ከቻሉ፣ እኛ ይበልጥ ማግኘት አይገባንምን?

እኛ ግን በዚህ መብት አልተጠቀምንም፤ ይልቁንም ለክርስቶስ ወንጌል ዕንቅፋት እንዳንሆን ሁሉንም ነገር እንታገሣለን፡፡ በቤተ መቅደስ የሚያገለግሉ ምግባቸውን ከቤተ መቅደስ እንደሚያገኙ፣ በመሠዊያውም የሚያገለግሉ ከመሥዋዕቱ እንደሚካፈሉ አታውቁምን? እንዲሁም ወንጌልን የሚሰብኩ ለኑሮ የሚያስፈልጋቸውን ከወንጌል እንዲቀበሉ ጌታ አዞአል፡፡

እኔ ግን ከእነዚህ መብቶች በአንዱ እንኳ አልተጠቀምሁም፤ አሁንም ይህን የምጽፍላችሁ እንደነዚህ ያሉትን ነገሮች ታደርጉልኛላችሁ በሚል ተስፋ አይደለም፤ ማንም ትምክህቴን ከንቱ ከሚያደርግብኝ ሞት ይሻለኛልና፡፡ ወንጌልን መስበኬ አያስመካኝም፤ የምሰብከው ግዴታዬ ስለሆነ ነው፤ ወንጌልን ባልሰብክ ግን ወዮልኝ፡፡ በፈቃደኝነት ብሰብክ ሽልማት አለኝ፤ በፈቃደኝነት ካልሆነ ግን፣ የምፈጽመው ተግባር የተጣለብኝን ዐደራ መወጣት ብቻ ይሆናል፡፡ ታዲያ ሽልማቴ ምንድን ነው? ሽልማቴማ ወንጌልን ስሰብክ በመብቴ ሳልጠቀም ወንጌልን ያለ ክፍያ መስበክ ነው፡፡

1ኛ ቆሮንቶስ 9፡1-18
(አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

የድንኳን አገልግሎት የክርስትና ባሕርይህን ይፈትናል፡፡ እንደ ራስን መግዛት እና ልከኝነት ያሉ ባሕርያት ይለካሉ፡፡ የሕክምና ተማሪ በሆስፒታል ውስጥ ዶክተር ሳለሁ፣ የዕረፍት ጊዜዬን ለአገልግሎት መሥዋዕት ማድረግ ነበረብኝ፡፡ ሰዎች ቴሌቪዥን ሲመለከቱ፣ ያንን መዝናኛ ሳገኝ አልችልም ነበር፡፡ ዋጋ ለሌለው ማኅበራዊ ግንኙነትና ለጨዋታ ጊዜ አልነበረኝም፡፡ ትርፍ ጊዜዬ በሙሉ ተይዞ ነበር፡፡



# 9. ከፍተኛው የድንኳን አገልግሎት እንቅፋት ራስ ወዳድነት ነው

ብዙ ሰዎች በትርፍ ጊዜ ወይም በድንኳን አገልግሎት እንዳይሳተፉ የሚያደርጋቸው ዋነኛ ምክንያት ራስ ወዳድነት ነው፡፡ ብዙ ሰዎች በመሠረቱ ለሕይወት ያላቸው አመለካከት ግለኝነት ነው፣ ከራሳቸው በቀር ለማንም ግድ የላቸውም፡፡ በራሳቸው ዙሪያ በገነቡት ትንሽ ዓለም ተውጠዋል፡፡ ራስ ወዳድነት የሚያሳየው ግለኝነትን፣ ለራሴ ብቻ፣ ራሴን በተመለከተ፣ ራስን መርዳት እና ራስን ማስደሰትን ነው፡፡

ራስ ወዳድ የሆነ ሰው መቼም ቢሆን የጌታ ባሪያ ሊሆን አይችልም፡፡ ራስ ወዳድነት ለራስህ ብቻ እንድታስብ ሲያደርግህ አገልግሎት ግን ስለማታውቃቸው ሰዎች እንኳ እንድታስብ ያደርግሃል፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ ስለዚህ ሁኔታ አልቅሷል፡፡ ሁሉም ስለ ራሳቸው ደኅንነት ብቻ ግድ እንደሚላቸው አስተውሏል፡፡

እንዲህ አለ፣ "ስለ ጌታ ነገር ግድ የሚለው የለም፡፡"

> ስለ እናንተ ድነት የሚገደው እንደ እርሱ ያለ ማንም የለኝም፤ ሁሉም የኢየሱስ ክርስቶስን ሳይሆን የራሳቸውን ፍላጎት ለማሟላት ይሯሯጣሉና፡፡
>
> ፊልጵስዩስ 2፡20-21
> (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

በተፈጥሮአችን ሁላችንም ራስ ወዳዶች ነን፣ ግን በጌታ ሥር እየሰደድን ስንሄድ፣ ራስ ወዳድነታችን እየቀነሰ ይሄዳል፡፡ የብዙ ክርስቲያኖች መካንነት ከራስ ወዳድነት መንፈስ የመነጨ ነው፡፡

ወደ ሲኦል ቢወርዱ ማን ግድ ይለዋል? ቢያንስ እኔ ወደ መንግሥተ ሰማያት እገባለሁ፡፡ ወንጌልን ያልሰማ አንድ ገጠር ቢኖር ማን ግድ ይለዋል? ቢያንስ ቢያንስ እኔና ቤተሰቤ ደህና ነን፡፡ አንድ ሰው ታሞ

ሆስፒታል ቢተኛ ማን ግድ ይለዋል? እኔ ደህና ከሆንኩ ምን ቸገረኝ:: አንድ ቆሻሻ እስረኛ እስር ቤት ውስጥ ቢማቅቅ ማን ግድ ይሰጠዋል? እኔ ነፃ ከሆንሁ ምን ቸገረኝ!

ያ ነው በቤተ ክርስቲያን እና በክርስቲያኖች ላይ እየሠራ ያለው የራስ ወዳድነት መንፈስ::

ኢየሱስ ራስ ወዳድ ቢሆን ኖሮ፣ በክብር ያለውን ዙፋኑን ትቶ ወደዚህ የበሰበሰ ዓለም ባልመጣ ነበር::

## 10. የድንኳን አገልግሎት ሌላው ትልቅ እንቅፋት ስንፍና ነው

ብዙ ሰዎች ካልተከፈላቸው በቀር ለማንም የመሥራት ዝግጁነታቸው በጣም ዝቅተኛ ነው::

## 11. በድንኳን አገልግሎት ስትሰማራ ብዙ ጥበብ ተጠቀም

> እነሆ፣ እኔ እንደ በጎች በተኩላዎች መካከል እልካችኋለሁ፤ ስለዚህ እንደ እባብ ልባሞች እንደ ርግብም የዋሆች ሁኑ::
>
> ማቴዎስ 10:16

ለእግዚአብሔር ለአገልግሎት ካላቸው እውነተኛ ጥላቻ የተነሣ፣ መጋቢ የሆነን ሰው መተንኮስ ይወዳሉ::

> ከፈሪሳውያንም ወገን የአይሁድ አለቃ የሆነ ኒቆዲሞስ የሚባል አንድ ሰው ነበረ፤ እርሱም በሌሊት ወደ ኢየሱስ መጥቶ፦ መምህር ሆይ፣ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ከሆነ በቀር አንተ የምታደርገውን እነዚህን ምልክቶች ሊያደርግ የሚችል የለምና መምህር ሆነህ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደመጣህ እናውቃለን አለው::
>
> የሐንስ 3:1-2

ብዙ ጊዜ ሰዎች በሥራም ሆነ በትምህርት ቤት ውስጥ ጥፋትህን ይፈልጋሉ:: እንደዚህ ያሉ ነገሮችን ይናገራሉ፣ "አንድ መጋቢ እንዲህ ማድረጉ ይገርመኛል:: መጋቢዎች ወደ ሥራ አርፍደው ይገባሉ ብዬ በፍጹም አልገምትም"::



አስታውሳለሁ በጋና ትልቁ ሆስፒታል በኮሬል ቡ የሕክምና ማስተማሪያ ሆስፒታል ውስጥ በዶክተርነት ስሠራ መጋቢነቴን በፍጹም ነግሬአቸው አላውቅም:: ትንሿን አጋጣሚ በመጠቀም እንደሚነሡብኝ አውቅ ነበር:: ተማሪም መጋቢም በነበርሁበት ጊዜ፣ ሃይማኖተኛ መሆኔን እንኳ ጠቅሼ አላውቅም:: ስለ እኔ ምንም ነገር እንዲያውቁ አልፈልግም ነበር::

መጋቢ ወይም ሃይማኖተኛ መሆንህን ለዓለም ሁሉ እየዞሩ መናገር ሞኝነት ነው:: ኢየሱስ እንደ እባብ ብልህ እንድንሆን ነግሮናል:: እንደ እባብ ብልህ መሆን ማለት ምን ማለት ነው? እባብ ምን ጥበብ አለው? በሚጠሉት ሰዎች መካከል ድምፁን አጥፍቶ መኖር የመቻል ጥበብ አለው::

እባብ በአጠቃላይ የተጠላ እና ከታየ ያለ ምንም ጥያቄ የሚገደል ነው:: ይሁንና ግን፣ እባብ በዙሪያችን ተንሰራፍቶ ይገኛል:: በዓለም ላይ በሚሊዮን የሚቆጠሩ እባቦች አሉ:: እባብ እንዴት አድርጎ ፈጽሞ በሚጠላው ዓለም ውስጥ ሊኖርና ሊበዛ ቻለ? በጥንቃቄ፣ በማመዛዘን፣ በምሥጢር እና በአስተዋይነት ነው::

## 12. በድንኳን አገልግሎት ውስጥ በመሳተፍ በገንዘብ የምትደግፍ ሁን

> እንዲሁ እየደከማችሁ ድውዮችን ልትረዱና እርሱ ራሱ፦ ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብፁዕ ነው እንዳለ የጌታን የኢየሱስን ቃል ልታስቡ ይገባችሁ ዘንድ በሁሉ አሳየኋችሁ::
>
> የሐዋርያት ሥራ 20:35

ከትርፍ ጊዜ መጋቢዎቹ ከፍተኛ የገንዘብ ድጋፍ መምጣቱ በጣም ይገርማል:: ብዙ ጊዜ ልዩ የገንዘብ ድጋፍ ጥያቄ ሲመጣ፣ በጣም የሚደግፉኝ የትርፍ ጊዜ (የድንኳን አገልግሎት) መጋቢዎቹ ናቸው::

በአገልግሎት ውስጥ ስትገባ፣ ለአገልግሎት የሚያስፈልገውን ታውቃለህ። የድንኳን አገልጋዮች ለሁሉም ቤተ ክርስቲያናት ጥሩ ድጋፎች ናቸው።

## 13. የድንኳን አገልግሎት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለን ሥራ ፈትነት ይዋጋል

ሥራ ከቶ ሳይሠሩ፣ በሰው ነገር እየገቡ፣ ያለ ሥርዓት ከእናንተ ዘንድ ስለሚሄዱ ስለ አንዳንዶች ሰምተናልና።

2ኛ ተሰሎንቄ 3፡11

ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለተወሰነ ጊዜ ከቆዩ በኋላ፣ ስብከቶችህን ሁሉ የሚያውቁ ይመስላል። የፈለግኸውን ዓይነት ዘዴ ብትጠቀምም፣ መልእክቱን ማወቅና፣ ከየት እንደመጣም ያውቃሉ።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በተከታታይ የሰበኩትን ስብከት አስታውሳለሁ። ሰዎች በእርግጥ ተባርከውበት ነበር። አገልግሎቱ ምን ያህል ኃይለኛ እንደ ነበር ብዙዎች አስተያየት ሰጡ። ከዚያ አንድ ማስታወሻ ተላከልኝ። ይህ ማስታወሻ ረጅም ጊዜ ከቆየ የቤተ ክርስቲያን አባል የተላከ ነበር።

እንዲህ ብሎ ጻፈ፣ “ውድ መጋቢ በዛሬው ምሽት መልእክትህ እጅግ ተባርከናል።” በመቀጠልም፣ “ከአምስት ዓመት በፊት ይህን ራሱን ነበር የሰበከው። ርዕሱን ብቻ ነው የቀየርኸው።” አሁንም ቀጠል አድርጎ የአሁኑን መልእክት ከየት እንደቀዳሁት ዘረዘረ። ከዚያም ሊያጽናናኝ “ለማንኛውም በኃይለኛ ሁኔታ ስለተባረክን መልካሙን ሥራ ግፋበት” አለኝ።



አየህ፣ የክርስቲያኖች በአገልግሎት ውስጥ መሰማራት አስፈላጊ ነው፤ አለበዚያ ግን በትችት የተጠመዱ ይሆናሉ፣ በማያውቁት ነገር ውስጥ ገብተው የሚተነትኑ እና አስተያየት የሚሰጡ ይሆናሉ።

አቤቱ ልቤ አይታበይብኝ፤ ዓይኖቼም ከፍ ከፍ አይበሉብኝ፤ ከትልልቆች ጋር ከእኔም ይበልጥ ከሚከበሩ ጋር አልሄድሁም።

መዝሙር 131፡1

*ከዚህም ሁሉ በላይ፣ ልጄ ሆይ፣ ተግሣጽን ስማ ብዙ መጻሕፍትን መጻፍ ፍጻሜ የለውም።*